በየ15 ቀኑ

በሀሳብ ልዕልና እናምናለን!

አዲስ ገጽ

ቅጽ 01 ቁ 01 ህዳር 2008 ዓ.ም ዋጋ12 ብር

የርሃቡ ነገር፤ ‘ ‘ግመል ሰርቆ አጎንብሶ’ ’

ብርቱካን አሊን ያየ ኑሮን አያማርርም!

በጃንሆይ መንገድ ...

‹‹የኢሕአዴግ የፍትሕ ሥርዓት አስመሳይ ስለሆነ፤ በውስጡ ላሉት ሁሉ አስጨናቂ ነው››

‹‹የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ አያያዝ እና ቀጥሎም የተፈፀመባቸው ሁሉ፣ ምንም አይነት የሕግ ድጋፍ የለውም››

‹‹የኢትዮጵያን የፍትሕ ሥርዓት ፍጹም እርቃኑን ያስቀረው፣ የሙስሊሙ እንቅስቃሴና የእነአቡበከር አሕመድ በፍ/ቤት እና በሕጋዊ መልኩ መብታቸውን ለማስከበር ያደረጉት እንቅስቃሴ መሆኑን አምናለሁ››

ተማም አባቡልጉ /ጠበቃ/

BBC
Menu
NEWS
Sections
World

Drought takes terrible toll in Ethiopia

አገዛዝ እስካላ ድረስ መራባችን ይቀጥላል!

ያልተገረዙ የመሪዎቻችን አንደበቶች

በቃሉ አጥናፉ (ዶ/ር)

የኢትዮጵያውያንን ሐሳብ ለማፈን የሚፈፀሙ ደባዎች

በፍቃዱ ዘ ኃይሉ

የጠ/ሚ ኃይለማርያም ንግግር እና ሀገርን ሊውጥ ያቆበቀበው ኔትወርክ

ሙሼ ሰሙ

የለውጥ አዋጅ......
እንቢልታው ይነፋ!
ነጋሪት ይጎሰም!

ሰሎሞን ተሰማ


ፈኮኖሚክሱ መለኖሚክስ
የኢኮኖሚ እድገቱ ለማን ነው?
ኤድመን ተስፋዬ
ለምሊ፣ 2007
ፈኮኖሚክሱ መለኖሚክስ የኢኮኖሚ እድገቱ ለማን ነው? ኤድመን ተስፋዬ
0911124769
ዋጋ ብር 60፡80 $ 20

ማውጫ

<<የፍትሕ ሥርዓት አስመሳይ ስለሆነ፣ በውስጡ ላሉት ሁሉ አስጨናቂ ነው>>
ተማም አባቡልጉ /ጠበቃ/
14-15

3 አገዛዝ እስካለ ድረስ መራባችን ይቀጥላል!
4-5 የጠ/ሚ ኃይለማርያም ንግግር እና ሀገርን ሊውጥ ያቆበቀበው ኔትወርክ
6 የኢትዮጵያውያንን ሐሳብ ለማፈን የሚፈፀሙ ደባዎች
7 በጃንሆይ መንገድ ...
8 የውብሸት ስቃይ እና የመቻቻል ናፍቆት
9 ያልተገረዙ የመሪዎቻችን አንደበቶች
10 <<አገርህ በለጸገች ቢሉት፣ እኔ የት ሄጄ አለ?>> ጦም አዳሪ!
11 ሀይ ባይ ያጡት <<ትናንሽ አግዜሮች>>
12 ስምን ከመዝገብ ቃላት እንደማሰረዝ፣ ረሃብን ከአንጀት ማባረሩ ቀላል አይደለም!
13 ተግባራዊ ክብር ለመምህራን!
16-17 ለነፃነት እና ለዕውቀት ትኩረት ያልሰጠ ሥርዓት በኢኮኖሚያዊ ዕድገት የብዙሃኑን ኑሮ ሊያሻሽል አይችልም!
18 የኃይለማርያም ኑዛዜ
19 የለውጥ አዋጅ......እንቢልታው ይነፋ! ነጋሪት ይጎሰም!
20 ስለምልክት ቋንቋ አንዳንድ እውነታዎች
21 የርሃቡ ነገር፣ ''ግመል ሰርቆ አጎንብሶ''
<<አላየንም፣ አልሰማንም፣ አንናገርም>> 22
የፊልም ፖስተር Vs የቤተሰብ ፎቶ 23
የማኅበረሰብ ድረ ገጽ ቆይታችን ትርፍና ኪሳራ 26
ዜና 27
አሁንም ያልፀዳው ቤት - የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን 28

ርዕስ አንቀፅ

አንድ ብለናል!

በ«ፍትሕ» ጋዜጣ ላይ ሀሳቡን በነጻነት በመግለጹ ምክንያት የሶስት ዓመት እስር ተፈርዶበት በዝዋይ እስር ቤት የሚገኘው ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ፣ ጋዜጣዋ ላይ «አንድ በሉ» የምትል አምድ ሥር ይጽፍ ነበር፡፡ እኛም ዛሬ ይህቺን «አንድ በሉ» የምትለዋ አምድ ትዝ አለችን፡፡ ምክንያቱ ደግሞ «አዲስ ገጽ» መጽሔት፣ የመጀመሪያውን ዕትም «አንድ» በማለት መጀመሯን ለመግለጽ ነው፡፡

በኢትዮጵያ የግል ፕሬስ፣ «አንድ» ብሎ ስለመጀመር እንጂ እስከምን ድረስ መሄድ እንደሚቻል በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም፡፡ «አይቻልም» የምንለው ደግሞ በተግባር ተችሎ ስላላየነው ነው፡፡ በኢህአዴግ ዘመን፣ የፕሬስ አዋጅ ወጥቶ ተግባራዊ መሆኑ መልካም ነገር መሆኑን ብናምንም ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ ተፈጥሯዊ እና ሕገ-መንግሥታዊ መብትን በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ መንገድ መልሶ መደፍጠጥ፣ ማፈንና መግደል እጅግ አሳዛኝም አሳፋሪም ተግባር ነው፤ እንደታላቅ ሀገር!

የቀድሞውን ትተን የቅርብ ጊዜውን ብናይ እንኳን ከጥቂት «ተለሳላሽ» ጋዜጦች እና መጽሄቶች በስተቀር፤ ሁሉም የተለያዩ ጫናዎች፣ ወከባዎችና ምክንያቶች እየተፈጸሙባቸው ከመስመር እንዲወጡ ያለርህራሄ ተደርገዋል፡፡ በርካታ ጋዜጠኞች በፍርሃትና በስጋት ሀገር ጥለው ተሰድደዋል፤ ታስረው የተፈቱ፣ ታስረው በእስር ቤት ዛሬም ድረስ የሚንገላቱ መኖራቸውን ለአፍታም ቢሆን አንዘነጋም! በጋዜጠኝነት ሙያ ከልባቸው መስራት ቢሹም ያንን ማድረግ ያልቻሉ ብዙዎች መኖራቸውም ይታወቃል፡፡

በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 51/1 እና 2 ላይ «ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሀገሪቱ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪው የመረጠውን ሥራ የመስራት መብት አለው፡፡ ....ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደሪውን፣ ሥራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው» ተብሎ ተደንግጓል፡፡ ይህ በጣም ጥሩ ነው፣ እናምንበታለንም፡፡ ነገር ግን፣ ጋዜጠኝነትን መተዳደሪያው፣ሥራውንና ሙያውን ያደረገ ኢትዮጵያዊ መብቱን በሕግ መርህ ላይ ቆሞ መተግበር እጅግ አዳጋቹ ነው፡፡ የግሉ ፕሬስ እየተነሳ መውደቁ፣ እየታየ መክሰሙ፣ ለሀሳብ ነጻነት ሲንቀሳቀስ ለእስር፣ ለእንግልትና ለስደት መዳረጉ፤ በጥቂቱ በተግባር የሚደርስበት ችግሩ ብሎም መከራው ናቸው፡፡

ይህንን እያዩ እና እየሰሙም በርካታ አዳጊ እና ወጣት ኢትዮጵያኖች፣ ወደዚህ በአደጋ ቀጠና ወደተከበበው የተከበረ ሙያ ለመምጣት ደፍረት እና ወኔውን ያጡታል፡፡ ድፍረትና ወኔውን ያገኙትም ቢሆኑ «ተው፣ ይቀርባችሁ!» የሚላቸው ብዙ ነው፤ ከቤተሰብ ጀምሮ፡፡ እነዚህንም ተግዳሮቶች አልፈው፣ «አካፋን አካፋ» ብለው ለመስራት የቆረጡ ጋዜጠኞች ደግሞ ከኢህአዴግ በትር ጋር ለመጋፈጥ ራሳቸውን ማሳመን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ስለኢትዮጵያ የግሉ ፕሬስ ፈተናና ተግዳሮት ብዙ ነገር ዘርዝሮ መጻፍ ቢቻልም፤ ዛሬ በዚህ ርዕሠ አንቀጻችን ዋነኛ ወደሆነው ጭብጥ እናምራ፡፡

የግሉ ፕሬስ እጅግ በተመናነበትና በተዳፈነበት ነባራዊ ሀቅ ውስጥ፤ ዛሬ ላይ ሆነን፣ በጠበበችዋ በር መጥተናል፡፡ የፕሬስ አንዱ ኃላፊነት፣ ዜጎች የሕግ አግባብን በጠበቀ መልኩ ሀሳቦቻቸውን በነጻነት የመግለጽ ተፈጥሯዊ እና ሕገ-መንግሥታዊ መብቶቻውን እንዲጠቀሙ መድረኩን መክፈት ነውና፤ የፖለቲካ አመለካከት፣ የኃይማኖት ልዩነት፣ ...ወዘተ ሳንል «የምገልጸው ሀሳብ አለኝ» ለሚል ማንኛውም ኢትዮጵያዊ (የሌላ ሀገር ዜጋም ጭምር) በመጽሄታችን ላይ ሀሳቡን ማስተናገድ ይችል ዘንድ በራችን ክፍት መሆኑን በአክብሮት መግለጽ እንወድዳለን፡፡ የሀሳቦች መንሸራሸር፣ የሀሳቦች ሙግት፣ የሀሳቦች ክርክር፣ የሀሳቦች መስማማትና መለያየት ሀገራችንንም ሆነ ህዝቦቿን ይጠቅማታል የሚል ጽኑ ዕምነት አለን፡፡

በመሆኑም፣ ውድ የ«አዲስ ገጽ» አንባቢያን፣ አንድ በማለት በጀመርናት መጽሔት ላይ ገንቢም ሆነ አራሚ አስተያየቶችን በግልጽ ትሰጡን ዘንድ በቅድሚያ እየጠየቅን፤ መልካም ንባብ ይሁንላችሁ ብለናል!

በሀሳብ ልዕልና እናምናለን!

በኢ.ዲ.አይ.ኤፍ.ዋይ የህትመትና የማስታወቂያ ኃ/የተ/የግል ማኅበር በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊና በኪነ-ጥበብ ጉዳዮች ላይ በማተኮር በየ15ቀኑ ለሕትመት የምትበቃ መጽሔት

ዋና አዘጋጅ፡-
ኤልያስ ገብሩ
elias.gebru@addisgets.com
የካ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 11፣ የቤት ቁጥር አዲስ
ሞባይል፡- +251-912 064882

አምደኞች
በቃሉ አጥናፉ ታዬ ዶ|ር
ኢያሱ ኃይሉ (ዶ/ር)
ኤድመን ተስፋዬ
ኤፍሬም ስዩም
ሠለሞን ተሰማ ጂ.
ደረጀ ታደሠ
ዳንኤል ቢ.
ፍርድያውቃል ንጉሤ
ኢዩኤል ፍስሐ
ምስክር ዐወል
መስከረም ያረጋል
ሃና ረጋሳ
አብርሃም ፈቃደ
ግራፊክ ዲዛይነር፡- አብነት ረጋሣ

በሀሳብ ልዕልና እናምናለን!
አዲስ ገፅ

የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 02፣ የቤት ቁጥር አዲስ
ስልክ ቁጥር ፡- +251-118898912
ሞባይል ፡- +251-911634307
ድረ-ገጽ ፡- www.addisgeths.com
ፌስ ቡክ፡- www.facebook.com/addisgets
Info@addisgets.com

አታሚ፡- ናታን ማተሚያ ቤት

አገዛዝ እስካላ ድረስ መራባችን ይቀጥላል!

ኤልያስ ገብሩ

> “ አገዛዝ እስካላ ጭቆና አለ! አገዛዝ እስካላ ድረስ ኢ-ፍትሃዊነት አለ! አገዛዝ እስካላ ድረስ ኢ-እኩልነት አለ! አገዛዝ እስካላ ድረስ ኢ-ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል አለ! አገዛዝ እስካለ ድረስ መታረዝ አለ! አገዛዝ እስካለ ድረስ በመከራ ቀንበር ማልቀስ አለ! አገዛዝ እስካለ ድረስ አፈና አለ! ኢጋዝዝ እስካለ ድረስ የመረጃ ዕቀባ አለ! አገዛዝ እስካለ ድረስ ልመና አለ! አገዛዝ እስካላ ድረስ መዋረድ አለ! አገዛዝ እስካለ ድረስ መዋሸት አለ! አገዛዝ እስካላ ድረስ እውነትን መደበቅ አለ! አገዛዝ እስካላ ድረስ የእርዳታ እጆችን የማየት እውነታ አለ! አገዛዝ እስካላ ድረስ በምግብ እህል ራስን ያለመቻል ችግር አለ! አገዛዝ እስካላ ድረስ መራብ አለ፤ ያውም በተደጋጋሚ!

ረሃብ እና ድርቅ ሀገራችን ለዓመታት እየደቆሱ በሚሊየን የሚቆጠሩ ውድ ወገኖቻችንን ለሕልፈተ-ሕይወት፣ ለስደት፣ ለመከራ፣ ለችጋር፣ ለእርዛት፣ ለበሽታ፣ ለልመና፣ ለውርደት፣ ...መዳረጋቸው እኛ የጉዳዩ ዋነኛ ባለቤቶችም ሆንን ዓለም ያወቀው ገመናችን ነው፡፡የቅርቡን እንኳን ብናስብ፣ በአጼ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግሥት ሕዝባችን ተርቧል፣ ተርቦም በአሳዛኝ ሁኔታ ሞቷል፤ ተዘርዝረው የማያልቁ ችግሮችን ገፈጥ መቅመስ ሳይወድ ዕዳው ነበር፡፡ በደርግም አሳዛኝና አስከፊ ረሃብ ደርሶ ዓለም የዕርዳታ እጁን ቢዘረጋልንም የረሃብ ተምሳሌት ለመሆን መገደዳችንም የእኛው ሀቅ ነው፡፡ በሕወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝም ረሃብና ድርቅ ከዋኛ የሀገራችን ችግሮች ተርታ የሚመደቡ ናቸው፡፡

ሶስቱም ኢትዮጵያን በተለያዩ ጊዜያት ያስተዳደሩ ገዥዎች፣ ሶስትነትንም አንድነትንም የያዙበት እውነታ አለ፡፡ ሦስቱም የየራሳቸው የተለያየ የአገዛዝ አስተዳደር ቅርጽ እና ባህሪ ቢኖራቸውም፤ ሥልጣንን የዘላለም ርስት አድርገው ለመኖር በመፈለግ፣ ዜጎቻቸውን ጨፍልቀው መግዛታቸው ግን አንድ የመሆን መለያቸው ነው፡፡

በሦስቱም የአገዛዝ ዘመናት፣ በሚሊየን የሚቆጠሩ ኢትየጵያኖች ወገኖቻችን ተርበው ታርዘዋል፤ የሚቀመስ የሚላስ ጠፍቶ መራራ ሞትን ቀምሰዋል፡፡ ተወልደው የኖሩበትን ቀዬ ለቅቀው በግድ ወደሌላ ክልል ተሰድደዋል፤ ቤተሰብ እስከመበተን ደርሰዋል፡፡ እናት ለልጆቿ ጡቷን ሰጥታ ለማጥባት ከነፍሷ ብትጥርም፣ የሚወጣ ወተት ጠፍቶ ልጆች በእናታቸው ጡት ላይ እንደተደፉ በክፉኛ ሞት እስከወዲያኛው አሸልበዋል፡፡እናት እና አባት በረሃብ ጠኔ ተመትተው ልጆች ያለስብሳቢ መራራ ለቅሶን አልቅሰዋል፡፡ባል ከሚስት፣ ዘመድ ከወዳጅ፣ ጓደኛ ከጓደኛ፣ ዘመድ ከአዝማድ፣ ... እስከወዲያኛው ተለያይተዋል፡፡ ከችግሩ መትረፍ የቻሉትም ተለያይተው መኖር ግድ ብሏቸዋል፡፡እናት እና አባትም ውድ ልጆቻቸው በረሃብ አለንጋ ተቀጥፈው፣ የአብራካቸው ክፋዮቻቸውን ያገጠጡ አጥንቶች እንደታቀፉ ወደአፈር በመሪር ሀዘን ከትተዋቸው ነበር፡፡

የዘንድሮውን ረሃብና ድርቅ ተከትሎም በአማራ ክልል የምትገኘዋ ብርቱካን አሊ፣ የአምስት ዓመት ውድ ልጇን አብዱ መሐመድ ሞቶ እንደቀበረችው ስቅስቅ ብላ ነበር ለቢቢሲው ጋዜጠኛ ቃሏን ሰጥታ እኛም ዓለምም ድብቁን ረሃብ ያወቅነው፡፡ የአገዛዙ ፕሮፓጋንዲስቶች ግን «ልጄ የሞተው በድንገት በሽታ ተለየብኝ፣ በረሃም አይደለም» እንድትል በአማራ ቴሌቭዥን አስገደዷት፤ «የ77ቱ ድርቅ እየመጣ ነው» ብለው የነበሩት አቶ አበራ የሚባሉ ግለሰብም ጉዳዩን እንዲክዱ አስገደዷቸው፣ እውነት በፕሮፖጋንዳ ብዛት ባትቀየርም!

ይሄ ሁሉ የእኛ ታሪክ ነው፤ ይሄ ሁሉ የእኛ ውርደት ነው፡፡ ይሄ ሁሉ የእኛ ገመና ነው! ነገር ግን በአጼውም፣ በደርጉም በህወሃት/ ኢህአዴጉም የአገዛዝ ዘመኖች፣ ተመሳሳይ ሁነቶች ነበሩ፣ አሉም፡፡ ዜጎች ተርበው የመከራ ገፈጥ ቀማሽ በነበሩባቸውና በሆኑባቸው ጊዜያቶች ሁሉ፤ የአገዛዞቹ ሹማምንቶች ደስታዎቻቸውን በአደባባይ የገለጹባቸው አጋጣሚዎች ሌላኛው አሳዛኝ እና አሳፋሪ የታሪካችን አካል ነበር፤ ዛሬም ድረስ፡፡

በአጼ ኃይለሰስላሴ ዘመን፣ ዜጎች ተርበው፣ የንጉሡ ልደት ሲከበር ነበር፡፡ በደርጉም ዘመን ዜጎች በረሃብ እንደቅጠል እየረገፉ ለ10ኛው የደርግ ምስረታ በዓል ውስኪ ሲንቆረቆር፣ ከበርቻቻው ሲደምቅ እንደነበረ አሁንም ታሪክ ይነግረናል፡፡ የዛሬውም ገዥ ሥርዓት 15 ሚሊየን ዜጎች በድርቅ እና በረሃብ ተመትተው የአገዛዙ ሹማምነቶች ጡረታ ሲወጡ ለእያንዳንዳቸው 25 ሚሊየን ብር የሚያወጣ መኖርያ ቤት እየታዘጋጀላቸው መሆኑን በተቆጠራቸው ሚዲያዎች በዜና ሲታወጅም ተሰምቷል፤ ረሃቡን መደበቅ የማይቻልበት ሁነት ላይ ሲደረስ፣ በከፊል ማመን እና መካድ የአገዛዙ ሹማምንቶች ዕጣ ፈንታም ሆኖ ታይቷል፡፡ በዚህ በሳዛኝ የመከራ ወቅት የብአዴንን 35ኛ ዓመት ለማክበር ሽር ጉድ ማለታቸውም አልተገታም ነበር፡፡ወገን ለድርቅ ተጋልጦ እና ረሃብ ከደጃፉ ቆሞ፣ ከአምና ጀምሮ የህወሃትንና የኦህዴድን፣ ዘንድሮ ደግሞ የብአዴንን በዓል ብዙ ሚሊየን ብሮች በማውጣት ማክበሩም ከግብዝነት በላይ ምን ዓይነት ስያሜ እንሰጠው ይሆን?! ምኞት ላይ የተቀመጡ፣ የኢጋዛዙ ሹሞች እና ከታች ያሉ ታዛዥ አስመሳዮች፣ ድርቁም ሆነ ረሀቡ እንዴት ይግባቸው? የማይሰማ ጆሮ፣ የደነደነ ልብ፣ አይቶ እንዳላየ የሚያልፍ ዐይን አላቸውና!!!

በድርቅ መመታትና በረሃብ አለንጋ መቀጠፍ፣ በእኛ በኢትዮጵያኖች ብቻ የደረሰ ባይሆንም እንደኛ ግን ድርቁም ሆነ ረሃቡ ተፈራርቆ፤ የረሃብ ተምሳሌትነት ታፔላ የተለጠፈበት ሀገር የለም፡፡ «በተፈራራቂ ድርቅ እና ረሃብ ኢትዮጵያንና ዜጎቿን እንዲመቱ ለምን ሆነ?!» የሚለው ጥያቄ የጊዜው አንገብጋቢ ጉዳይ ይመስለኛል፡፡ ወቅት ጠብቆ ድርቁም ረሃቡም ተከታትለው ይመጣሉ፡፡ ዜጎችም የድረሱልኝ ጩኸት ያሰማሉ፡፡ በሀገርም ሆነ ከሀገር ውጪ የእርዳታ እጆች እስከመማጸን ደርሰው ይዘረጋሉ፡፡ በጊዜ ሂደት፤ የሚሞተው ሞቶ፣ የታረዘው ታርዞ፣ የሚፈናቀለው ተፈናቅሎ፣ የሚታመመውም ታምሞ፣ የሚቸገረውም ተቸግሮ ችግሩ ጋብ ይልና ዳግም ወቅት እና ቀን ጠብቆ አድብቶ ይነሳል፤ አድብቶ መግደሉን ይጀምራል፣ አድብቶ የመከራ በትሩን ያሳርፍብናል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት ከምር አስበን በጽናትና በአንድነት እስካልቆምን ድረስ፣ እየተሰጡ ያሉትና የሚሰጡ በቂ ያልሆኑ ጊዜያዊ እርዳታዎች ጊዜያዊ ሆነው ብቻ ያለፋሉ፡፡ጊዜ ያልፍና ደግሞ ሌላ ረሀብና ድርቅን እንደለመድነው እናስተናግዳለን፡፡

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ “Institute of Development research” ሥር ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ ለ10 ዓመት ያህል በ102 የኢትዮጵያ ወረዳዎች ላይ ምርምር አድርገው፤ ስለድርቅ በእቸው አጠራር «ችጋር» “Rural vulnerability famine in Ethiopia 1958-1977” የሚል መጽሐፍ ጽፈዋል፡፡የ«እምቢልታ ጋዜጣ» ዋና አዘጋጅ የነበረችው ጋዜጠኛ ጽዮን ግርማ በ2000 ዓ.ም ተከስቶ በነበረው የድርቅ ሁኔታ ላይ ከፕሮፌሰር መስፍን ጋር ባደረገችው ቃለ-ምልልሷ ዋነኛ ችግሩን አስመልክቶ እንዲህ የሚል ምላሽ ሰጥተዋት ነበር፡-

«ችጋር የሚመጣው በድርቅ ወይም በተምችና በሌሎች የሰብል ተባዮች ወይም በዝናብ ብዛትና በበረዶ ወይም እግዚያብሔር በመቆጣት ወይም በእነዚህ ሁሉ ነው ይባላል፡፡ እነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሚደረደሩት ሆን ተብሎ በማንም ላይ ኃላፊነት እንዳያርፍ ለማድረግ ነው፡፡ ሁሉም ከእውነቱ የራቀ ነው፡፡ እውነቱ ነገር፣ እነዚህ ሁሉ የተፈጥሮ ችግሮች በብዙ ችግሮች ይከሰታሉ፤ ሆኖም በዚህ ምክንያት ሰዎች በችጋር አለማለቃቸው ነው፡፡ እውነቱ ነገር ችጋር የአገዛዝ ሥርዓት ውጤት መሆኑ ነው፡፡ እውነቱ ነገር ችጋር ኅብረተሰቡ በአገዛዝ ሥርዓት ደንዝዞና በራሱ የኑሮ ትግል ተተብትቦ የመተሳሰብና የመረዳዳት መንፈሱ የተሟጠጠ መሆኑ ነው፡፡ እውነቱ ነገር፣ ችጋር የሚጀምረው የድርቅ ወቅት ከመድረሱ በጣም ቀድሞ ነው፡፡

«ገበሬው ነጻነት ከሌለው ችጋር በኢትዮጵያ ይኖራል» ብለው የሚስጠነቀቁት እኚህ ምሁር፤ እንዲህ በማለትም የችግሩን ቁልፍ ይገልጻሉ፡-

«...በሕዝብ ፍቃድ ላይ የተመሰረተ መንግሥት፤ የህዝብን ፍላጎት የሚፈጽም፣ ነገ ይሄ ህዝብ ከስልጣን ያወርደኛል ብሎ የሚሰጋ መንግሥት ካላ አስፈላጊውን ሁሉ አድርጎ ችጋሩን ማስወገድ ይችላል፡፡ ግን ሀገር አስተዳዳሪው መንግሥት ለጉዳዩ ግድ የሌለው ከሆነ ያ ገበሬ እንዴት ብሎ ነው ከችጋር ሊወጣ የሚችለው? አቅሙ የለውም፣ ነጻነቱ የለውም፣ ነጻነት፣ አቅም፣ ችሎታና ወኔ የሌለው ገበሬ ሁልጊዜ ሞት አፋፍ ላይ ነው ያለው፤ አንድ ትንሽ ነገር ሲደርስበት ክንብል ብሎ ይወድቃል»

በአሜሪካን ሀገር በቅርቡ የተመረቀችው «7 ኪሎ» ጋዜጣ ባልደረቦች የሆኑት ሜሮን አ. እና ዐብይ ተክለማርያም «ስለረሃብ ገና ብዙ እናወራለን» በሚለው ሰፊ መጣጥፋቸው መቋጫ ላይ፣ «ያለ ዴሞክራሲ፣ ያለ ኢንዱስትላይዜሽን ከርሃብ አደጋ ጋር መተናነቅ ሞኝነት ነው፤ ይኼን ስናጤን የ2008 ዓ.ም የርሃብ ዜና እና እርሱን ተከትሎ የሚመጣው የህዝብ ቁጣ ማክተሚያ እንደማይኖረው እንደራለን» በማለት ያስገነዝባሉ፡፡

በመሆኑም እላለሁ፣ አገዛዝ እስካላ ጭቆና አለ! አገዛዝ እስካላ ድረስ ኢ-ፍትሃዊነት አለ! አገዛዝ እስካለ ድረስ ኢ-እኩልነት አለ! አገዛዝ እስካላ ድረስ ኢ-ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል አለ! አገዛዝ እስካለ ድረስ መታረዝ አለ! አገዛዝ እስካለ ድረስ በመከራ ቀንበር ማልቀስ አለ! አገዛዝ እስካለ ድረስ አፈና አለ! ኢጋዝዝ እስካለ ድረስ የመረጃ ዕቀባ አለ! አገዛዝ እስካለ ድረስ ልመና አለ! አገዛዝ እስካላ ድረስ መዋረድ አለ! አገዛዝ እስካለ ድረስ መዋሸት አለ! አገዛዝ እስካላ ድረስ እውነትን መደበቅ አለ! አገዛዝ እስካላ ድረስ የእርዳታ እጆችን የማየት እውነታ አለ! አገዛዝ እስካላ ድረስ በምግብ እህል ራስን ያለመቻል ችግር አለ! አገዛዝ እስካለ ድረስ መራብ አለ፤ ያውም በተደጋጋሚ!

ይኼ እንዳይሆን፣ «ረሃብ በቃን!» ብለን ለዘላቂው መፍትሄ በበብርቱ እናስብ፣ አስበንም እንተግብር!!!

የጠ/ሚ ኃይለማርያም ንግግር እና ሀገርን ሊውጥ ያቆበቀበው ኔትወርክ

«ሲያይ የገባን ሲሰማ ቅበረው»

ሙሼ ሰሙ

ሰሞኑን በሃገራችን የተከሰተውን የድርቅ ችግር ተክቶ ከተማውን እያመሰው የሚገኘው ጉዳይ ቢኖር፣ የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ልዩ የካቢኔ ስብሰባ ነው።«ምክንያታዊ ነን» የሚሉም ሆነ በድፍን ወቀሳ የተጠመዱ በርካታ ሰዎች ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም በሥርዓት አልበኞችና በሙሰኞች ላይ ያቀረቡትን ሃሳብ እያወገዙት ይገኛሉ።አንዳንዶች ደግሞ የቀረበውን ሃሳብ እጅግ አጋንነው፣ አንቆለጳጵሰው፣ የጦር ሜዳ ድል አስመስለውና የደፋር የጀግና ተምሳሌት በማድረግ ጉዳዩን ወደ ሰማየ ሰማያት የሚያጦዙትን ያህል ሌሎቹ ደግሞ «የተለመደ የኢህአዴግ ማደናገርያ» ብለው የሚያዋድቁት ገጥመውኛል።

የእኔ አመለካከት ከሁለቱም ጎራ ለየት ይላል። በእኔ እምነት፣ አጀንዳው የማደናገሪያም ሆነ የደፋርነት ምሳሌ አይደለም። ይልቁንም ጉዳዩ ከሕግ የበላይነትና ሥርዓትን ከማስከበር ውጭ ተጋንኖም ሆነ ተንኳስሶ ሊቀርብ አይገባውም። አቶ ኃይለማርያም ሙስናን አምርሮ ለመታገል ያቀረቡት ሃሳብ ወቅታዊና አስፈላጊ ነው። ነገር ግን፣ጉዳዩከሕግየበላይነትውጭየደፋርነትምሆነየጀግንነት ትርጉም መስጠት ለሕግ የበላይነት ያለንን አመለካከት ምን ያህል የተዛባ መሆኑን የሚያመላክት ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀረቡት አጠቃላይ ወቀሳ ድፍረት የሚሆነው ማስረጃና መረጃ ሳይኖራቸው የተናገሩ ከሆነ ብቻ ነው።

በአቶ ኃይለማርያም አቀራረብ ላይ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች የተምታቱ ይመስለኛል። መምታታቱ የተፈጠረው ከአቀራረብ ችግር ወይም ከአጀንዳው ስር የሰደደ መሠረታዊ ባሕርይ ሊሆን ይችላል። ማጠቃለያ ሃሳቡ በአንድ በኩል ጽናትና ቁርጠኝነትን ያመለከተ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለአንድ ያልታወቀ ኃይል ትብብርና ተማጽኖን የሚጠይቅ ስለሚመስል ለተፈጠረው መደናገር አቀራረቡ መነሻ ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ።

ሪፖርቱን ተከትሎ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለካቢኔው ባቀረቡት ማጠቃለያ ላይ የተምታታው አንደኛ ጉዳይ፣ «እዚህ ተነጋግረን ስንወጣ የራሳችንን ኔትወርክ እንከላከላለን» የሚለው ሃሳብ ላይ የሚያጠነጥን ነው።ዜጎች የሃገራችን ሙሰኞች የጣሊያንን ማፊያ ያህል የሚፈሩት የመንግሥት ካባ ውስጥ ተከልለው፣ የመንግሥት ጥበቃ የሚያገኙ፣ «የመንግሥት ተቀጽላ ስለሆኑ» …ወዘተ የሚለውን መላምት ማመን ከጀመረ ውሎ አድሯል።በዚህም ምክንያት አቶ ኃይለማርያም በካቢኔያቸው ውስጥ ተጠርጣሪዎች እንደሚገኙ ማመላከታቸው ብዙዎችን አስደምሟል። በሕዝብ ዘንድ በአንድ በኩል «ምን ተከሰተ? ተጣሉ እንዴ?» የሚል ጥርጣሬን ሲያጭር በሌላ በኩል «ድፍረት ካልሆነ እንዴት እንዲህ ሊሉ ቻሉ?» የሚሉ ሃሳቦች ተሰራጭተዋል።

በእኔ በኩል ግን አሁንም የጉዳዩ መነሻም ሆነ መድረሻ የሕግ የበላይነት ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም በዚህ ደረጃ ከፍተኛ ተሿሚዎቻቸው ላይ ጣት የቀሰሩት ያለመረጃ ወይም ማስረጃ ነው ብዬ ለመገመት እቸገራለሁ። እውነታው ይህ ከሆነ ደግሞ ከሾሟቸው እንኳን አንድ ወር ካልሞላቸው የካቢኔያ አባሎች መካከል በዚህ ደረጃ ጣት የሚቀስሩበት መኖሩ ቀድሞውንም አሿሿማቸውን ዞር ብለው እንዲመረምሩ የሚያስገድድ ሁኔታ ነበር ማለት ነው። ከሕግ የበላይነትና ከተጠያቂነት አኳያ ስንመለከትው፣ ይህንን ክስተት ለማረም ደግሞ ከእሳቸው በላይ በሕገ-መንግሥቱ ሥልጣን የተሰጠው ምድራዊ ኃይል የለምና «ምን እያሉ ነው?» የሚል ጥያቄ ያጭራል። እሳቸው ቀድሞውንም ቢሆን «ኔትወርክ ተከላካዮቹን» ከካቢኔያቸው ለማስወገድ ከአዲሱ የካቢኔ ዘመን በላይ የተሻለ አማራጭ ከየት ሊያገኙ ይቻላቸዋል? ከሞራልም ሆነ ከሕግ የበላይነት ሚዛን ሲታይ፣ የካቢኔያቸው ሹም ሽር ከወር በፊት በከፍተኛ ድምጽ አስጸድቀው ከወር በኋላ በአናቱ ላይ ቀርበው በከፊልም ቢሆን በካቢኔያቸው ላይ ወቀሳ ማካሄዱ «ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ተሿሚዎቻቸውን በቅጡ አልመረመሩም» የሚል ጥያቄ የሚያጭር ነው።

ሁለተኛው ጉዳይ፣ በውይይቱ ላይ በስም ባይነሳም በተዘዋዋሪ መንገድ ተማጽኖ ሲቀርብለት የነበረው ድብቅና አሰናካይ ኃይል ጉዳይ ነው። በዚህ አጀንዳ ላይ ወደ ጽሑፌ ማጠናቀቂያ ላይ እመለስበታለሁ። ለዚህ መልስ ከመስጠቴ በፊት ሙስናና ኢህአዴግ ምንና ምን ናቸው ወደሚለው መነሻዬ ልምጣ።

ኢህአዴግ ደርግን አስወግዶ ሥልጣኑን ካደላደለበት በተለይ ከ1990 ዓ.ም ወዲህ የመልካም አስተዳደር እጦት፣ የፍትሕ መዛባት፣ የሃብት ክፍፍል ለጥቂቶች ማጋደልና የእነዚህ ሁሉ ማኅበራዊ ቀውሶች አባት የሆነው የሙስና መንሰራፋት ጉዳይ በሕዝብ ዘንድ እሮሮ ሆኖ ከመቅረብ የቦዘነበት ጊዜ አልነበረም። ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የግሉ ፕሬስ አባላት የሕዝቡን ምሬቶች አንግበው ጮኸ ብለው በማስተጋባት ችግሮቹ መፍትሔ እንዲያገኝ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ታግለዋል፤ መስዋዕትነትም ከፍለዋል።

ለዚህ የሚመጥን መፍትሔ ግን ከኢህአዴጋውያን ጎራ ጠብ ብሎ አያውቅም። ይልቁንም የሕዝብ ምሬት ተጠናክሮ ሥር-ነቀል ለውጥ ፍለጋ እየማሰነ መሆኑን ሲረዳ ኢህአዴግ የሕዝቡን ቁጣ ገና ከጅምሩ ለማዳፈን ወይም እራሳቸው ኮትኩተው ያሳደጉት የሙስና ሃይል ጡንቻውን አፈርጥሞ የሥልጣን ዘመናቸውን አደጋ ላይ ሲጥል መነቃቃትና ጊዜያዊ መፍትሔ ፍለጋ ራሳቸው ታምሰው ሃገሩን ማመሳቸው የተለመደ ጉዳይ ነው። ኢህአዴግ በሥልጣን ዘመኑ ውስጥ አንድም የተሳካ የሙስና ትግል አካሂዶ አያውቅም። በአንድ ወቅት «ከእንጥል መበስበስና ከአናት መግማት» ብሎ «በቦና ፓርቲዝም» ላይ ከተጀመረው ንቅናቄ አንስቶ በርካታ ድፍረት የተሞላባቸው ጥናቶችና ዕቅዶችን በሙስናና በመልካም አስተዳዳር መሰናክሎች ላይ ያወጣ ቢሆንም ጅምሮቹ ጅምር ከመሆን መዝለል እንዳቃታቸው ይታወቃል።

ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የግሉ ፕሬስ እነዚህንና መሰል ምሬት የቀሰቀሳቸው ሕዝባዊ አጀንዳዎችን አንግበው መፍትሔ ፍለጋ ያካሄዷቸው እንቅስቃሴዎችም ሙስናን በመታገሉ ሂደት አጋዥ ሃይል አድርጎ መጠቀም ሲገባ እንዲያውም በተቃራኒው ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የግሉ ፕሬስ ለእንግልትና ለእስር ተዳርገዋል።ኢህአዴግም ጥልቅ እሮሮ በሚሰማበትና ለመታገል ሰፊ ተነሳሽነት በሚታይበት የሙስና ጉዳይ ላይ ሁሉንም አስተባብሮ →

ቢጋራ ለችግሩ መፍትሔ በማፈላለግ ኃላፊነቱን ከመወጣት ይልቅ ተቃዋሚዎችን ኃላፊነት የማይሰማቸው፣ በሃሰት የሚወነጅሉና የገጽታ ግንባታ ጸሮች አስመስሎ በማቅረብ አልፎ ተርፎም ችግሩ ጥልቀት የሌለው፣ የጥራዝ ነጠቆች ቱማታ አስመስሎ ሕዝቡን በመደለል ውሎና አዳሩን ማሳመርን አማራጭ አድርጎ ቆይቷል።

ምንም እንኳን ተቃዋሚዎችና የግሉ ፕሬስ አባላት ከሕዝብ ተቀብለው ያቀጣጠሏቸው አጀንዳዎች በኢህአዴግ የማጣጣልና የማዳከም ወይም ሕዝብን የማዘናጋት ስልት ተልፈስፍሰውና ተዳክመው ለጊዜውም ቢሆን ከዕይታ የተሰወሩ ቢመስሉም ውሎ አድሮ ግን ችግሮቹ በወቅቱ ባለመቀጨታቸው እንደገና ጎልብተውና ተጠናክረው እያገረሹ በመመለስ የሕዝብን ጉስቁልና ማባባሳቸው እየታየ ነው።

በዚህ ሂደት ውስጥ እርግጥ ነው፤ ኢህአዴግ ፋታ አግኝቶ፣ ጊዜ ገዝቶ ሊሆን ይችላል። ተቃዋሚዎችም መሠረታዊ የሆነውን ሕዝባዊ አጀንዳ ተነጥቀው ወይም በማዋከብ ምክንያት አጀንዳውን ችላ ብለውት ሊሆን ይችላል። ከዘለቄታዊ የሕዝብና የሀገር ጥቅም አኳያ ግን ኢህአዴግ የተከተለው ስልት ያስገኘው ጉዳይ ቢኖር ሕገ-ወጦች፣ ሙሰኞች፣ በዘር፣ በጥቅምና በሃይማኖት ተደራጅተው ሕዝቡን ሲያንገላቱና ሀገሪቱን ሲቦጠቡጡ የነበሩ ሃይሎች ትንፋሽ አግኝተው እንዲጠናከሩና የሕዝቡን መከራ ማራዘማቸው ብቻ ነው። በዚህ አካሄዱ ኢህአዴግም ቢሆን ከዕለት ወደ ዕለት በማይወጣው ፈተና ውስጥ እየዳከረ መሆኑ የሰሞኑ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ግምገማ አመላካች ነው።

«ውሃን ከጥሩ፣ ነገርን ከስሩ» እንዲሉ በመንደርደርያነት ከላይ የጠቃቀስኳቸው ጉዳዮችን ሂደትን ያመላከቱ ናቸው። ከላይ እንደጀመርኩት፣ በኢህአዴግ/ በመንግሥት በኩል ሙስናንና መልካም አስተዳደርን ለመታገል የተካሄደው ስብሰባ ግን ዋነኛ መነሻዬ ነው። ስብሰባው በዝርዝር እንዳመላከተው ሙስናውና የመልካም አስተዳደር እጦቱና የፍትሕ መጓደሉ ውሎ አድሮ ስር በመስደድ ደርግ በአብዮቱ ዘመን «አብዮት ልጆቿን ትበላለች» ይል እንዳልነበረ ሁሉ፣ ዛሬ ላይ ደግሞ ታሪክ እራሷን በተወላገደ መልኩም ቢሆን ደግማለች። የቀድሞውም ሆነ የአሁን ጠቅላይ ሚኒስትሮች እንዳሉት፤ ስር ሰደደው የሙስና ችግሩ እራሱንም ሆነ ሕዝብ አዘናግቶ እዚህ ያደረሰውን ሥርዓትና ኢህአዴግን ሊበላቸው አቆብቁቧል።

የችግሩ መጠንና ስፋት በተለያየ ጊዜና በተለያዩ መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ተቋማት አማካኝነት የሙስናው ችግር ስፋትና ጥልቀት እንዲሁም አሳሳቢነት መጠን የተገለጸ ቢሆንም ጉዳዩ ሰሚ ጆሮ ሳያገኝ በመቅረቱ ዛሬ ላይ ከፍተኛው የሥልጣን አካል ስለሙስና ሲወያይ በከፊል እጅ ሰጥቶ ሊሆን ችሏል። ሰሞኑን በተደረገው ግምገማ ላይ በጥናት ተደረሰበት የተባለው የሙስና፣ የመልካም አስተዳደር እጦትና የፍትሕ መጓደል ስፋትና ጥልቀት ከዚህ በፊት ከተቃዋሚዎች በተለይ ደግሞ ሕዝብ በምሬት ሲነሳቸው ከነበሩት ዝርዝር ጉዳዮች የተለየ ነገር አልያዘም። ለየት የሚያደርገው ነገር ካለም ሙስናው በጉዳዩ ዋነኛ ባለቤት በኢህአዴግ ሲወሳ ማድመጣችን ነው። በዚህም ምክንያት አጀንዳው አዲስ ነገር ይዞ አለመቅረቡ ብቻ አይደለም አቀራረቡም ለአንድ ለማይታና ለማይዳሰስ ኃይል ተማልዶ ትብብርን የሚጠይቅ መሆኑ ይበልጥ ቁርጠኝነትን እንድንጠራጠር ያደረገ ነው።

ኢህአዴግ በሥልጣን ዘመኑ ከሕዝብ የተሰጡት ሕዝባዊ አደራዎች ወደ ሕዝባዊ እሮሮ ተለውጠው አስከፊ ደረጃ ላይ መድረሳቸውን በጥናት ደርሼበታለሁ የሚለው ጊዜ ጉዳዮቹ «ለያዥ ለገናዥ» ካስቸገሩ በኃላ ዛሬ ላይ ነው። ኢህአዴግ እራሱ ሊያዳምጠውና ሊያስታውሰው ከፈቀደው ትናንት ሌላ ትናንት የለም። የሙስና ጉዳይ፣ የመልካም አስተዳደር እጦትና የፍትሕ መዛባት ትናንት በተቃዋሚዎች፣ በሙያ ማኅበራት፣ በጋዜጠኞች …በተለያዩ አካላት አማካኝነት በስፋትና በጥልቀት ሲተነተን የኖረ ጉዳይ ነው። በሙስና ዙሪያ ብዙ የተባለለትና በርካታ መረጃና ማስረጃ የቀረበበት ትናንት የኢህአዴጋውያን ስላልነበር በታሪክ ውስጥ እንደሌለ ተቆጠሯል፤ ተዘሏል። በዚህም ምክንያት የችግሩ ተዋናዮች ብቻ ሳይሆኑ ችግሩ እዚህ እስኪደርስ እያወቀ እንዳላወቀ ሆኖ ትናንትን የረሳው ኢህአዴግ የሁላችንንም ጥሪ በቸልተኝነት በማለፉ ዳፋው ከሕዝብ ደፍ አልፎ እራሱ ኢህአዴግ ደፍ መፍሰስ ጀምሯል፣ እንደ ድርጅትም የሙስናው ማዕበል እየናጠው ይገኛል። ዛሬስ ኢህአዴግ ከዚህ ስህተቱ ይማር ይሆን? ውሎ አድሮ የምናየው ይሆናል።

በእኔ እምነት አንድ መንግሥት ዋነኛ በሆኑት ሙስናን ማዳከም፣ መልካም አስተዳዳርና ማስፈን፣ ፍትሕን ሚዛናዊና ፍትሐዊ ማድረግ ሳይችል «የሕዝብ ድጋፍ አለኝ» እያለ በመንግሥት መቀጠሉ ለራሱም ቢሆን ሊያስደንቀው ይገባል። ምክንያቱም ማንኛውም ድርጅት የኢኮኖሚያዊም ሆነ የፖለቲካዊ ወይም የማኅበራዊ ጉዳዮች ቁልፍ መሳሪያ የሆኑትን መልካም አስተዳዳርንና ፍትሕን ማስፈንና ካልቻለና ሙስናን ከስሩ ካልነቀለ በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ የመንግሥትነት ሚናው ሆነው ከሰፈሩት ነገሮች ውስጥ ማሳካት የቻለው የቱን እንደሆነ እንድጠይቅ ያደርገኛል።

ለማጠቃለል ያህል፡- በዚህ ደረጃ የተዛነፈ አሰራርን ተሸክሞ በቀጥታ «አካፋን አካፋ» ማለት እና «እናውቃለን እዚህ ካቢኔ ውስጥ ተጠርጠሪዎች አላችሁ» ወይም «ፓርቲያችንም ቢሆን የዚህ ችግር ሰለባ ሆኗል» ማለት ለየቅል ናቸው። ይህ ደግሞ በምንም መስፈርት የቁርጠኝነት መለኪያ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም። ግምገማውን በቅጡ ላዳመጠው የንቅናቄው ቁርጠኝነትም ቢሆን በውሳኔ መልክ የቀረበ ሳይሆን ገና በጥያቄና በስጋት መልኩ የቀረበ ነው። ከግምገማው በመነሳትም «ውጤታማ ሥራ ለመስራት ያስችላሉ» በሚል ለከፍተኛ አመራሩ የቀረቡት መነሻዎች የቀረቡበት መንገድ ድምጹ ለማይሰማ አንድ ሃይል ስጋት በተሞላበት ተማጽኖ፣ አልፎ ተርፎም ትብብርን በሚጠይቅ መልኩ የቀረበ ስለነበረ ሂደቱ ከወዲሁ እንዳይኮላሽ ስጋት አለኝ። «ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው» ይባላልና።

ከላይ ለማንሳት እንደሞከርኩት፣ ሂደቱ ላይ አንድ የማይታወቅ የተሰጋ ኃይል እንዳለ የሚጠቁም በርካታ ነገሮች በተደጋጋሚ ተነስተዋል። አልፎ ተርፎም «ሁላችንም ካመንበት፣ ከተስማማንበት» በሚል ከወዲሁ ጥርጣሬና ጥያቄ የሚያጭሩ ቁርጠኝነታችን በራስ መተማመን የጎደለው ዝንባሌ ታይቷል። በተለይ ደግሞ እነዚህ መሠረታዊ ጉዳዮች የሚጣሱትና የሚጨፈለቁት በሌላ መጤ ኃይል ሳይሆን በራሱ በኢህአዴግ አባላትና በከፍተኛ አመራሮች መሆኑ ሲተነተን መስማት በጥቅሉ «ኢህአዴግ ምን እያለ ነው?» የሚያስብል ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

የኢህአዴግ ተነሳሽነትና ፍላጎቱ ሙስናን፣ የመልካም አስተዳደር እጦትን መታገል ሊሆን ይችላል። ነገር ግን፣ በዚህ ስብሰባ ላይ ቁርጠኝነቱም ሆነ አቅሙ በማያወላዳ መልክ አልታየኝም። ኢህአዴግ በመጀመሪያ ሂደቱን በማደናቀፍና ውጤቱን በማንከላወስ ወይም ንቅናቄው ላይ በማፌዝ የሚያዳክሙትን ከወዲሁ ካላጠራ ስለቁርጠኝነትም ሆነ ስለመፍትሔ ሰጭነት እንዴት ሕዝብ ፊት ቀርቦ መናገር እንደሚችል ግልጽ አይደለም። በእኔ እምነት፣ ኢህአዴግ በተደጋጋሚ የመማር ዕድል ተሰጥቶታል። ዛሬ ላይ ግን ማለት የሚቻለው «ሲሰማ የገባን ሲያይ ቅበረው ነው»■

> ስብሰባው በዝርዝር እንዳመላከተው ሙስናውና የመልካም አስተዳደር እጦቱና የፍትሕ መጓደሉ ውሎ አድሮ ስር በመስደድ ደርግ በአብዮቱ ዘመን <<አብዮት ልጆቿን ትበላለች>> ይል እንዳልነበረ ሁሉ፤ ዛሬ ላይ ደግሞ ታሪክ እራሷን በተወላገደ መልኩም ቢሆን ደግማለች። የቀድሞውም ሆነ የአሁን ጠቅላይ ሚኒስትሮች እንዳሉት፤ ስር ሰደደው የሙስና ችግሩ እራሱንም ሆነ ሕዝብ አዘናግቶ እዚህ ያደረሰውን ሥርዓትና ኢህአዴግን ሊበላቸው አቆብቁቧል።

የኢትዮጵያውያንን ሐሳብ ለማፈን የሚፈፀሙ ደባዎች

በፍቃዱ ዘ ኃይሉ

ከወረቀት አንስቶ እስከ በይነመረብ ድረስ የሚደረጉ ዕቀባዎች በሙሉ የሚደረጉት በማንም ላይ አይደለም። በኢትዮጵያውያን ላይ ነው። የገዢ ልሒቃኑ ይህንን የሚያደርጉት በብዙኃኑ ጥቅም እያሳበቡ ነው፡፡ብዙኃን ግን እነማን ናቸው? ራሳቸውን መግለጥ እና የሚጠቅማቸውን መረጃ ማግኘት ያልቻሉ ብዙኃን ተጠቃሚ የሚሆኑት በምን መንገድ ነው? ብዙኃን ገንዘባቸውን የሚከፍሉለት እና በሥማቸው በተገኘ ገንዘብ የሚተዳደሩት «የመንግሥት» ብዙኃን መገናኛዎች እውን ብዙኃኑን እያገለገሉ ነው ወይስ የገዢ ልሒቃኑን? እነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች እንዲዳፈኑ፣ መንግሥት ይተጋል፡፡ምክንያቱም ኢትዮጵያውያን ሐሳባቸውን መግለጽ እና የሌሎች አቻዎቻቸውን ሐሳብ ማድመጥ የቻሉ ጊዜ ኢሕአዴግ ታሪክ የሚሆን እንደሆነ ያውቃልና!

ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው መንግሥት የደኅንነት ኃይሎች ቁጥጥር ሥር ስውል፥ በቦርሳዬ የነበረች አንዲት የማስታወሻ ደብተርም አብራኝ በቁጥጥር ሥር ውላለች። ማስታወሻ ደብተሯ ለመጠመር ወይም ለማጥናት የምፈልጋቸውን ጉዳዮች ባጭሩ የማሰፍርባት ነች። ለጦማር ከያዝኳቸው ነጥቦች ውስጥ «10 things Ethiopia do to sabotage freedom of expression» የሚል ይገኝበታል። ከሥሩ ስድስት ነጥቦች ተዘርዝረዋል። እንግዲህ 10 ያህል፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው መንግሥት ሐሳብን የመግለጽ ነጻነትን የሚያፍንባቸውን መንገዶች ለመዘርዘር ፈልጌ ከስድስት በላይ መሻገር አቅቶኝ ያቆምኩት ማስታወሻ መሆኑ ነው። የ«ማዕከላዊ» መርማሪዎች ግን ይህንንም እንደወንጀል ከክስ ፋይሌ ጋር አያይዘው እንደ ማስረጃ አቅርበውብኛል። የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ከመታሰሬ በፊት የጀመርኩትን እነዚህን ደባዎች ለመተንተን የመሞከር ሥራ መቀጠል ነው።

በ21ኛው ክፍለ ዘመን የፖለቲካ ሥልጣንን መቆጣጠር፣ ሰፊ የደኅንነት አውታር መዘርጋት እና ጠንካራ ሠራዊት መገንባት በብቸኝነት የበላይነትን ለመቆናጠጥ አያስችልም። በመሠረታዊ የአስተዳደር ፍልስፍናው ‹በአንድ ሜዳ ከአንድ ኃይል በላይ መኖር የለበትም› የሚል አቋም ያለው ኢሕአዴግ መራሹ መንግሥት፣ በዚህ እምነቱ ሳቢያ የሚያጠፋው ወይም የሚያዳክመው አማራጭ የፖለቲካ ኃይሎችን ብቻ ሳይሆን አማራጭ ሐሳብ የሚያመነጩ እንደ ብዙኃን መገናኛ እና ጠያቂ ማኅበረሰብ ለማፍራት የሚሠሩ ሲቪል ማኅበራትንም ጭምር ነው። ይህ ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊነትን ለማምጣት የሚደረገውን መፍጨርጨር ያዳፍነዋል። ይሁን እንጂ መንግሥቱ ይህንን ሲያደርግ በተለያዩ ሰበብ አስባቦች በመሆኑ፣ ደባውን የሚረዱት ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ዜጎች ብቻ ናቸው። ብዙኃን የምንፈልገውን ያህል አማራጭ ሐሳቦችን እንዲናገሩም፣ እንዲያዳምጡም ሁኔታዎች በደባ ይደናቀፉባቸዋል።

ወደ መቶ ሚሊየን እየተጠጋ ያለውን የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ አርባ ሚሊየን የማይሞላ ሕዝብ ካላት ኬንያ ጋር ማነጻፀር ብንጀምር እንኳ የምናገኘው ውጤት በጣም አሳዛኝ ነው። በየዕለቱ ብዙ ዐሥር ሺሕዎች የሚጠጋ ቅጂ የሚያሰራጩ ሁለት የግል ጋዜጦች አሏቸው፤ እኛ አንድም ዕለታዊ የግል ጋዜጣ የለንም። ከአምስት በላይ ፖለቲካ የማይፈሩ የግል ቴሌቪዥኖች አሏቸው፤ እኛ አንድም የለንም። 64 በመቶ ኬንያውያን የበይነመረብ (ኢንተርኔት) ተጠቃሚዎች ናቸው፤ ከበይነመረብ ጋር የተዋወቁ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ሶስት በመቶ አይሞላም። በዚህ ስሌት መሠረት ኢትዮጵያውያን አማራጭ የመረጃ ምንጭ ውሱንነት አለባቸው ማለት ነገሩን ማቃለል ይሆናል። ኢትዮጵያውያን አማራጭ የመረጃ መስጫ እና መቀበያ መንገድ የላቸውም። ይህንን ክፍተት እንዳይሞላ እንኳን ሲቪል ማኅበረሰቡ በሕግ ሥም አብሮት ተገድቧል።

በዓለማችን የሕትመት ብዙኃን መገናኛዎች ተፈላጊነት እየቀነሰ መጥቷል። ምክንያቱ ደግሞ የበይነመረብ እና ኤሌክትሮኒክ ብዙኃን መገናኛዎች መበራከት እንደሆነ ይገመታል። ኢትዮጵያ ውስጥ ግን አማራጭ የኤሌክትሮኒክ ሚዲያ በሌለበት እና የበይነመረብ ተዳራሽነቱም እጅግ ዝቅተኛ በሆነበት ሁኔታ፣ ‹ነጻ ፕሬስ ተፈቅዷል› በሚል ሁለት ዐሥርት ዓመታት እየተዘመረ ባለበት ሁኔታ የሕትመት ሚዲያው ከአጀማመሩ አንፃር ለምን ተዳከመ? ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው መንግሥት እነዚህን ደባዎች ይጠቀማል፡-

1. ፈቃድ መከልከል

የብሮድካስት ባለሥልጣን ለብዙኃን መገናኛዎች የሥራ ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን ያለው መሥሪያ ቤት ነው። መሥሪያ ቤቱን ፈቃድ ሊጠይቁ የሚሄዱ የመገናኛ ብዙኃን ሰዎች በመጀመሪያ ጀርባቸው ይጠናል። ሰዎቹ ገዢው ፓርቲ ለሚፈልገው የአንድ አመለካከት መርሕ የሚስማሙ ዓይነት ሰዎች ከሆኑ ፈቃዱን ወዲያው ያገኛሉ። አለበለዚያ ግን ፈቃድ ይከለከላሉ። ፈቃድ የሚከለከሉት በቀጥታ ትዕዛዝ አይደለም፤ በአብዛኛው በቢሮክራሲያዊ ማዘግየት፣ ማሰልቸት እና ገና በመቋቋም ላይ ያለውን ድርጅት በማክሰር (በተዘዋዋሪ ፈቃድ) መከልከል ነው።

2. የማተሚያ ቤቶች ቁጥጥር

በኢትዮጵያ የማተሚያ ቤት ሥራ፣ እንደንግድ ሥራ አዋጭ ሥራ ነው። ሆኖም የጋዜጣና መጽሔት ሕትመት መሥራት የሚችሉት ማተሚያ ቤቶች በጣም ጥቂት ናቸው። እነርሱም አደጋ ያለው ‹ቢዝነስ› መሥራት አይፈልጉም። ምክ'ንያቱም በቂ ሥራ አላቸው። ራሳቸውን ከሕግ በላይ ያደረጉት የደኅንነት ሰዎች፣ ሥራ ባያጡም ‹ለሕዝብ መረጃ መድረስ አለበት› በሚል እምነት ጋዜጣ ለማተም የሚስማሙትን ማተሚያ ቤቶች በተለያየ መንገድ ያስፈራሯቸዋል። ከማስፈራሪያዎቹ አንዱ ‹ታክስ› ነው፤ ማተሚያ ቤቶቹ ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው መንግሥት የማይወደዱትን የሕትመት ውጤቶች የሚያትሙ ከሆነ በታክስ ስም ከገበያ ይባረራሉ።

3. በሕግ ሥም ምኅዳሩን ማጥበብ

እንደ አርቲክል 19 ያሉ ለሐሳብ ተቆርቋሪ ዓለምአቀፍ ድርጅቶች ኢትዮጵያ በስም ብቻ ‹የፕሬስ እና መረጃ የማግኘት ነጻነት አዋጅ› ማውጣቷን፣ ይህንን ማድረግ ካልቻሉት የአፍሪካ አገራት አንፃር እያወዳደሩ ያወድሱላታል። እንደእውነቱ ግን የሕግ ማዕቀፉን ተከትሎ ማዕቀቦችም ተወልደዋል። አዋጁ በወጣበት ጊዜ የወንጀል ሕጉ ውስጥ የተጨመረው አንቀጽ በጋዜጣ ላይ የሚታተምን ‹ሥም ማጥፋት› ቦርቃቃ ያደርገዋል። ‹ጸሐፊው በእውነተኛ መረጃ ላይ ተመሥርቶም ቢሆን የጻፈበት መንፈስ ሌላውን ግለሰብ ለመጉዳት አስቦ ከሆነ› (ቅንነት ከጎደለው) በስም ማጥፋት ሊከሰስ እንደሚችል ይደነግጋል። እንግዲህ ቅንነትን ከእውነት በላይ በምን ማረጋገጥ እንደሚቻል ግልጽ አይደለም። ከዚህም በላይ የፀረ-ሽብርተኝነቱ አዋጅ ጸሐፊዎችን በቀላሉ ሽብርተኛ የሚያሰኙ አንቀጾችን ይዟል። ለምሳሌ፣ አገሪቱ ውስጥ ባለው መንግሥት ሽብርተኛ ብሎ ከሰየማቸው ድርጅቶች የተገኘ መረጃ ማተም ‹ሽብርተኝነትን ማበረታታት› ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። በዚህ መንገድ ዜጎች መረጃ እንዳያገኙም፣ እንዳያሰራጩም (ከሐሳብ እንዲገደቡ) ያስገድዳል።

4. ጋዜጠኞችን ማዋከብ

ጋዜጠኞች በሚሠሩት ሥራ ከሚዋከቡባቸው ጥቂት አገሮች ውስጥ ኢትዮጵያ ግምባር ቀደም ናት። እንደ ሲፒጄ ሪፖርት ኢትዮጵያ ጋዜጠኞችን በማሰር በአፍሪካ ሁለተኛ አገር ነች። የኢትዮጵያ የብዙኃን መገናኛ ነጻነት ሁኔታ በተለይ ምርጫ በቀረበ ቁጥር ሲያል ውስጥ ይገባል። በ2006 ዓ.ም መጨረሻ ላይ (ምርጫ 2007 ዓመት ገደማ ሲቀረው) ከ30 በላይ ጋዜጠኞች በውክቢያ ሰበብ አገር ጥለው ተሰድደዋል። አምስት መጽሔቶች እና አንድ ጋዜጣ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ታግደዋል። የዚህ ዓይነቱ ውክቢያ ዐደት ምርጫ በመጣ ቁጥር የሚደጋገም ነው። በምርጫ ዋዜማ ጋዜጠኞችን እና አሳታሚዎችን እረፍት በሚያሳጣ ሁኔታ የሚያዋክቡት የመንግሥት የደኅንነት ሠራተኞች፣ በምርጫ ማግስት ሥራቸውን እንደጨረሱ ሰዎች እረፍት ስለሚወስዱ የመገናኛ ብዙኃኑ ምኅዳር ትንሽ እፎይ ይላል። በአሁኑ ሰዓት እያየን ያለነው ይህንኑ ነው። ጋዜጠኞችን ማዋከብ ሙሉ ለሙሉ ባይቀርም በምርጫ ማግስት በጣም ይቀዛቀዛል።

5. ማገድ

አሁን በእስር ላይ የሚገኘው ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ተጋድሎ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው መንግሥት የፕሬስ ጠላትነት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ምሳሌ ነው። እርግጥ እስክንድር ነጋም ሰባት ያህል ጋዜጦችን ጀምሮ ተዘግቶበት፣ አሁን እሱም የ18 ዓመት ፍርዱን እየገፋ 4ኛው ዓመት ላይ ይገኛል። ተመስገን ደሳለኝ በ«ፍትሕ» ጋዜጣ ጀምሮ፣ በሕገ ወጥ መንገድም ቢሆን ሲታገድበት «አዲስ ታይምስ» መጽሔትን፣ ከዚያ «ልዕልና» ጋዜጣን፣ ከዚያ «ፋክት» መጽሔትን እያለ ለመታገል ሞክሯል። መንግሥትም ከስር ከስሩ እየተከታተለ በተገኘው ዕድል ሁሉ ጋዜጦቹን ሁሉ አግዷል። በመጨረሻ ሙሉ ለሙሉ ዝም ማሰኘት የቻለው ተመስገንን ወህኒ በመወርወር ነው።

መንግሥት የሚያግደው ጋዜጦችን ብቻ አይደለም፣ የበይነመረብ የዜና ድረ-አምባዎችንም ጭምር ነው። ሰሞኑን ፍሪደም ሐውስ ባወጣው ሪፖርት እንኳ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው መንግሥት ከ190 በላይ የበይነመረብ የዜና አውታሮችን እንደአገደ ገልጿል።

ወደ ገፅ 10 ዞሯል

በጃንሆይ መንገድ ...



**ኤፍሬም ስዩም
(ገጣሚና ባለቅኔ)**

በአንድ ወቅት የኢትዮጵያ ባል /በዓል/ ሆነው የነበሩት 'ጃን ሆይ' በሀገሪቱ ውስጥ የነበሩትን የቅኔ መምህራን ከሰሜንና ከደቡብ፣ ከምስራቅና ከምዕራብ፣ ከሊባ ከመስዕ፣ ከአዜብ ከናጌብ ወደ አሊቅ ከናጌብ ወደ አዲስ አበባ ቤተ መንግሥት ሠበሰቡ፡፡

ለቤተ መንግሥቱ የግብር አዳራሽ ተሰብስበው የነበሩት የቅኔ መምህራን «ንጉሡ ስለ ምን ጠሩን?» በሚል ሃሣብ ተጨንቀው ተጠበው ነበር የሰነበቱት፡፡ ንጉሡ ግን ሊቃውንቱን የሰበሰቡበት ዋና ምክንያት ይህ ነበር ...

«በሃገሪቷ ውስጥ የሚኖረው ሕዝብ ጠባዩ ይህን ይመስላል ለማለት አስቸጋሪ ነው፡፡» የሚለውን አይልም፤ የማይለውን ይላል፡፡ የሚመስለውን አይመስልም፤ የማይመስለውን ይመስላል፡፡ «እንዲህ ነኝ» ሲል «እንዲያ ነው»፣ «እንዲያ ነኝ»ም ሲል «እንዲህ ሆኖ» ይገኛል፡፡ የሆነውን አይደለም፣ ያልሆነውን እንጂ፡፡ «እንዲህ ዓይነቱ ሕዝብ ታድያ እንዴት ይገልፁታል? ያልተገለፀውንስ እንዴት ሊገዙት ይቻላል?» ...ይህ የጃንሆን ጥያቄና ሃሣብ ነበር - ያልተነገረ በልብ የታሰበ፡፡ አንድ ቀን ታድያ ጃንሆይ ከብላቴን ጋር ለእልፍኝ ሁለቱ ብቻ ሆነው እየተጫወቱ ሣለ፣ ጃንሆይ ጠየቁ ... ጉሮሯቸውን አሸተው፡፡

«እኔ ምልህ ብላቴን» አሉ ጃንሆን በተለመደው ንጉሣዊ አንደበት

«አቤት፣ ጃንሆይ» አሉ ብላቴን በንቁህ ሕሊና ወደ ንጉሡ አተኩረው፡፡ ጃንሆይም «ብላቴን ዛሬ ምጠይቅ/ ማጫውትህ ነገር ከመቸውም ጊዜ የላቀና ከመቸውም ጊዜ በላይ ደግሞ ለመንግሥታችን ፅንዓትና ለዕድሜውም ርዝመት ወሳኝ መሆኑ አይጠራጥርም፡፡ ዛሬ እኔ እና አንተ የምንነጋገረውን ወፍ እንኳ ሊሰማው አይገባም፡፡ በጆሮህ ከሰማኸው በኋላም በሰገነት የምትዋዛው አይደለም፡፡ ቁም ነገር ነውና፡፡»

ብላቴን ከተቀመጡበት ተነስተው እጅ ነሱ፡፡ ትዕዛዝ አክባሪነታቸውንም ያለ ቃል ገለፁ - እጅግ ጎንበስ ብለው፡፡ ...ጃን ሆይም ሚስጢረኛ ባለሟላቸው እንዲቀመጡ በምልክት ከገለፁ በኋላ ነገራቸውን እንዲህ ሲሉ ጀመሩ፡-

«ሕዝባችን የዋህ ይመስላል ግን ከባድ ነው፡፡ እንደሚታወቀው አንድ መንግሥት የጊዛውን ሕዝብ ጅምላ ማንነት ካልተዳ የግዛቱ ጊዜ አምብዛም ነው ይላሉ የእንግል ጣር ሰዎች እናም ያ የሃሣባቸው መንገድ የሚያስኬድ ይመስላል፡፡" ንጉሱ ለስጦታ ከወጣላቸው ረዥም እድሜ ከፈጀ ለወርቃማ ብር ፅዋቸው ከተቀዳ ኮኛክ ተጎንጭተው ሪዛቸውን እየመዘዙ ብላቴንና አስተዋሏቸው ጃን ሆይ እንዲህ ሲመለከቱ የማይፈራና በልቡ የማይደነግጥ ሹመኛ እምብዛም ነው፡፡ ምክንያቱም ንጉሱ እንዲህ አየነት አስተያየት የሚኖራቸው እጅግ አሣሣቢ ነገር በሚኖራቸው ጊዜ ነውና፡፡ ቀጠሉ ንጉሡ፡፡

" እንደሚታወቀው እዚህ እኛ ሐገር የሚኖረውን ሕዝባችን ልብ ብለሸው እንደሆን እንደየ ሀገሩ ሁኔታና እንደየሀገሩ የአየር ጠባይ ዓመሉ ለየቅል ነው፡፡ ምንም እንኳ እንዴት ሐገርና አንድ ሕዝብ ብሎ መንግስታችን ቢያምንም ሕዝቡ ግን እንደ ተወለደበት ስፍራ የራሱ የሆነ ጠባይ አለው፡፡ ለምሳሌ ትግሬው ከጎንደሬው፣ ጎጃሜው ከወሎው፣ ሰሜኑ ከደቡብ፣ ምስራቁ ከምዕራብ ደጋው ከቆለኛ ሌላውም እንዲሁ ሁሉም እንዳመሉ የየራሱ ጠባይ አለው፡፡ ይኸውም እያንዳንዱ ብሔርም ለየራሱ የሆነ የጉያ ዓመል እንዳለው ሁሉ እያንዳንዱ ብሔርም ለየግሉ በጅምላ አንድ የሚያደርገው ጠባይ አለው፡፡ ጎጃሜው በጎጃሜነተ፣ ትግሬው በትግሬነቱ፣ ጎንደሬው ወለየው፣ ቆለኛው ደገኛው ኦሮሞው ጉራጌው ሁሉም በየብሔሩ የሚያመሳስለው መጥፎም ሆነ ደግ ጠባይ ይይዛል፡፡ ባገር ልጅነቱ ሁሉም እየራሱን ይሆናል፡፡ " ጃንሆይ ንግግራቸውን ጋብ አድርገው ብላቴኑን አስተዋሉ ብላቴን አግራሞትና ምን ሊመጣ ይሆን በሚል የጥያቄ ምልክት ውስጥ ናቸው፡፡ ለልባቸውም የመንግስትን እድሜ ለማርዘም የሕዝብን ማንነት ማወቅ ምን ይሉት ፍልስፍና ይሆን? እያሉ፡፡

ይህጥያቄቀርቦየነበረውንጉሡቢነግሡለ80ኛው ዓመት ሁዳዴ ላለፈ ለስለንቱ በእለቱ እሁድ ነበር ይላል፡፡ የመዋእለ ዘመን ታሪክ ፀሐፊ የነበረው ኤስድሮስ ሣልሣዊ፡፡

ንጉሡ ወደ ወጋቸው ማብቂየ ላይ ለብላቴን አንድ ጥያቄ አቀረቡ፡፡ በዚህ መልኩ እንዲህ አንተም እንደምታውቀው አፍርንጆቹም እንደሚሉት አንድ ግለሰቡ ለቤተሰብ መለክ ወዲያ ደግሞ ቤተሰቡ በመንደር መንደሩ በጎሣ ጎሣው በብሔር ብሔሩ ለሃገር ደረጃ የየራሱን የግልና የጅምላ ማንነት እየያዘ ተመጣና መጨረሻ ላይ የተለያየው ብሔርና ክልል ደግሞ አንድ ሐገር ይሆናል፡፡ ልክ ፈረንሳይ እንግሊዝ አሜሪካ እንደሚባለው እንግዲህ ልክ እንደዚሁ እኛም ብዙ ማንነት ያለን አንድ ኢትዮጵያውያን ሆነናል፡፡ ነንም እንሆናለንም፡፡ ያውም መልከ መልካም ጠይም፡፡

እንግዲህ ጥያቄዬ እዚህ ላይ ነው " ኢትዮጵያዊ ለሞላው/በጅምላው/ ከላይ ከላይ ሣይሆን ውስጣዊ በሙሉ ማንነቱ ጠባዩ ምን አይነት ነው? እንዴትስ ነው ተብሎ መደምደም ይቻላል? አሉ ጃንሆን ጠቅሰው

ብላቴን ተገረሙ ተደነቁ ንጉሱን በልባቸው አከበራቸው፡፡ እውነትም የኢትዮጵያ ላለ አሉ፡፡ እንደህ ያለ ብልህ ንጉስ ጠላቱ ሊሆን የሚችለው ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ከዚያ በተረፈ ግን ሊረታው የሚችል የለም፡፡ የሕዝቡን የልብ መንገድ የሚያውቅ እንዴት መሄድ እንዳለበት ያውቃልና፡፡ ይህንን በልባቸው እያሰቡ በአንደበታቸው እንደዚህ መለሱ፡፡

እውነት ነው ጀን-ሆይ ራሴ ፈረንጆቹ አበክረው የሚጠሩት ፈላስፋ፣ አዋቂ/ ሰው አላቸው " ሶቅራጦስ" ሚሉት እናመ አንድ ቀን በቤት ራት ከሚያደርጉ ፈረንዶች ጋር ሆኜ በሆነ አጋጣሚ ስሙ ተነሳና ጠየቅኳቸው፡፡" ለመሆኑ ሶቅራጠስ፡ አግናችሁ እንድታዩ ምክንያት የሆናችሁ ነገር ምንድን ነው? ሲል ከእነርሱ አንዱ ብላቴን ለአውሮፖ ብዙ ታላላቅ ሰዎች ተነስተው ነበር፡፡ ይነሣሉም ከተነሡት አብዛኞቹ ሚመራመሩ የኖሩት ወደ ዋቅ ነበር፡፡ዙሪያችንን ወደ ከበበው ነገር ከቅንጣት እስከ ኘላኔት ብዙዎች ተመራምረዋል፡፡ ደከመወልም፡፡ ነገር ገን ሶቅራጥስ እንደ ብዙዎቹ ሁሉ ምርምሩን ዙሪያው ወደ ከበበው ነገር አላደረገም፡፡ ወደ ማሰው ነው የገባው ሶቅራጥስ ሰው መንድን ነው ማለት ጀመረ፡፡ መርዝ እስከመጎንጨት ደረሰ፡፡

ጃንሆይ እርስዎም ዛሬ ያመጡት ጥያቄ የታላቁን ፈላስፋ ዓይነት ነው፡፡ መቸም የሕዝባችንን ጥቅል ፀባይ ለማወቅ ሁሉን ስንመራመር አንከርምም የሕዝባችንን ጠባይ ለማወቅ የሕዝቡ ጥበብ መገለጫ የሆኑትን ሪሶቹን መሰብሰብ ነው፡፡ ፈረንዶች አርቲስቶች ይሏቸዋለ፡፡ በሐገራችንም እኮ እረኛ መን አለ ተብሎ ልክ እንደእርስዎ ነገስታት ይጠይቁ ነበር፡፡ አዝማሪና እረኛ ምን አሉ እያሉ፡፡ ስለዚህ ጀን-ሆይ የሕዝባተንን ጠባይ ለማወቅ የሕዝቡ ሃሣብ መገለጫ የሆኑትን ታላላቁን ባለ ቅኔያት እንሰብስብ የማል መከንየት ነበር የተሰበሰቡት ሉቃውንቱ

የምሁራት ፀጥታ የንጉስን ቡረፍያ ይመስላለ፡፡ ጃን-ሆይ ፀጥታውን ንዴት፡፡ ካላቸውን ከግራ ወደ ቀኝ አጣፍተው እንዲህ ሲሉ ተናገሩ ሊቃውንት ሆይ እናንተ የሕዝብ አይኖች ናችሁ ፈጣሪ ጠብቆን እንጆ በዚች እለት የሚያጉረመርሙ ጠላቶቻችን እዚህ ምርፍቅ ውስጥ አንዳች በደል ሊፈልሙ የሀገር ዓይን ጠፋ ማለት ነው፡፡ እናንተ ዓይኖች ናችሁ ህዝብን አየታችሁ የመትተረጉሙ እና የመትተነትኑ ዛሬ እኔ ለእናንተ ለዓይናማዎቹ አንዴት ቀላል ጥያቄ አነሳለሁ ያን ጥያቄም ለሚመልስልኝ ሊቅ ለመንግስቴ እንዲህ የሆንለታል፡፡

" ካባ ላንቃ ያለብሣል ለቀኜ የቀመጣለ እኔ ከምበላው ይበላል ከምጠጣውመ ጠጅ ይጠጣል ለመንግስቴ ከወና አማካሪዎቹ አንደ አንዱ ይሆናለ በሉ ልብ ብላችሁ አድምጡኝ አሉና ጥያቄወን ሰነዘሩ ሁለት መስመር የአማርኛ ጉባኤ ቃየ ነበረች ጥያቄዋ.....

ልጅ እያለ ጥቁር ሲያረጅ የሚቀላ

ይህን የሚመስል

በቀኜ ተቀምጦ እኔ ጋር ይጠጣ ከኔ ገራ ይብላ ብለው ዘፋናቸው ላይ ተቀመጡ

ሊቃውንቱ ጥያቄዋን ለመመለስ አወጡ አወረድ ቅንድቦቻቸውን ከፈ ዝቅ አደረጉ የጥያቄውን ትርጉም ፈልጋም አብዝተው ደከሙ፡፡ በየልቦናቸውም ዋጅ እያለ ጥቁር ሲየረጅ የሚቀላ መንድነው አሉ፡፡

ከመሃለ አንድ ሊቅ እመረ ብለው ተነሱ፡፡ መልሱን እንዳገኙትም ፊታቸው ላይ ያለው የግርምት-ፈገንታ ያሣብቅባቸው ነበር፡፡ ፡ ጃን-ሆይ አሉ አዳፋ ለባሹ የቅኔ መምህር፡፡ ጃንሆይ ትኩረታቸውን ወደ ሊቁ መለሡ፡፡

በመዝጊየ ስምና፤ በገበሬ ከብት ይፍቀድልኝ እና ልግባ ልጫወት በማለት ቅኔውን በቅኔ መለሰው ሊቁ ተቀመጡ፡፡ የንጉሱ ፊት አብዝቶ ፈገገ በአዳራሹ የነበሩት መምናራንም ነገሩ ገብቷቸው እጆቻቸውን አነሱ፡፡ እንደዚየን እለት ያለ ጭብጨባ እስከዛሬ ድረስ ተሰምቶ አያውቅም፡፡

ከዚያ በኋላ መልሱን ለመለሱት ባለ ቅኔ ሁሉን ነገር እንደ ንጉሱ ቃል ሆነላቸው፡፡ ንጉሱም መልካም አማካሪ ከጐናቸው በመኖሩ የግዛታቸው ዘመን ከ5 አስርታት ያለፈ ነበር፡፡

ጀን ሆይ የሕዝባቸውን ልቡና የተረድት በሊቁ አመላለስ ነበር፡፡ መልሱ ቀይ አልነበረም፤ ጥቁርም አለነበረ፡፡ ጠይም ነበር፡፡..... መላሹ መልሰን በቀጥታ አልተናገሩም፡፡ የሕዝባቸው ውጤት ነበሩና.....በዘወርዋራው ነበር የተናገሩት፡፡ ሊቁ ሊሉ የሚፈልጉትን ለማለት ነበር የመለሱት፡፡ ንጉሱም ባለ ማለት ውስጥ የነበረው ማለት ገብቷቸው ነበር..... እውነት እላችኋለው ይላሉ የጃንሆይ መዋዕለ- ዘመን ሕጋዊ የነበሩት ኤስ ድረስ ሳልሳዊ፡፡

" እውነት እላችኋለው ጥያቄውን በቀጥታ የሚመልስ ቢኖር በንጉሱ የተገባው ቃለ ይታጠፍ ነበር፡፡ .... ምክንያቱም እሱ የዚያ ሕዝብ ውጤት አይደለም እና፡፡" ሌላው ይላሉ ኤስድሮስ ሳልሳዊ " ልጅ እያለ ጥቁር " ለሱ ይህ ይዝብ ነው ይላሉ ኤስድሮስ የራሳቸውን የሕይወት ታሪክ በጻፉበት " የዘጋቢው መዝገብ " መጽሐፍ ላይ አዎን አበሻ ልጅ እያለ እንዲመቸው እድል ከእርሱ ጋር የለችም፡፡ ጠይም ሕዝብ ሕይወትን ማለት ልጅነት ወይም መልካም ወጣትነትን መኖር የሚጀምረው በስተእርጅናው ነው፡፡ ይህን ያስተዋልኩት ጀንሆይ ያስተማሩዋቸው ወጣቶች ከአመፁ በኋላ የደረሰባቸውን ልብ ስል ነው በማለት ልጅ እያለ ጥቁር ሲያረጅ የሚቀላ ይህ ጥያቄ አሁን ፖርላማ ለሚገኙት አባላት ቢቀርብ አንድ እጁን አውጥቶ በመልስ እድሉ ምን ይሆን ነበር?፡፡ ሀ. እስራት 2. ስደት ሐ. ሹመት ይኸው እዚህ ጥግ ላይ አንድ የተቃዋሚ ፖርቲ አባል እጁን አንስቶ በርበሬ ብሎ ተናገረ፡፡ እኔ ግን እንደዚህ አይነቱን እንደዚህ ይመስላል ለማለት ይከብደኛል፡፡

የውብሸት ስቃይ እና የመቻቻል ናፍቆት

‹‹እኔም ሳድግ እንደ አባቴ እስር ቤት እገባ ይሆን?››

አቤል ዓለማየሁ

ጭቆና በተንሰራፋበት ዘመን ላይ ለመወለዱ ስሙ ዝንተ ዓለም ምስክር ሆኖ ይቀመጣል። እድለኛ ሕጻን አይደለም። እንደ ዕድሜ እኩዮቹ የአባት ፍቅር ምንነትን በቅርብ ሆኖ ማጣጣም አልቻለም። እንደ አቶ ኃይለ ማሪያም ደሳለኝ ልጆች በቤተ መንግሥት የመቀማጠልን፣ እንደ ብዙ የባለሥልጣን ልጆች ባህር ማዶ ተልኮ ትምህርት የመከታተልን፣ እንደ ጥቂት 'የጊዜው' ባለሃብት ልጆች በምቾት መንደላቀቅ ቢቀርበት እንኳን እንደ ብዙ መደበኛ ሕጻናት በአባቱ ትምህርት ቤት የመድረስ እና የመመለስን ወግ እንኳን ለማየት አልቻለም።

አባቱ በቤቱ ሆኖ ከተንከባከበው ጊዜ ይበልጥ እርሱ በየእስር ቤቱ እየተንከራተተ አባቱን የጠየቀበት ዓመት ከዕድሜው ላይ አብላጫውን ጊዜ ይዟል። በሳምንቱ መጨረሻ የዕድሜ ዕኩዮቹ ወደ መጫወቻ ስፍራ ሲላኩ እሱ ግን ከተከለለው አጥር ወዲያ አባቱን ለመጎብኘት ከእናቱ ጋር ረዥሙን ጉዞ ይጀምራል። ተስፋው በድንግዝግዝ የተሞላ ነው። ጓደኞቹ ዶክተር፣ ፓይለት፣ የጠፈር ሳይንቲስት' መሆን ምኞታቸው እንደሆነ በጉልድፍ አማርኛቸው ሲገልጹ እሱ ‹‹መጽደቁ ቀርቶብኝ በቅጡ በኮነነኝ›› ያለ ይመስላል። የሚሆነውን ከማለም ይልቅ ‹‹እኔም ሳድግ እንደ አባቴ እስር ቤት እገባ ይሆን?›› በሚል ስጋት ጭንቅላቱ ተወጥሯል። ይህ ሕጻን ዝዋይ እስር ቤት ተወርውሮ የሚገኘው የጠንካራው ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ ልጅ - ፍትሕ ውብሸት ነው።

በአገራችን ያለው የፖለቲካ አስተዳደር እጅግ ሀብታም እና እጅግ ድሃ የሆኑ ዜጎች እንዲፈጠሩ ምክንያት እንደሆነው ሁሉ አሳሪ እና ታሳሪ የሚሉ ሁለት ተቃራኒ ጫፎችንም ፈጥሯል። ከብዙሐን ጋር ሊያገናኙ በሚችሉ በማንኛውም 'ሚዲየሞች' መንግሥትን አጥብቀው የሚተቹ ሀሳቦችን በቁርጠኝነት ያራመዱ ትጉሐን የመጨረሻ ማረፊያቸው እስር ቤቶች መሆናቸው ከታወቀ ሰነባብቷል። ባለ ጊዜዎች ‹‹አገሬን›› የሚሉን ለማሰር ለሰከንድ ዳናቸውን ከመከታተል አይቦዝኑም። አስረውም አይረኩም። ለዚህ ደግሞ ውብሸት ታዬ እና በርካቶች ላይ እየደረሰ ያለው የመብት ጥሰትን ለማስረጃነት ማቅረብ ይቻላል።

የውብሸት ጥያቄ ምላሽ ያግኝ!

ከሰኔ 12/2003 ዓ.ም. አንስቶ ከአራት ዓመት ከሩብ በላይ በእስር ቤት የሚገኘው ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ ከፍተኛ ስቃይዎች ደርሰውበታል። በቤተሰቡ በቅርበት መጠየቅ እንዳይችል ከአዲስ አበባ 160 ኪሎ ሜትር አርቀው ዝዋይ እስር ቤት ቆልፈውበታል። እዚያ ደርሰው ወደ እስር ቤቱ የውስጥ መንገድ ለመዝለቅ ጋሪ መጠቀም የግድ ይላል። የዓይን ጠንቅ የሆነው ከፍተኛ አቧራ ጉብኝዎችን ያሰቃያል። [ፍትሕ እና እናቱ ብርሐኔ ተስፋዬ ይህን አቧራ በየሳምንቱ 'ይምጉታል'] ይሄው አቧራ ወደ እስረኞቹ ግቢዎች ስለሚዘልቅም የታሳሪዎች የዘወትር የስቃይ ምክንያት ነው።

በተጨማሪም የቆርቆሮ ቤቶቹ ሙቀት እና የሚጠጡት ውሃ ንጽህና መጓደል ውብሸት አሁንም ድረስ ለሚያመው የኩላሊት ኢንፌክሽን ሕመም ምክንያት እንደሆነው የጋዜጠኛ መብት ተከራካሪው ሲ.ፒ.ጄ.ን ጨምሮ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ላይ ተገልጿል። ውቤ ለሕክምና ወደ አዲስ አበባ ቢመጣም የተሳካ የጤና እርዳታ ሳያገኝ (መድኃኒት እንኳን ሳይታዘዝለት) ወደ ዝዋይ እንዲመለስ ተደርጓል። ህመሙ እስከአሁንም አብሮት በመሆኑ በየቀኑ ሰላማዊ እንቅልፍ ማግኘት አዳግቶታል።

ዝዋይ ድረስ ወስደው አስረውት እንኳን ከቤተሰቡ ውጪ በሌሎች ሰዎች እንዳይጠየቅ ተከልክሏል። የዚህ ጽሑፍ አቅራቢን ጨምሮ ሌሎች ወዳጆቹ ያንን ሁሉ ኪሎ ሜትር አቋርጠን ተጉዘን ሳንጠይቀው ተመልሰን እናውቃለን።

የ'Human Rights Watch' የመናገር ነጻነት ሽልማት (ሄልማን ሃሜት) እና ለአፍሪካ ዕድገት ጉልህ ሚና ለሚጫወቱ ስመጥር ጋዜጠኞች የሚሰጠውን የ'CNN African Award' አሸናፊ የሆነው ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ ከደረሰበት ግፍ የከፋው ለሱ ተከልክሎ ለሌሎች የተሰጠው የ'ይቅርታ' ፍቺ ነው። ፍትሕ ሚኒስቴር እንደ እርሱ በ'ሽብር' የተከሰሱትን ስዊድናዊያን ጋዜጠኞች ማርቲን ሽብዬ እና ዮሃን ፐርሰን ይቅርታ ተቀብሎ ከፈታቸው የሰነበተ ሲሆን ውብሸት ግን እስከዛሬ ድረስ በእስር እየማቀቀ ይገኛል።

‹‹በሽምግልና ጉዳዩን እንጨርሳለን›› ባሉ ሰዎች ከፍተኛ ገፋፊነት ይግባኝ ከመጠየቅ ይልቅ ይቅርታን ያስቀደመው ውብሸት ጉዳይ እስከ ዛሬ ድረስ እልባት አልማግኘቱ በቤተሰቡ፣ በወዳጆቹና በአድናቂዎቹ ዘንድ ቁጭትን ፈጥሯል። ተመሳሳይ ክስ የቀረበባት ብርቱዋ ጋዜጠኛ ርዕዮት ዓለሙ [ይግባኝ መጠየቋ እና ከአራት ዓመት በላይ ታስራ መለቀቋ ይታወሳል] በእስር በተፈታችበት ሰሞን እነውብሸት ሊፈቱ እንደሚችሉ ወሬዎች ተናፍሰው የነበረ ቢሆንም እስካሁን ይህ ተፈጻሚ ባለመሆኑ የውብሸት የስቃይ ሕይወት ቀጥሏል።

> ካልተቻቻልን፣ ካልተደማመጥንና ካልተባበርን 'እንደ አገር' ልንበለፅግ አንችልም። ባልተጻፈ ሕግ አሳሪና ታሳሪ የሚሉ ጎራዎች እየገመድን የጋራ አገራዊ አጀንዳዎች ሊኖሩን አይችሉም።

እስረኞቹ ይፈቱ! መቻቻልም ይምጣ!

የተቃውሞ ድምፆችን በማፈን ጊዜያዊ የሥልጣን መደላድል ማግኘት ይቻል ይሆናል እንጂ አስተማማኝ እና ዘላቂ ሰላምን መገንባት አይቻልም። እያሰሩ፣ እየጨቆኑና አማራጭ ድምጾችን እየጠረቀሙ ‹‹እንገነባዋለን›› የሚሉትን ዴሞክራሲ ስንዘር ያህል ማስጓዝ እንደምን ይቻላል? ዴሞክራሲ ለጥቂቶች ብቻ ምቹ ከባቢን ፈጥሮ ብዙኃኑን ጠርንፎ መግዛት አይደለም። ብሔራዊ ምርጫ በመጣ ቁጥር ፕሬስ እያፈኑ፣ ጋዜጠኞችን እያሳደዱና እያሰሩ ስለ ዴሞክራሲ መለፈፍ የአምባገነኖች ነጭ ውሸት ነው።

ያለ መናገር ነጻነት፣ ያለ ነጻ ፕሬስ፣ ያለ ገለልተኛ የፍትህ አካላት፣ ያለ ነጻ እና ፍትሐዊ ምርጫ ዴሞክራሲ አይገነባም። ዜጎች በጉዳዮቻቸው ላይ ውሳኔ አሳላፊ እና በያገባኛል ባይነት ተሳታፊ እስካልሆኑ ድረስ ድርቅና ርሀብን መመከትና አገርን መገንባት አስቸጋሪ ነው። ዜጎች የአገራቸውን ሀብት ያለ አድልዎ ተካፋይ ቢሆኑ፣ በነጻነት ውሳኔ አሳላፊ እንዲሆኑ ቢመቻች የኢትዮጵያ መለያ ያህል ተደርጎ ማጣቀሻ የተደረገብን ረሀብ ደጋግሞ ባልጎበኘን ነበር። ነጻነት እና አንድነት ካለ ረሃብን ማጥፋት ተሻግረነው ርብርባችን አገርን ስለ መገንባት ይሆናል።

ያለ ሁሉም ዜጎች ተሳትፎ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ግቡን ሊመታ አይችልም። ይህን መሰል የብዙኃን ርብርብ የሚፈልጉ ዕቅዶች ተፈጻሚ እንዲሆኑ በጋራ መረባረብ ከተፈለገ ደግሞ ሊቀድሙ የሚገባቸው የብዙኃኑ ጥያቄዎች ሊመለሱ ይገባል። ሀሳብን በነጻነት የመግለፅ መብት በተግባር ሳይሰፍን እና መቻቻል ሳይመጣ እውነተኛ ዕድገት ሊመጣ አይችልም። ‹‹ሁለት ዲጂት የኢኮኖሚ ዕድገት አስመዝግበናል›› ተብሎ እየተለፈፈ የአንድ ዝናብ አልባ ሲዝን ድርቅን መመከት ካልቻልን ዕድገቱ ጤነኛ አይደለም ወይም ዕድገቱ ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ የተደገሰ ነው ማለት ነው።

ካልተቻቻልን፣ ካልተደማመጥንና ካልተባበርን 'እንደ አገር' ልንበለፅግ አንችልም። ባልተጻፈ ሕግ አሳሪና ታሳሪ የሚሉ ጎራዎች እየገመድን የጋራ አገራዊ አጀንዳዎች ሊኖሩን አይችሉም። [መንግሥት መልካም አስተዳደር ካሰፈንኩ እጠፋለሁ የሚል ስጋት ካልኖረው በስተቀር]

መልካም አስተዳደር የሚሰፍነው ነባሩን ካድሬ በአዲስ፣ አንዱን ሙሰኛ በእጩ ሙሰኛ፣ አንዱን የወረዳ አመራር አባል በሌላ ስም በመቀየር ሳይሆን መደማመጥ ሲቻል ነው። ከተደማመጥን ደግሞ ሊሰሙ የሚገባቸው የታፈኑ ድምጾች መገኛ እስር ቤቶች ናቸውና በግፍ ተይዘው የታሰሩ ዜጎቻችን ሁሉ ይፈቱ። የእነ ውብሸት ይቅርታ ተቀባይነት ያግኝና ከእስር ይለቀቁ። ተመስገን ደሳለኝ ተፈትቶ በቤቱ ሆኖ ሕክምና ያግኝ። ፍርድ ቤት በነጻ ያሰናበታቸው እነህብታሙ አያሌው ይፈቱ። እነ እስክንድር፣ አንዱዓለም፣ ናትናኤል፣ አብርሃ ደስታ፣ የሺዋስና ሌሎችም ከነሙሉ የመናገር መብታቸው ነጻነታቸው ይታወጅ። ካልተቻቻልን፣ ካልተደማመጥን፣ ይቅር ካልተባባልን ከፍ አንልም። መንግሥት ሥልጣኑን ዜጎችን ለማፈኛነት መጠቀም እስካላቆመ ድረስ እንደ ፍትህ ውብሸት ‹‹እኔም ሳድግ እንደ አባቴ እስር ቤት እገባ ይሆን?›› (የውብሸት ባለቤት ለሲ.ፒ.ጄ. እንደተናገረችው) እያሉ በሰቀቀን የሚያድጉ ህጻናት እንባ ይፋረዳል!!!

ያልተገረዙ የመሪዎቻችን አንደበቶች

በቃሉ አጥናፉ ታዬ ዶ/ር

'የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው' (ምሳሌ 1:7) ተብሎ እንደተፃፈ እግዚአብሔርን የሚፈሩ በጥበብ የተሞሉ መሪዎቻችን ለዓለም የሚያስደንቅ ትሩፋቶችን እንድንወርስ አድርገውናል። እግዚአብሔርን የማይፈሩት የአሁን መሪዎቻችን ትተውልን ከሚያልፉት እዳዎች (መለያየትን፣ ስደትን፣ መፈናቀልን፣ የጎሳ ቅራኔንና ግጭትን፣ እስርን፣ ሞትን) በተጨማሪ አስጸያፊ ንግግራቸው እግዚአብሔርንም ሰውንም የማያከብሩ እና ለቦታው የማይመጥኑ እንደሆኑ እያረጋገጡልን ነው።

መሪ በአመራር ብቃቱ ተፅዕኖ አሳድሮ የሚመራውን ህዝብ ደጀን አድርጎ በአገር ላይ አዎንታዊ እና አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደር ይችላል። አንድ መሪ ብርቱ ይሁን ደካማ፣ ብልህ ይሁን ቂላቂል፣ ኩሩ ይሁን ወራዳ፣ ሥልጡን ይሁን ኃላቀር፣ ውሸታም ይሁን ሃቀኛ፣ ታማኝ ይሁን ከዳተኛ ህዝቡን ለመጥፎም ይሁን ለመልካም ሥራ የማነሳሳት አቅም አለው።

ለዚህም ነው ብልህ፣ ብርቱ፣ ሥልጡን፣ ሃቀኛ እና ታማኝ የነበሩ እነ ኢዛና፣ ላሊበላ፣እና ፋሲል ለዓለም ህዝብ ዕጹብ ድንቅ የሆኑ አሻራቸውን ትተው ያለፉት። ሥልጣኔ በዓለም መድረክ እንደ ሜንጦ የተሰቀለ ተስፋ በሆኑባቸው ዘመናት እነዚያ ጥበብን የተሞሉ መሪዎች (ኢዛና፣ላሊበላ፣ ፋሲል) የህዝቡን ስሜት እያባበሉ የተለያዩ ክህሎት እና ችሎታ ያላቸውን ሰዎች ጥልቅ የሆነውን ኪነ ጥበባዊ ዕውቀታቸውን እንዲጠቀሙበት በማድረግ እነሆ ለዓለም የሚያስደንቅ ትሩፋቶችን እንድንወርስ አድርገውናል። ጥበብን ከእነ ኢዛና፣ ላሊበላና ፋሲል፣ ስለ ሀገር ፍቅር እና አንድነት ከእነ ቴዎድሮስ፣ ዮሐንስና ሚኒሊክ ተምረን ያንን ታሪክ እና ስራ ማስቀጠል ሲገባን ይህንን ሊያስተባብር የሚችል መሪ ከሰማኒያ ዓመት ወዲህ በማጣታችን ያገናና የኢትዮጵያ ሥም መዘባበቻ ከሆነ ውሎ አደረ። በዚህም ሳያበቃ ህዝቧ ለድህነት፣ ለስደት፣ ለመከራ፣ ለሞት፣ ለእስር ቤት መዳረጉ የዕለት ከዕለት ተግባር እየሆነ መጥቷል።

> የኢህአዴግ መሪዎች የፍቅር ድባብን ፈጥረው የህዘቡን ዕውቀት እና ክህሎት ከመጠቀም ይልቅ ቅራኔዎችን እየፈጠሩ እና እያባባሱ ህዝቡን ባረጀ ባፈጀ የፖለቲካ ስልት ለመሸንገል ይሞክራሉ። ሥርዓቱ ከሚፈጽመው የከፋ ድርጊቶች (መፈናቀል፣ መሰደዱ፣ የጐሳ ግጭት፣ ሙስና፣ የመልካም አስተዳደር ዕጦት፣ የኑሮ ውድነት) ባሻገር የኢህአዴግ ሹማምንቶች ንግግር የምንጸየፈው እየሆነ መጥቷል።

የኢህአዴግ መሪዎች የፍቅር ድባብን ፈጥረው የህዝቡን ዕውቀት እና ክህሎት ከመጠቀም ይልቅ ቅራኔዎችን እየፈጠሩ እና እያባባሱ ህዝቡን ባረጀ ባፈጀ የፖለቲካ ስልት ለመሸንገል ይሞክራሉ። ሥርዓቱ ከሚፈጽመው የከፋ ድርጊቶች (መፈናቀሉ፣ መሰደዱ፣ የጐሳ ግጭት፣ ሙስና፣ የመልካም አስተዳደር ዕጦት፣ የኑሮ ውድነት) ባሻገር የኢህአዴግ ሹማምንቶች ንግግር የምንጸየፈው እየሆነ መጥቷል።

በገዥው ፓርቲ ጎራ የተሰለፉ አመራሮች ከአጸያፊ ቃላት የጠበቀ ወዳጅነት ፈጥረው ከህዝብ ጋር የአጭር ጊዜ የቴሌቪዥን ዕይታ እንኳን የዕብሪት ወኔያቸውን፣ ነገር ያረገዘ አዕምሯቸውን፣ መርዝ የሚተፋ ምላሳቸውን፣ ስድብ ያጨቀ እስትንፋሳቸውንና የሰው ልጅ ማንነትን የሚጫን ንግግራቸው የየዕለቱ ትዕይንት እየሆነ መጥቷል፡፡ የገዥው ፓርቲ አባላትን ከሚያዋስናቸው ባህሪያት መካከል ስድብ፣ በህዝብ ላይ መሳለቅ፣ ዘመን የማይሻገር ሃይላቸውን ለማሳየት መሞከር ሲሆን፤ ይህ ባህሪያቸው አላዋቂነታቸውን፣ የአመራር ብቃት ማነስን፣ለህዝብ የማይመጡ መሆኑን ከማረጋገጡ ባሻገር ለገዥው ፓርቲ በህዝብ ላይ የሚኖረውን ቅቡሉነት ዕለት ዕለት እየሸረሸረው መጥቷል፡፡

የገዥው ፓርቲ አባላት በሚናገሩት ንግግር፣ በሚያፈልቁት የስድብ ቃላት የተሽማቀቅንባቸውና ያፈርንባቸው ጊዜያቶች በጣት የሚቆጠሩ አይደሉም፡፡ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር፣ በፓርላማ ባደረጓቸው ንግግሮች አብዛኞዎቹ በስድብና በንቀት የተሞሉ ነበሩ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትርነት መለኮታዊ ሥልጣን ያቀዳጃቸው ይመስል፤ ከእሳቸው የተለየ ሃሳብ ያነገበን ሰው በስድብና በንቀት ይሳለቁበታል፡፡ ከበፊቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ራዕይ ዘብ የቆሙና የአሁን ጠቅላይ ሚኒስትርም በንግግራቸው መለስን ከመሰሉ ሰነባብተዋል፡፡ የስድብ ትሩፋቶችንም እንዲያሳኩ አደራ የተሰጣቸው ይመስላል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ የታችኞቹም ሹማምንት ሆኑ ደጋፊዎች ከማን አንሼ በማለት የመከባበር እና የውይይት ዳራ እያጣፉት መጥተዋል፡፡

አንጋፋው ምሑር ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም፣ በአባይ ጉዳይ ላይ ለሀገር የሚጠቅም ዕይታቸውን ባሰፈሩ ማግስት የመንግሥት የመገናኛ ብዙሃን እና ጥቂት የኢህአዴግ ደጋፊዎች በፕሮፌሰሩ ላይ የሰነዘሩት ትችት እጅግ በጣም አሳፋሪ ከመሆኑም በላይ ያለንበትን የፖለቲካ ሥርዓት አስከፊነት ያጐላዋል፡፡ በታዋቂው ጋዜጠኛ በሲሳይ አጌና ላይ፣ አንድ የኢህአዴግ ደጋፊ በሰኔ ወር 2005 ዓ.ም በተላለፈው የአድማጮች አስተያየት ላይ የሰነዘረው ትችትና ስድብየፖለቲካሥርዓቱእናየሥርዓቱደጋፊዎችስለራሳቸው የገነቡት ዕይታ የገዘፈ እንደሆነና ከነባራዊ ሁኔታው ውጭ እንደሆነ ለመረዳት ያስችላል፡፡ በዚሁ አጋጣሚ ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና ላሳየው ጨዋነት እና ለተላበሰው የነጻ ሚዲያ ጋዜጠኝነት ባህሪ ላደንቀው እወዳለሁ፡፡

በማንኛውም ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሥነ-ልቦናዊ ጉዳዮች ላይ ሰዎች በሀሳብ አንድ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ በአንድ ጉዳይ ላይ ሰዎች የተለያየ አመለካከት መያዛቸው ሰውኛ ነው፡፡ በማንኛውም ጉዳይ ላይ የተለመደውን የአሰራር ሂደት 'ለምን' ብሎ መጠየቅ የሰው ትክክለኛ ባህርይ ነው፡፡ ይህ ግን በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት አለመታየቱ የፖለቲካው የውይይት ባህል ገና እንጭጭ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በማኅበረሰቡ ውስጥ የሰፈነውን ውጥረት፣ ሒሳዊ ፖለቲከኛ ወይም ግለሰብ ሂሱን በጨዋነት ሲገልፅ የተሰነዘረውን ሃሳብ መዝኖ ከመጠቀም ይልቅ የተሰነዘረውን ሃሳብና ግለሰቡን ማንኳሰስ የኢህአዴጐች ያልበሰለ ንቃተ አእምሮ (naïve conscience) ያመነጨው ውጤት ነው፡፡ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ከኢህአዴግ የማይተናነስ የማይገሰስ እኩል መብት እንዳለው መረዳት ያስፈልጋል፡፡ የአመለካከት ልዩነትን ጠብቆ የአብሮነት ጉዞውን መቀጠል ያስችል ዘንድ የግለሰቦችንም ሆነ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን አመለካከትና አስተያየት በአንድ መልኩ መበየን በኢህአዴግ ዘንድ ቀልጦ ሊጠፋ የሚገባ ጉዳይ መሆን አለበት፡፡

የሰው ልጆች በቋንቋ፣ በባህል፣ በዘር፣ በማህበራዊ ጉዳዮች ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም እያንዳንዱ ሰው ግን ከማንኛውም ሰው የሚለይበት ልዩ የሆነ አስተሳሰብ፤ መረዳትና ባህርይ ያለው ፍጡር ነው፡፡ እውነታው ይህ ሆኖ እያለ፣ ከ90 ሚሊየን በላይ የሆነውን ህዝብ እኔ ብቻ በማስበው እና ባዘጋጀሁት የፖለቲካ ቅኝት ካልሄዳችሁ ብሎ መወንጀል ርካሽ ተግባር ነው፡፡እንደ ጋሪ ፈረስ በአንድ አቅጣጫ ብቻ ከኢህአዴግ የሚመጣውን መረጃ እና አስተሳሰብ ሕዝቡ እንዲከተል ማስገደድ፣ ከዛም አልፎ ያሉትን ልዩነቶች በፈጠራ ክስ እና ዘመን ባፈራው ቃላት 'በአሸባሪነት' እየወነጀሉ ህዝቡን በሽብርና በረሃብ መግዛት ትንሽነት ነው፡፡ ከኢህአዴግ የፖለቲካ ዕቅድ ጋር የማይጣጣሙትን አስተያየቶች እና የሚሸነቁጡ ትችቶችን የሚሰነዝሩ ዜጐችን የተለየ ስያሜ እየሰጡ ዘብጥያ ማውረዱ አስጸያፊ ተግባር ከመሆኑም ባሻገር ብዙ ርቀት የማያስኬድ ረብ የለሽ እንቅስቃሴ ነው፡፡

የህዝብ ልብ የሚያሳርፍ መሪ፤ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያነገበ የፖለቲካ ሥርዓት፣በንግግራቸው ጨዋነትን የተላበሱ መሪዎች መቼ ይሆን ይህች ሀገር የሚኖራት? ከስድብ፣ከጥላቻና ከንቀት ይልቅ ፍቅርን፣ መከባበርን፣ ትህትናን የተመረኮዙ የፖለቲካ ሹመኞችን የምናይበት ጊዜ መቼ ነው? ከሥልጣንና ከገንዘብ ይልቅ ዕውቀትን የተደገፉ መሪዎችን የምናዳምጥበት ጊዜስ መቼ ይሆን? የተንኮል ብኩርና ያነገቡ የፖለቲካ ከያኒያን እንደ ጉም የሚተኑበት ጊዜ እና የናፈቅነው ፍትህ የሰፈነባት ጊዜው ከደጁ የደረሰ ይመስላል - ምክንያቱም የዕብሪቱ መጠን የሞላ ይመስላልና፡፡ ጨዋ ባይሆኑም ስለ ወንበሩ ክብር እንኳን ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን ሊላበሱ አልሞከሩምና፡፡

መሪ ከዜጎች፣ አለቃ ከሰራተኞች፣ መምህር ከተማሪዎች፣ ባል ከሚስት ልቀው ካልተገኙ የሚኖራቸው ትስስር፣ ስኬትንና እርካታን የተላበሱ እንደማይሆኑ በርካታ የሥነ ሥልቦና ባለሙያዎች የሚስማሙበት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ሳይሆን ሲቀር ግን መሪ ከህዝብ፣ አለቃ ከሠራተኛ፣ መምህር ከተማሪ ተሽለው ካተገኙ፤ አላዋቂነታቸውን የሚጠቀሙበት ስልት ቁጡ ባህሪያትን ማሳየት ነው፡፡ ለዚህም ነው፣ የስድብ ከበሯቸውን እየደለቁ አቅም አልባ መሆናቸውን በስድባቸው የሚያሳዩን፡፡

'‹‹ተግሳፅን የሚወድ እውቀትን ይወድዳል፤ ዘለፋን (ትችትን) የሚጠላ ግን ደንቆሮ ነው›› (መፅሐፈ. ምሳሌ 12፡1 እና 2) ተብሎ እንደተጻፈ አስተያየቶችንና ትችቶችን ጽልመት በሞላበት የድንቁርና አረዳድ መረዳት ትንሽነት ነው፡፡ አስተያየቶች ጠቃሚ መረጃን ስለሚይዙ በቅንነት ተረድቶ ነገሮችን ማስተካከል የተሻለ አማራጭ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ስብዕናችሁ የማይፈቅድ ከሆነ ለአጭር ጊዜ በሚኖራችሁ የቴሌቪዥን ቆይታ የመሪነት ሰብዕና እና አንደበት ተላብሳችሁ ቅረቡ።

«አገርህ በለጸገች ቢሉት፣ እኔ የት ሄጄ አለ?» ጦም አዳሪ!

(ደሃው፣ ኢ.ብኮና ጠንቋዩ ...)



ዳንኤል ቢ.

> **ሁሉም ነገር ከአቅሜ በላይ ሆኗል። እናም እራሴን ለማጥፋት ወስኛለሁ። ነገር ግን እራሴን ከማጥፋቴ በፊት ስለ አንድ ነገር እርግጠኛ መሆን እፈልጋለሁ፣ እውን ኢ.ብኮ እንደሚለው ሀገራችን በመለወጥ ላይ ነች? እውን ኢ.ብኮ እንደሚለውስ አገራችን ኢትዮጵያ በቅርብ ዓመታት ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ትመደባለች?**

መቼም «የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (ኢ.ብኮ) የሚዛናዊ ዜና ዘገባ ችግር አለበት» እየተባለ መታማቱ የአደባባይ ምስጢር ነው፤ እኔም እስማማበታለሁ፡፡ ዳሩ ግን ኢ.ብኮ የሚዛናዊ ዘገባ ችግር ብቻ አይደለም ያለበት፡፡ ከኢ-ሚዛናዊ የዜና ዘገባውና ከአሰልቺ ልማታዊ የፕሮፓጋንዳ ፕሮግራሞቹ የተረፉትን ጥቂት የመዝናኛ ፕሮግራሞች እጅ እጅ እስኪሉ ድረስ ያለአግባብ የመደጋገም አባዜ ሌላው መሠረታዊ የተቋሙ ችግር ነው፡፡

የሆነው ሆነና፣ «ነገርን ነገር ያነሳዋል» እንዲሉ፤ ከረጅም ጊዜ በፊት በኑሮ ውድነት ምክንያት ሁሌም እራሱን ለማጥፋት የሚያስብ አንድ ድሃ ሰው ነበር አሉ፡፡ ዳሩ ግን አልተሳካለትም። ልክ የመንጠልጠያ ገመዱን ጣራዉ ላይ አስሮ የኑዛዜ ደብዳቤ መፃፍ ሲጀምር፣ «ኢ.ብኮ» በምሽት ሁለት ሰዓት የዜና እወጃው ከች ይልና፣ ሀገራችን ኢትዮጵያ በአስገራሚ ፍጥነት በማደግ ላይ መሆኗን፣ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ እንደምትመደብ ዜና አንባቢውን ተመስገን በየነን ተመስሎ ሹክ ይለዋል፤ ይህኔ ያመነታል፡፡ «ሆ! ለምን ብዬ ለትንሽ ቀን» ይልና እራሱን የማጥፋት ዕቅዱን ይሰርዘዋል። እንደገና ደግሞ ከሳምንት በኋላ ያገረሸበትና በቀጥር ሰባት ሰዓት ገመዱን ይሰቅላል። አሁንም «ኢ.ብኮ» በተጠቀሰው ሰዓት ዜናው ቤቱ ድረስ ከተፍ ይልና በአማረ ማሞ በኩል የተስፋ ቃሉን ያቀብለዋል። ጭራሽ ተራ አርሶ አደሮች ሳይቀሩ ሚሊኒየነር እንደሆኑ ሲነግረው ራሱን የማጥፋት ወኔው ይከደውና ገመዱን ከሰቀለበት ያወርዳል።

ሰውየው ተስፋ ቆርጦ ገመድ ሲሰቅል፣ ኢ.ብኮ ደግሞ በዜናው ተከታትሎ ሲያከሽፍ፤ እንዲህ እንዲህ እያሉ ኢ.ብኮና ሰውየው ዘንድሮ ላይ ደረሱ አሉ። እንዳይሞት ተስፋ ያለው ይመስለዋል፣ እንዳይኖር ኑሮ ከአቅም በላይ ሆኖበታል። መላ አጥቶ ሲቸገር፣ አውጥቶ አውርዶ አንድ ነገር ብልጭ አለለት። ጠንቋይ ቤት ሄዶ እውነቱን ማጣራት። እናም ወደ አንድ «የሚናገረው መሬት ጠብ አይልም» ወደሚባልለት ስመ-ጥር ጠንቋይ ቤት አመራ አሉ። እንደደረሰም ወረፋ ይዞ ብዙ ሲጠባበቅ (ልብ አድርጉ ወረፋው ጠያቂዎች ስለበዙ ነው) ከቆየ በኋላ ተራው ደርሶ ተጠራና ገባ። ጠንቋዩ ሰውዬም ተረኛ ሰው እንደገባ በተከለሉበት መጋረጃ ቀዳዳ በአንድ አይናቸው አጮልቀው ካዩ በኋላ፣ የእግዜርን በሚመስል ድምፅ «ምን ሲያበር አመጣህ?» ሲሉ ይጠይቁታል። ሰውየውም እየተርበተበተ «ኧረ እንደው ከባድ ችግር ገጥሞኛል አባቴ!» ሲል መልስ ይሰጣል። «እኮ ምን?» አሉ ጠንቋዩ። ሰውየውም «ኧረ እንደው አባቴ፣ የኑሮ ውድነት ነገር አልሆነልኝም፤ በዚሁ ምክንያት እራሴን ለማጥፋት ስሞክር ብዙ ጊዜ ቢሆነኝም፣ «ኢ.ብኮ» ቤቴ ድረስ እየመጣ ትንሽ ብታገስ ሁሉም ነገር እንደሚለወጥ እየወተወተ ሙከራዬን እያከሸፈብኝ ተቸገርኩ። አሁን ግን አልቻልኩም፣ ሁሉም ነገር ከአቅሜ በላይ ሆኗል። እናም እራሴን ለማጥፋት ወስኛለሁ። ነገር ግን እራሴን ከማጥፋቴ በፊት ስለ አንድ ነገር እርግጠኛ መሆን እፈልጋለሁ፣ እውን ኢ.ብኮ እንደሚለው ሀገራችን በመለወጥ ላይ ነች? እውን ኢ.ብኮ እንደሚለውስ አገራችን ኢትዮጵያ በቅርብ ዓመታት ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ትመደባለች? እውን ኢ.ብኮ እንደሚለው ከእኔ በስተቀር ሌላው ሁሉ ጠግቦ ያድራል? እውን ድህነትስ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተረት ይሆናልን?» እነዚህን ጥያቄዎች እርስዎን ለመጠየቅና እውነቱን ለማረጋገጥ ነው የመጣሁት። እውነት ኢ.ብኮ የሚለው እውን የሚሆን ከሆነ ለትንሽ ጊዜ ብዬ ራሴን ከማጥፋት ለአጭር ጊዜም ቢሆን ተቸግሬ መቆየትን እመርጣለሁ፡፡» በማለት የመጣበትን ያስረዳል።

ጠንቋዩም፣ ግሩም ነው፣ እንዲህ ያለ ጥያቄ ካንተ በስተቀር እስከአሁን የጠየቀኝ የለም። ለመሆኑ ጥያቄህን ጨረስክ?» ይሉታል። አዎ ሲል ይመልሳል ሰውየው። ይሄኔ ጠንቋዩ ከመጋረጃቸው ተስፈንጥረው ይወጡና አንዴ በጥፊ ያጮሉታል። ሰውየውም ሰማይ መሬቱ ዞሮበት እየተርበተበተ «ምነው አባቴ፣ ምን አጠፋሁ?» ሲል ይጠይቃል። ጠንቋዩም «እንዴት አባክ ብትንቀኝ ነው? እኔኮ እዚህ የተቀመጥኩት ለሰው የተሰወረን፣ ለፈራጅ የቀለለን እውነት ልገልጥና ልናገር እንጂ እንዲህ ያለውን ሀገር ያወቀው፣ ፀሀይ የሞቀውን ተረት ልደግም አይደለም። ነው ወይስ አንተ የምታውቀውን እኛም እናውቀዋለን ብለህ ልትዘብትብኝ ፈልገህ ነው?!» በማለት ያፈጡበታል። ሰውየው ግራ በመጋባት፣ «ኧረ አባቴ፣ እንደዛ አስቤ አይደለም፤ ግራ ቢገባኝ መላ ቢያጥረኝ ነው የመጣሁት» አለ እየተቅለሰለሰ። ጠንቋዩ ግን አሁንም ከብስጭታቸው አልበረዱም፣ ጭራሽ ባሰባቸው! «ምናባህ መላ ያጥርሃል? እንኳን ኢ.ብኮ እግዜር እራሱ ‘በአምስት ዓመት አይደለም በሀምሳ ዓመት ከኢትዮጵያ ድህነት ይጠፋል’ ቢል እንደማይሆን ጠፍቶህ ነው ወይ?!» ይሉና ያምባርቁበታል። (ሰዉየውም በሆዱ እርስዎስ ልክ ነዎት፡፡ እንደእርስዎ ያለ የቀን ጅብ እያለ በየት በኩል ሲል አጉተመተመ)። ጠንቋዩ ግን «ነገረኝ እንጂ?! አንት የማትረባ ቆረቆንዳ!» በማለት በድጋሚ አምባረቁበት (በልባቸዉ ግን መጠንቆል ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ዛሬ ገና የሚያውቁትንና ትክክለኛ ነገር ስለመለሱ ተደስተዋል)። ሰውየው ግን በቀላሉ እንደማይለቁት ስለገባው፣ «ልክ ነዎት አባቴ፣ ይቅር በሉኝ፤ አሁን ገብቶኛል» ብሎ እግራቸው ስር ይወድቅና ይለምናል። ጠንቋዩም «ተነስ!» ካሉ በኋላ አንዴ በካልቾ ያቀምሱትና በዘበኛ አስይዘው ያስወጡታል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ግን ሰውየውን አየሁ ያለ አልተገኘም። የበላው ጅብም ቢሆን እስከአሁን አልጮኸም። አንዳንዶች ግን በአንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ በሚገኝ የቀበር ሀውልት ላይ የሰፈረን ፅሁፍ በጥርጣሬ አይን እያዩ፤ እራሱን ከዚህ ሀውልት ሥር ሳይቀብር እንዳልቀረ በእርግጠኝነት ሳይሆን በጥርጣሬ ይናገራሉ። «ሀገርህ በለጸገች ቢሉት እኔ የት ሄጄ አለ?» ጦም አዳሪ! እንዲል በሀይሉ ገ/እግዚአብሔር። ለማንኛዉም ሀውልቱ ላይ ተፅፎ የተገኘዉ ፅሁፍ እንዲህ ይነበባል፣

ዳግም ላይነሳ በፅኑ የማለ፣

ከዚህ ሀውልት ሥር የተኛ ድሀ አለ።

የኢትዮጵያውያንን ሐሳብ...

ከ ገፅ 6 የዞረ

አርዌላዊው መንግሥት

እንግሊዛዊው የሽሙጥ ደራሲ ጆርጅ ኦርዌል፣ 1984 የሚል ርዕስ በሰጠው ልቦለዱ ‹‹የወደፊቱን ለመቆጣጠር፣ ያለፈውን መቆጣጠር ያስፈልጋል፤ ያለፈውን ለመቆጣጠር ደግሞ አሁንን መቆጣጠር ያስፈልጋል›› ብሎ አሽሟጥጧል። ሽሙጡ ‹ኦርዌልያዊ› እየተባለ የሚታወቅ የፖለቲካ አስተሳሰብ ሆኗል። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው መንግሥትም ይህንኑ ‹ስትራቴጂ› ሲጠቀምበት ማየት የተለመደ ነው። እያንዳንዷን የአሁን ዘመን ትርክት በመቆጣጠር እና ብቸኛው ታሪክ እና ትርክት ተናጋሪ በመሆን፣ የኢትዮጵያን ታሪክ ሳይቀር ራሱ በሚመቸው መንገድ እየገለጸ እና እያስተማረ ለወደፊቱ የሚበጀውን ስንቅ ለማኖር እየተውተረተረ ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን የቴክኖሎጂ ዘመን ማኅበራዊ አውታሮችን ፈጠረ። የነፌስቡክ እና ትዊተር መወለድ ያልተጠበቀ ክስተት ነው። በተለይ ኢትዮጵያ ውስጥ ላለው መንግሥት በቀደሙት ምርጫዎች ብዙም ተገዳዳሪ ያልነበረ እና ያልታሰበበት ፈተና ነበር።

ቴክኖሎጂን በመቆጣጠር ረገድ ቻይናና ራሽያ ተወዳዳሪ የላቸውም። ቻይና ‹ፌስቡክ›ን ‹ባይዶ› በሚባል፣ ‹ትዊተር›ን ‹ዌይቦ› በሚባሉ አገር በቀል አውታሮች ተክታቸዋለች። እነዚህኞቹ በቻይና መንግሥት ጥብቅ ሳንሱር የሚያልፉ አውታሮች ብዙ ቃላቶችን እያጠለሉ ለመንግሥት ደኅንነት ሠራተኞች የሚያስተላልፉ በመሆናቸው ዜጎች በፍርሐት መንግሥታቸው የማይወደውን ነገር አይጽፉባቸውም። ይህ ብቻ በቂ አለመሆኑን ስለሚያውቁም፣ የኮሙኒስት ፓርቲ አመራሮች አቅጣጫ አስቀያሽ፣ አስተባባይ፣ እና ተሳዳቢ አስተያየት ሰጪዎችን በአንድ አስተያየት ‹50 ሳንቲም› በመክፈል አሰማርተዋል። ራሽያም ለምሳሌ ‹ዩትዩብ›ን፣ ‹ሩትዩብ› በተባለ ድረ-አምባ ተክታለች፤ ቅጥር ጠማሪዎችንም አሰማርታለች። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውም መንግሥት ቴክኖሎጂን በቴክኖሎጂ መተካት አቅሙ ስላልፈቀደለት፣ ሐምሌ 2006 ዓ.ም ገደማ 400 ሰዎችን ባሕር ዳር ላይ በማኅበራዊ አውታሮች ላይ አስተያየት ሰጭ ታማኝ ካድሬዎችን አሠልጥኗል። አሁን በማኅበራዊ አውታሩ ላይ የሚታየው ያልተሰበሰበ፣ ቅጥ ያጣ እና ዘለፋ የበዛበት የማኅበራዊ ሚዲያው ምስቅልቅል ዕጣ ፈንታም የዚያ ሥልጠና ውጤት እንደሆነ ይገመታል።

ከወረቀት አንስቶ እስከ በይነመረብ ድረስ የሚደረጉ ዕቀባዎች በሙሉ የሚደረጉት በማንም ላይ አይደለም። በኢትዮጵያውያን ላይ ነው። የገዢ ልሒቃኑ ይህንን የሚያደርጉት በብዙኃኑ ጥቅም እያሳበቡ ነው፡፡ብዙኃን ግን እነማን ናቸው? ራሳቸውን መግለጥ እና የሚጠቅማቸውን መረጃ ማግኘት ያልቻሉ ብዙኃን ተጠቃሚ የሚሆኑት በምን መንገድ ነው? ብዙኃን ገንዘባቸውን የሚከፍሉለት እና በሥማቸው በተገኘ ገንዘብ የሚተዳደሩት «የመንግሥት» ብዙኃንመገናኛዎችእውንብዙኃኑንእያገለገሉነውወይስየገዢ ልሒቃኑን? እነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች እንዲዳፈኑ፣ መንግሥት ይተጋል፡፡ምክንያቱም ኢትዮጵያውያን ሐሳባቸውን መግለጽ እና የሌሎች አቻዎቻቸውን ሐሳብ ማድመጥ የቻሉ ጊዜ ኢሕአዴግ ታሪክ የሚሆን እንደሆነ ያውቃልና!

ሀይ ባይ ያጡት ‹‹ትናንሽ እግዜሮች››

ኢዩኤል ፍስሐ

<<“ትናንሽ እግዜሮቹ” እብሪታቸውን በአደባባይ ያሳዩዋቸዋል፡፡ “የአይንህ ቀለም አላማረኝም” ብለውም ከበር ላይ ይመልሷችኋል፡፡ ሕጉን እያጣቀሳችሁ ልትሞግቷቸው ብትሞክሯቸው “ሕጉን ለእኛ ተወው” የሚል ንቀት አዘል መልስ ይሰጧችኋል፤ አልያም ደግሞ “ምንም አታመጡም!” ይሏችኋል>>

ዘወትር የሚያብሰለስለኝ አንድ ዓብይ ጉዳይ አለ፡፡ ጉዳዩ ራሳቸውን ከሕግ በላይ አድርገው ሕግን በተደጋጋሚ እየተላለፉ ስለሚገኙት የአገዛዙ አገልጋይ ስለሆኑትና ሀይ ባይ የሚላቸው ስለጠፋው «ትናንሽ እግዜሮች» ነው፡፡ እነኚህ የተሰጣቸውን ትንሽዬ ሥልጣንን መከታ በማድረግ አያሌ በደልን ይፈፅማሉ። በእኔ እምነት፣ «ትናንሽ እግዜሮቹ» የሕግ የበላይነት በዛሬዋ ኢትዮጵያችን እንደሌለ ህያው ምስክር ሲሆን መገኛቸውም ብዙ ነው፡፡ በዛሬው ጽሑፌ በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ሥር ስለሚገኙት «ትናንሽ እግዜሮች» ጥቂት ልል ወደድኩና ይህቺን ከተብኩ፡፡

በታሪክ ሀገራችን ከአምባገነኖች መዳፍ ተላቅቃ የማታውቅ ሀገር መሆኗ ይታወቃል፡፡ በዛሬው አምባገነን አገዛዝ ላይ ብርቱ ተቃውሞ የሚያሰማ ኢትዮጵያዊ ደግሞ ማረፊያው ቃሊቲ፣ ዝዋይ፣ ቂሊንጦ አልያም ሸዋ ሮቢት ነው፡፡እነዚህ እስር ቤቶች በኢትዮጵያ መንግሥት «የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር» የሚል ስያሜ የተሰጣቸው ’ማረሚያ’ ቤቶች ናቸው፡፡ በግሌ በእነዚህ ‘ማረሚያ’ ቤቶች ቆይታ አድርገው የወጡ የሕግ ታራሚዎችን ለማነጋገር ጥረት አድርጌያለሁ። አብዛኞቹ ማለት ይቻላል፣ ስለ ’ማረሚያ’ ቤቶቹ የነገሩኝ ነገር ተመሳሳይ ነው፡፡ አስተያየታቸውን ስጠቀልለውም ማረሚያ ቤቶቹ ማረሚያ ሳይሆኑ ማጎሪያ ናቸው፡፡ በማረሚያ ቤቶቹ የሚገኙት አብዛኞቹ ፖሊሶች ታራሚን የሚንቁ፣ በሙስና የተጨማለቁ፣ ከሕግ በላይ የሆኑ፣ ሀይ ባይ ያጡ ናቸው የሚል ነው፡፡ አስተያየት ሰጪዎቹ «በማረሚያ ቤቶች ውስጥ የሚገኙትን ፖሊሶችን በጠቅላላ ጨፍልቆ መመልከት አግባብ አይደለም» ይላሉ። የተወሰኑ ቢሆኑም ሕግን የሚያከብሩና ለታራሚውም ክብር ያላቸው ፖሊሶች እንዳሉ ይመሰክራሉ። በተጨማሪም እነዚህ የሕግ ታራሚዎች ከህሊና እስረኞች በተሻለ መብታቸው እንደሚከበርላቸው ይናገራሉ፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት «የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር» ከሚላቸው አራት ማረሚያ ቤቶች መካከል ሁለቱን በተደጋጋሚ ተጉዤባቸዋለሁ። የጉዞዬ ዓላማም አምባገነኑን አገዛዝ በብርቱ ስለተቃወሙ ብቻ ወደ ወህኒ የተወረወሩትን የህሊና እስረኞችን ለመጠየቅ ነው፡፡ ማንኛውም እስረኛ በማንም የመጠየቅ ሕገ-መንግሥታዊ መብት ቢኖረውም፤ ይህ ሕገ-መንግሥታዊ መብቱ የህሊና እስረኛ ከሆነ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይገፈፋል። «የህሊና እስረኛ በተወሰኑ ሰዎች ብቻ እንዲጠየቅ» የሚል ያልተጻፈ ሕግ አለ፡፡ ይህን ያልተጻፈ ሕግ በመተግበር ረገድ ዋነኛ ሚናን የሚጫወቱት ሀይ ባይ ያጡት «ትናንሽ እግዜሮች» ናቸው፡፡ የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 21 ንዑስ አንቀፅ 2 በሕግ ተፈርዶባቸው ስለሚገኙ ሠዎች በተመለከተ «ማንኛውም ሠው ከባለቤቱ፣ ከቅርብ ዘመዶቹ፣ ከጓደኞቹ፣ ከኃይማኖት አባቱ፣ ከዶክተሩና ከጠበቃው ጋር የመገናኘት መብት አለው» ሲል ይደነግጋል። ሕገ-መንግሥቱ ይህን ቢልም፤ የአገዛዙ ሎሌዎች በሕገ-መንግሥት ሳይሆን በፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም አጠራር፣ በሕግ አራዊት የሚመሩ ናቸውና ሕገ-መንግሥቱን በጠራራ ፀሃይ ይንዱታል፡፡ በአገዛዙ ቋንቋ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን (ሥርዓት ከተባለ) በሀይል በመናድ ሊከሰሱ የሚገባቸው እነዚህ የአገዛዙ ሹመኞች ነበሩ፡፡

በአሁኑ ወቅት ሕገ-መንግሥታዊ መብታቸው የተናደባቸው አያሌ የህሊና እስረኞች በሀገራችን አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፣ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሣለኝ፣ ፖለቲከኛው አንዷለም አራጌና ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ ከብዙ በጥቂቶቹ ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ የህሊና እስረኞች ቁጥራቸው ውስን በሆኑ የቤተሰባቸው አካል ብቻ እየተጠየቁ ይገኛሉ። በጓደኞቻቸው፣ በቤተዘመዶቻቸውና በኃይማኖት አባቶቻቸው የመጎብኘት መብታቸው ተገፍፎ «ትናንሽ እግዜሮቹ» ብቻ በፈቀዱት የሰው ቁጥር ብቻ እየተጠየቁ ይገኛሉ።

«ትናንሽ እግዜሮቹ» እብሪታቸውን በአደባባይ ያሳዩዋቸዋል፡፡ «የአይንህ ቀለም አላማረኝም» ብለውም ከበር ላይ ይመልሷችኋል፡፡ ሕጉን እያጣቀሳችሁ ልትሞግቷቸው ብትሞክሯቸው «ሕጉን ለእኛ ተወው የሚል» ንቀት አዘል መልስ ይሰጧችኋል፤ አልያም ደግሞ «ምንም አታመጡም!» ይሏችኋል። «ትናንሽ እግዜሮቹ» ጋር መብትን ማስከበር የሚል ነገር አይሰራም፡፡ እጅ ነስተው፣ ተለማምጠው ካለለፉ ዳግመኛ ያንን ግቢ ላይረግጡም ይችላሉ። በተለይ በተለይ የሚጠይቁት የህሊና እስረኛ ከሆነ፣ ገና ከመግቢያ በሩ ጀምሮ ነገር ነገር ያሰኛቸዋል። ታዲያ ይህን ጊዜ እርስዎም ቆጣ ብለው፣ «ይሄ እኮ ሕገ-መንግሥታዊ መብቴ ነው» ብለው ሙግት ቢገጥሙ ሰሚ የልዎትም፡፡ ሕግና ሕገ-መንግሥት «ትናንሽ እግዜሮቹ» ጋር ቦታ የላቸውምና! «የትናንሽ እግዜሮቹን» እብሪት የሚያሳይ አንድ ገጠመኜን ላካፍላችሁ።

ወዳጆቻችን እስክንድር ነጋንና አንዷለም አራጌን ለመጠየቅ ሰብሰብ ብለን ወደ ቃሊቲ እስር ቤት አመራን፡፡ የእስር ቤቱን ቅጥር ግቢ አልፈን ስማችንን ካስመዘገብን በኋላ፣ የእስር ቤቱ «ትንሽዬ እግዜር» አንዱን ወዳጄን ማንን እንደሚጠይቅ ይጠይቀዋል፡፡ ወዳጄም «አንዷለም»ን ሲል መለሰ፡፡ «ከአንዷለም ጋር ግንኙነትህ ምንድን ነው?» ወዳጄም «የትግል አጋሬ ነው» በማለት መለሰ፡፡ ይህን ጊዜ «ትንሹ እግዜር» ቆጣ በማለት «ስንት መስዋዕትነት ተከፍሎ የመጣ ሥርዓት እያለ የትግል አጋሬ እያልክ ታሸሚጥጣለህ» በማለት ሁላችንም ግቢውን እንድንለቅ አሳሰበ፡፡ ቢለመን፣ ምን ቢባል፣ «ቃሌን አላጥፍም» አለ። «ትንሽዬውን እግዜሩ»ን አረጋግቼው ለማነጋገር ጥረት አደረኩኝ። ጥረቴ ፍሬ እንደማያፈራ እያወኩም ቢሆን ልምምጥ ተያያዝኩት። «እንዴት እንዲህ ይላል?! እኛ በደምና በአጥንት የገነባነው ሥርዓት ላይ እኮ ነው ያሾፈው» አለኝ፡፡ «ትንሹ እግዜር» ቃሉን እንደማያጥፍ ስለገባኝ ውትወታውን ገትቼ ግቢውን ለቅቄ ወጣሁ። እሱ ባስተላፈው ትዕዛዝ እስከዛሬ ድረስ አንዷለም አራጌም ሆነ እስክንድር በተወሰኑ ሰዎች ብቻ እየተጠየቁ ይገኛሉ። እኔም እነሱን የመጠየቅ ሕገ-መንግሥታዊ መብቴ ተጥሶ እነሱም በወዳጆቻቸው የመጎብኘት ሕገ-መንግሥታዊ መብታቸው ተጥሶ ይገኛል።

«ትናንሽ እግዜሮቹ» ሀይ ባይ እንደሌላቸው ማሳያ የሚሆን አንድ ሌላ ክስተት ላካፍላችሁ። ከተመሰረተባቸው የሽብርተኝነት ክስ፣ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 19ኛ ወንጀል ችሎት በነጻ ያሰናበታቸው፤ የአንድነት፣ የአረናና የሰማያዊ ፓርቲ አመራር አባላት የሆኑት ሀብታሙ አያሌው፣ ዳንኤል ሺበሺ፣ አብርሃ ደስታና የሺዋስ አሠፋ ታህሳስ 12 ቀን 2007 ዓ.ም ከሌሊቱ 8፡00 ሰዓት «ማረሚያ» ቤቱ ’ፍተሻ‘ ሲል የሰየመውን ዘረፋ በተቃውሞ አመራሮቹ ላይ ይፈፅማል፡፡ አመራሮቹ ይህን በማስመልከት ታህሳስ 15 ቀን 2007 ዓ.ም ክሳቸውን እያየ ለሚገኘው የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 19ኛ ወንጀል ችሎት በጠበቃቸው ተማፃኝ አባቡልን አማካኝነት አቤቱታቸውን ያሰማሉ። ከተቃውሞ ጎራ አመራር ከሆኑት መካከል አቶ ሀብታሙ አያሌውም ለፍርድ ቤቱ እንዲህ በማለት አቤቱታቸውን መናገራቸውን አስታውሳለሁ፡-

«በህይወቴ ላይ የደህንነት ስጋት አለብኝ ነው እያልኩ ያለሁት፤ ይህንን ስጋቴን ለችሎት እያስረዳሁ ነው፡፡ ግን እርስዎ የበቀል እርምጃ እንዲወሰድብን ማሳሰቢያ እየሰጡ ነው፡፡፡ ይህ ተገቢ አይደለም። በእርግጥ አሁንም የበቀል እርምጃ እንደማይወሰድብን ማረጋገጫ የለንም። እሺ ለማን አቤት ይባላል?! የደረሰብንን በደል ለፍርድ ቤት ከማስረዳት ውጪ ለማን አቤት እንላለን?!»

የአቶ ሀብታሙ አያሌውን ምላሽ ተከትሎ የችሎቱ ዳኛም «እርስዎ ደረሰብኝ የሚሉት ነገር እውነት ነው አይደለም የሚለውን ማጣራት ይኖርብናል፤ አሁን ላይ ቅሬታውን ማቅረቡ ማረሚያ ቤቱ የበቀል እርምጃ እንዲወስድ ሊገፋፋው ይችላል» በማለት ምላሽ መስጠታቸውን አስታውሳለሁ።

በወቅቱም ይህንን ዜና ለመዘገብ በችሎቱ ተገኝቼ የነበረ ሲሆን፤ ከአንድ ዳኛ እንዲህ የሚል ቃል ስሰማ እጅግ ተሸማቅቄ ነበር። አንድ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ፣ በማረሚያ ቤት ያሉት «ትናንሽ እግዜሮች» ምን ሊፈፅሙ እንደሚችሉና ከሕግ በላይ መሆናቸውን በግልፅ ሲናገር ከመስማት በላይ ምን የሚያሳፍር ነገር አለ? የዳኛው «የበቀል እርምጃ እንዲወስድ ሊገፋፋው ይችላል» ማለት «ትናንሽ እግዜሮቹ» የፈለጉትን ቢፈፅሙም በሕግ ያለመጠየቅ መብት አላቸው የሚል አንደምታ የያዘ ንግግር አድርጎ መረዳት ይቻላል፡፡

ፍርድ ቤቱ የተቃውሞ አመራሮቹ ባቀረቡት ክስ ላይ የካቲት 25 ቀን 2007 ዓ.ም በተሰየመው ችሎት የተከሳሾቹን አቤቱታ ሙሉ ለሙሉ ውድቅ አድርጎ፤ ዝርፊያ የፈፀሙት «ትናንሽ እግዜሮች» ላይ አንዳችም ቅጣት ሳያስተላልፍ ቀርቷል፡፡ የዳኛው «ማረሚያ ቤቱ የበቀል እርምጃ ሊወስድ ይችላል» የሚለውን ንግግር ችሎት ውስጥ ተቀምጬ ሳደምጥ ፍርድ ቤቱ «ትናንሽ እግዜሮቹ»ን ከሕግ በላይ አድርጎ እንዳስቀመጠና የቅጣት ውሳኔ ሊያስተላልፍ እንደማይችል ገምቼ ነበር፤ የሆነውም ይህ ነበር። ይባስ ብሎ የፍርድ ቤቱ [illegible] የተቃውሞ አመራሮቹ ችሎት መድፈር በሚል በመጀመሪያ የሰባት ወር፣ በመቀጠል ደግሞ የዘጠኝ ወር እስራት በይነውባቸዋል። [illegible] ዘረፋ [illegible] እስራት ተበይኖባቸዋል፡፡ ታዲያ ከዚህ ክስተት በላይ «ትናንሽ እግዜሮች» ከሕግ በላይ መሆናቸውን የሚያሳይ ምን ነገር አለ?

አገዛዙ ሕግን አርክሶ ከሕግ በላይ የሆኑ «ትናንሽ እግዜሮች»ን ፈልፍሏል። እነዚህ «ትናንሽ እግዜሮች» አገዛዙ እስካለ ድረስ አብረው የሚኖሩ ሀይ ባይ ያጡ ትናንሽ መንግሥታት ከሆኑ ሰነባብተዋል። እናንተ «ትናንሽ እግዜሮች» ሆይ «መንግሥታት ይቀያየራሉ ሀገር ግን ዘላለማዊ ናት!» የሚለውን አባባል ሰምታችሁት እንደሆነ ባለሙሉ ተስፋ ነኝ። «አገዛዙ ሲቀየር እኛም እንደቀደሞቹ እንሸሻለን» ወይም «በሕግ አንጠየቅም» ብላችሁ ከሆነ ይህን ሀሳባችሁን ታስቡበት ዘንድ በትህትና እማፀናችኋለሁ። ነገ ላይ ልጆቻችሁ በእናንተ አፍረው አንገታቸውን እንዳይደፉ ዛሬ ላይ መታበያችሁን አቁሙ! የጥቂት ፈላጭ ቆራጮች ሎሌ ከመሆን የራሳችሁን ዕድል በራሳችሁ ወስኑ። ጥቂቶች በእናንተ ላይ ቆመው የጭቆና ቀምበርን [illegible] እናስጠብቃለን! ምርጫው የእናንተ ነው፤ የጥቂቶች አሽከር ሆኖ መቀጠል ወይም ከብዙሃኑ ጎን በመሰለፍ ነፃነትን መቀዳጀት ይሻላል? ምርጫውን ለእናንተ ተውኩት!!

ስምን ከመዝገብ ቃላት እንደማሰረዝ፣ ረሃብን ከአንጀት ማባረሩ ቀላል አይደለም!

ምስክር ዐወል

«እየታገልንለት፣ እየተዋጋንለት፣ ያለው ህዝብ በረሃብ እያለቀ ነው» የቀድሞ ጠ/ሚ/ር መለስ ዜናዊ

«ዋይ ዋይ ሲሉ ወገኖች» ድምጻዊ ጥላሁን ገሠሠ

"We are the world" ድምጻዊ ማይክል ጃክሰን

ከላይ የጠቀስኳቸው ሰዎች በአንድ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ ተከስቶ ስለነበረው ረሃብ ያንጎራጎሩና የተማፅኖ ድምጽ ያሰሙ ነበሩ:: እንደ አሁኑ በ«ልማት» ሳንንበሸበሽ፣ በቀን ሶስት ጊዜ በልተን (አንዳንዶቻችን መክሰስን ጨምሮ አራት ጊዜ)፣ ሆዳችን ሞልቶ ፎቅ ስንገነባ፣ ልማታዊ አርሶ አደሩ ሚሊየን ብሮችን ሲቆጥር ሳናይ፣ በደጋውም በቆላውም ያለ «አዝመራ በአዝመራ ነን» እያለ መግለጫ የሚሰጠን የግብርና ባለሙያ ሳይኖረን፣ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (ኢብኮ) አሁን የሚያስጎበኘን ኢትዮጵያ ሳትፈጠር፣ ጣዕረ-ሞት በሀገራችን ክንፉን ዘርግቶ በነበረበት ወቅት፣ «አቤት!» ያሉ ባለውለታዎቻችን ናቸው::

በዚህ ጽሑፌ ከሰሞኑ በሀገራችን በተከሰተው ድርቅና ከ30 ዓመት በፊት አንድ ሚሊየን የሚጠጉ ወገኖቻችን እንደ በጋ ቅጠል ስላረገፉበት ረሃብ በጥቂቱ ለመዳሰስ እጥራለሁ::

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ረሃብን ጠንቅቆ ያውቀዋል:: በአንድ ወቅት ምግብ አልደረሰ ሆኖ፣ ኪሳችን ገንዘብ ሳይኖር ቀርቶ፣ አሊያም ምግብ በአቅራቢያችን በማይገኝበት ቦታ ሆነን ተርበን እናውቅ ይሆናል:: የረሃብን ስሜት የማታውቁ ካላችሁ እናንተ የባለሁለት አሃዝ አዳጊዋ ሀገር ዜጎች ስለሆናችሁ አልፈዋለሁ:: ባትራብም የወገንህ መራብ የሚያሳስብህ ከሆንክ ግን ተከተለኝ::

ረሃብ በሀገሬ እንዲህ ነበር፡- ሰዎች ለቀናት ብሎም ለሳምንት፣ ለወራት፣ ለዓመት የሚቀምሱት ይቅርና አይተው የሚጎመዡበት የምግብ ዘር በአጠገባቸው አልነበረም:: በዚያን ጊዜ ሰው ቆዳው ከአጥንቱ ተጣብቋል! እግሩና የሰውነት አካሎቹን አልችልም ብለው እንደ ቄጤማ ተብረክርኳል! ጆሮው እንደ ሰፌድ ተዘርግቷል! አንጀቱ ወደ ውስጥ ከመራቁ የተነሳ መተንፈስ አቅቶታል! የወገኖቻችን ረሃብ እንዲህ ነበር::ስታስቡት ልብ-ወለድ እየመሰላችሁ ከሆነ አንጄ ማንበቡን ቆም አድርጉና ጎግልን «ረሃብ ምን ይመስላል?» ብላችሁ ጠይቁት:: እኔ ካልኩት በላይ፣ «ሰው እንዲህም ይከሳል እንዴ?» እስክትሉት ድረስ ያስጎበኛችኋል::

የእርስ በእርስ ጦርነት፣ የተፈጥሮ አደጋዎች፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ አስተማማኝ ያልሆነ የግብርና ፖሊሲ ለድርቅና ለረሃብ መከሰት አይነተኛ መንስኤዎች ናቸው::

በአንድ ወቅት ዶ/ር መረራ ጉዲና በንግግራቸው እንዲህ ብለው ነበር:: «የሚበላውን ያጣ ህዝብ መሪውን ይበላል» እውነት ነው አይደለም መሪውን፣ እናት ልጇቿን መብላቷን ታሪክ ይነግረናል:: ነገር ግን፣ አሁን ላይ የዶክተር መረራን አባባል ቆም ብዬ ሳጤነው «መሪውን ለመብላት መሪው ካለበት ድረስ የሚያስኬድ አቅም ያጣ ረሃብተኛስ እውን መሪውን ይበላል?» ብዬ እንድጠይቅ ያደርገኛል:: ይልቁንስ በወደቀበት በረሃ ተጋድሞ በጣዕረ-ሞት የአሸዋ አቧራ እየቃመ «መሪዬ መጥቶ ያነሳኝ ይሆን ወይ?» እያለ ተስፋ የሚያደርግ ይመስለኛል::

የዚህ አይነት መቅሰፍትና የረሃብ ጠኔ ሲወርድብን፣ በወቅቱ የደረሱልንን (ከላይ የጠቀስኳቸውን ሶስት ሰዎች) ሥራ በትንሹ ልጠቅስ እወዳለሁ::

1983-85 እ.አ.አ. ኢትዮጵያውያን በረሃብ ጥርሳቸውን እያፋጩ የዓለምን የእርዳታ እጅ ይጠባበቁ ነበር:: ነገር ግን፣ ዓለም አፍሪካን ብሎም የኢትዮጵያን ድንበር አሻግሮ የወደቁ አጽሞችን፣ በሲቃ የሚያለቅስን ህፃን ድምጽ የሚሰማ ሚዲያና የሚያሳይ መነጽር አልነበራትም:: ምስጋና ለማይክል ብሩክ ይሁንና በአንድ የቢቢሲ ፕሮግራም ዓለም የኢትዮጵያንን ሰቆቃ እንዲመለከት አደረገ:: ዓለምም ከዳር እስከ ዳር የረሃብ የመጨረሻው የጉዳት ጥግ ምን እንደሚመስል በእነማይክል ብሩክ የካሜራ ሌንስ አማካኝነት ታዘበ::

> የረሃብ ስማችንን ከመዝገበ ቃላት አሰረዝን» እያልን
> የጨፈርንበት አቧራ ሳይጠፋ ዳግም የገረጡ ፊቶች፣ የቀጨጩ
> እጆች፣ ያገጠጡ ጥርሶች ይዘን ዳግመኛ የ30 ዓመት ታሪክ ለመድገም
> እየተንደረደርን ነው:: እኔን ውስጤን እየራበኝ፣ ‹ጠግበሃል፣ በቀን
> ሶስት ጊዜ መብላት ትችላለህ› የሚለኝ መሪ ሲኖረኝ ደግሞ ረሃቡ
> ከጎዳኝ በላይ አዕምሮዬም ክፉኛ ይጎዳል::

«ይህን እያየን ዝም አንልም!» ያሉ ሁሉ ኢትዮጵያውያንን ለመርዳት መንቀሳቀስ ጀመሩ:: የ21ኛው ክፍለ ዘመን ገዳይ ክስተት በሚል አፍሪካውያንን በተለይም (ኢትዮጵያውያንን) ለመታደግ ሁሉም በያለበት ተንቀሳቀሰ::

በቴሌቭዥን የተመለከተ፣ በጋዜጣ ያነበበውና ልቡ በከፍተኛ ያዘነው የእንግሊዝ ህዝብ በሶስት ቀናት ውስጥ አምስት ሚሊየን ፓውንድ አሰባሰበ:: በተጨማሪም ጥበብ፣ በተለይም ሙዚቃ ነፍስ ለመታደግ መከረች:: ማይክል ጃክሰንንና ቦብ ጊልዶፍን ፊታውራሪ አድርጋ ስለ መረዳዳትና አንድነት "we are the world' የሚል ድምጿን አሰማች:: በማይክል ጃክሰንና በሊዮኔል ሪቼ ተጽዕኖ በ1985 በ A and M studio ተሰርቶ የቀረበው አልበም፣ በ20 ሚሊየን ኮፒ ሽያጭ የዓለማችን 30 ምርጥ የምንጊዜም ሙዚቃ ለመሆን በቅቷል:: በታሪክም በፍጥነት ተሸጦ ዓለምን ያጥለቀለቀ የአሜሪካን ፖፕ ሙዚቃ ተብሎ ተመዝግቧል:: ለዚህም ስኬታማ ስራቸው የፕላቲንየም፣ የኳድሪትንየምና Recording Industry Association of America ሰርተፍኬት ሸልሞታል::

በዚያው የረሃብ ዘመን፣ በረሃ ትግል ላይ የነበረው መለስ ዜናዊ ለቢቢሲ በሰጠው ቃል ምልልሱ «እየታገልንለት እየተዋጋንለት ያለው ህዝብ በረሃብ እየረገፈ ነው» በማለት ዓለምን በሚያሳዝን የተማጽኖ ድምጽና የድረሱልን ጥሪ አስተላልፏል:: አቶ መለስን በዘመኔ እንደዛ አዝኖና ተከፍቶ አይቻው አላውቅም:: አባታቸው አቶ ዜናዊ አስረስ አርፈው ለሥርዓተ ቀብር አድዋ አመርተው ሳለ እንኳን እንደዛ አላዘኑም:: እኔ የሚገርመኝ ዓለም አሁን የተከሰተው ረሃብ በጊዜ መፍትሄ ካልተፈለገለት ችግሩ የከፋ እንደሚሆን ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እያስጠነቀቁ ባለበት ሁኔታ «አልተራብንም፣ ልማት ላይ ነን:: ልማታችን እንዳይስተጓጎል ነው እንጂ የተራቡትን መመገብ እንችላለን» ማለት ምን ማለት ነው? ራዕዩን ከወረሱ አይቀር እስከ ሩህሩህ ልብ ድረስ መሆን ነበረባቸው:: የሚሰራውን መንገድ የሚራመድበት ሰው ከሌለ ምን ያደርጋል?!

እኛም እንደ ዜጋ፣ ጋሽ ጥላሁንም
«ዋይ ዋይ ሲሉ የረሃብን ጽዋ
ወገኖቼ አልፍኳቸው በአይኔ አይቼ»

እንዳለው እያየን ዝም ከምንል ቢያንስ ጉዳያቸውን ጉዳያችን አድርገን «የኔ ጉዳዩ ነው» እንበላቸው:: ካፌና ሬስቶራንት ቁጭ ብለን፣ እየተመገብን በድንገት በረሃብ የተወጋ ህፃን ከእናቱ ተለይቶ አይን አይናችንን እያየ «ራበኝ፣ የምበላው» ሲለን እንዴት ልባችን አይደማም?!

በመረዳዳት ጥሩ ታሪክም ነበረን:: ከ«አንድ ብር ለአንድ ወገን» እስከ «ሰው ለመርዳት ሰው መሆን በቂ ነው» እየተረዳዳን ነበር::

መኪናችሁን እየነዳችሁ አሊያም በክፍለ ሀገር አውቶቡስ እየተጓዛችሁ አሻራችሁ የገጠሩን ኢትዮጵያዊ ህይወት ለማየትና ለመረዳት ሞክሩ እስኪ::

ምናልባትም አሻግረን ከምናየት ደሳሳ ጎጆ ውስጥ የረሃብ ጣዕረ-ሞት ሸብቦት የሚያቃስት ህፃን ታገኙ ይሆናል:: «ራበኝ! እማዬ ራበኝ!» የሚለውን ልጇን ፊት ላለማየት ድንጋይ ላይ ቁጭ ብላ እንባዋን የምታፈስ እናትም ታገኙ ይሆናል:: «የረሃብ ስማችንን ከመዝገበ ቃላት አሰረዝን» እያልን የጨፈርንበት አቧራ ሳይጠፋ ዳግም የገረጡ ፊቶች፣ የቀጨጩ እጆች፣ ያገጠጡ ጥርሶች ይዘን ዳግመኛ የ30 ዓመት ታሪክ ለመድገም እየተንደረደርን ነው:: እኔን ውስጤን እየራበኝ፣ ‹ጠግበሃል፣ በቀን ሶስት ጊዜ መብላት ትችላለህ› የሚለኝ መሪ ሲኖረኝ ደግሞ ረሃቡ ከጎዳኝ በላይ አዕምሮዬም ክፉኛ ይጎዳል:: ስምን ከመዝገብ ቃላት እንደማሰረዝ ረሃብን ከአንጀት ማባረሩ ቀላል አይደለም!! እኔ በበኩሌ ለእነ አይ.ኤም.ኤፍ ሪፖርት «አፍ ያወራል፣ ተግባር ይገልፃል» ብያለሁ:: ስለ ራሴ ከእኔው በላይ ማን ያውቃል?

ሳይኖረን አለን ብለን ያወራነው አሳፍሮን ጠግበናል እያልን ማለቅ የለብንም:: ደግሞ ማይክል ጃክሰን ዳግም ጥላሁን ገሰሰን ዳግም ማይክል ብሩክን ተመኘሁ::

ልማት እያለማለት ያለው ህዝብ፣ በረሃብ እያለቀ መሆኑን የሚረዳ መሪ ይስጠን!

«ጠግበሃል አትበሉኝ መጥገብ መች እንዲህ ነው?
የወገኔ ማጣት ለኔም ርሃቤ ነው»

ተግባራዊ ክብር ለመምህራን!

መስከረም ያረጋል



ለጊዜው መምህራን ከሥራቸው የሚያገኙት እርካታ፣ የሥራቸውን ፍሬ እያዩ በመደሰት ተወስኗል። ነገር ግን፣ ይህ ሁኔታ በአስቸኳይ ሊቀየር ይገባዋል። መንግሥት መምህራን እያበረከቱት ላሉት ታላቅ ሀገራዊ አስተዋጽኦ፣ ተገቢውን ክፍያ የሚያገኙበትን መንገድ በአፋጣኝ ማስተካከልና ከክፍያ ጋር የተያያዘውን ችግራቸውን የመፍታት ግዴታ አለበት።

«መምህርነት ዕንቁ የሆነ ሙያ ነው» ይለኝ ነበር ለሰላሳ ዓመት በመምህርነት ያገለገለው እና በሙያው በጣም ይኮራ የነበረው አባቴ:: እኔም ይህን ሀሳቡን እጋራለሁ:: መምህርነት ትውልድን የማነጽ ትልቅ ኃላፊነት የተጣለበት ክቡር ሙያ ነው::

«በእርግጥ ግን ይህ የተከበረ ሙያ፣ የሚገባውን ያህል ክብር ተሰጥቶታል ወይ?» የሚል ጥያቄ የጫረብኝ እና ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነኝ፣ በአጋጣሚ ካገኘኋቸው ወጣት መምህራን ጋር ስናወጋ የተነሱ ነጥቦች ናቸው::

መምህራን እያሳለፉ ያሉትን በርካታ ችግሮች የተለያዩ ፀሐፊያን አንስተው አስነብበውናል:: በተማሪዎች እና ወላጆች ካለመከበር እስከ ደመወዝ ማነስ ያሉ ሰፊ ችግሮች ከዚህ ቀደም የተነሱ ቢሆንም ችግሮቹ አሁንም ሳይቀረፉ ቀጥለዋል:: ለዚህም ነው፣ እኔም ከወጣት መምህራን ጋር ከነበረኝ ወግ ተነስቼ ከእነዚህ ተጠቃሽ ችግሮች መካከል አንዱ ስለሆነው የመምህራን ደመወዝ ማነስ ልጽፍ የወደድኩት::

መቼም ማንም ሰው ከሥራው ጋር የተመጣጠነ ክፍያን ቢያገኝ በሥራው ላይ ያለው ትጋት እና እርካታ የተሻለ እንደሚሆን ግልጽ ነው:: ነገር ግን፣ በሀገራችን ኢትዮጵያ የሥራ ድርሻ እና የሚገኘው ክፍያ አለመመጣጠን ችግር በብዙ የሙያ ዘርፎች ላይ በጉልህ ይታያል:: ለዚህም አንዱ ማሳያ የመምህራን ደመወዝ ነው::

እንደእኔ እምነት፣ ብቁ ዜጋን የማፍራትና ትውልድን የመቅረጽ ኃላፊነት የተጣለበት የመምህርና ሙያ እና ለዚህ ጉልህ ድርሻቸው የሚከፈላቸው ወርሃዊ ደመወዝ ፍጹም የተቀራረበ አይደለም::

በአሁኑ ወቅት ብዙ መምህራን እንደሚናገሩት፣ በሚያገኙት ደመወዝ ቤተሰብ መስርቶ ኑሮን ለመምራት ቀርቶ፣ ለራሳቸው በአግባቡ መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን አሟልተው ለመኖር ከባድ ፈተና ሆኖባቸዋል:: በዚህም ምክንያት፣ ብዙ መምህራን ሙያቸውን ቢወዱትም የኑሮን ሸክም ሊያቀልላቸው ያልቻለውን ይህን ክቡር ሙያቸውን ባገኙት አማራጭ ሥራ እየለቀቁ እንደሆነ ይስተዋላል::

የነገውን ሀገር ተረካቢ ዜጋ፣ በዕውቀት የሚያንጸው መምህር፣ ብዙ ዓይነት የተማሪ ባህሪያትን፣ በየትምህርት ቤቱ ያሉ የአስተዳደር ችግሮችን፣ በየጊዜው የሚጠሩ አላስፈላጊ ፖለቲካዊ ስብሰባዎችን፣ እንዲሁም ሌሎች ያልጠከስኳቸውን ብዙ ጫናዎች ተቋቁመው ለሚወጡት ለዚህ ክቡር ሥራቸው፤ ህይወታቸውን እንኳን በአግባቡ እንዲመሩበት ያላስቻላቸውን ክፍያ በማያገኙበት ሁኔታ፣ ሌሎች የሥራ አማራጮችን ወደመፈለግ ቢያመሩ አይፈረድባቸውም:: ምክንያቱም ሙያው ምንም ያህል ክቡር ቢሆንም ኑሮን ማሸነፍ ደግሞ የህልውና ጉዳይ ነው::

መንግሥት ይህን የመምህራን ችግር ቢያውቀውም፣ በተለያዩ ጊዜያት «ደመወዝ ጭማሪ» ተብሎ የሚነገርለት የገንዘብ መጠን ግን እጅግ አነስተኛ እና የመምህራንን ችግር ሊፈታ የማይችል፣ እንዲሁም የኑሮ ግሽበቱን ፍጹም ያላገናዘበ ነው:: በዚህም ቅሬታቸውን ሊያቀርቡ የሞከሩ መምህራን እስከ መታሰር እንደደረሱ ይታወቃል:: ይህ ግን የመንግሥት፣ የመምህራንን ችግር ችላ ማለት የመምህራንን ቅሬታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያባሰው እና በፍላጎትና ምርጫ ሊኖሩ የሚችሉ ዜጎችን እያሸሸ ይገኛል:: መንግሥት «ክብር ለመምህራን» የሚለውን ቃል ከቃላት እና ከባዶ ፕሮፖጋንዳ ባለፈ በተግባር ሲገልጸው እስከአሁን አልታየም::

ባሳለፍነው ዓመት መንግሥት «ክብር ለመምህራን» በሚል መሪ ቃል፣ የመምህራንን የላቀ አገልግሎት ለማውሳት አዘጋጅቶት ከነበረው የተለያዩ ፕሮግራሞች መካከል አንዱ፣ ከ35 ዓመት እና ከዚያ በላይ ያገለገሉ ቁጥራቸው በርከት ያሉ መምህራንን የመሸለም እና ዕውቅና የመስጠት መርሃ-ግብር ነበር:: በዚህ ፕሮግራም፣ መምህራን ብዙ ጠብቀው የነበረ ቢሆንም መንግሥት ግን ለእነዚህ ለ35 እና ከዚያ በላይ በመምህርነት ላገለገሉ፣ ብዙ ሺህ ኢትዮጵያኖችን በዕውቀት ለቀረጹ፣ እጅግ በርካታ ሙያተኞችን ላፈሩ መምህራን ሜዳሊያ እና 1000 ብር ብቻ «እየሸለመ» መልሷቸዋል:: እስኪ ይታያችሁ፣ ለዚህ ክቡር ሙያ ባለቤቶች፤ ያውም 35 ዓመት + ሀገራቸው የጣላችባቸውን ተተኪ ትውልድ የማፍራት አደራን ለተወጡ መምህራን 1000 ብር መስጠት ምን ይባላል?!

አባቴ ስለ መምህርነት ሲያጫውተኝ፣ «ትልቁ እርካታዬ ያስተማርኳቸው ልጆች ትልቅ ቦታ ደርሰው ስመለከት ነው» ይለኝ ነበር:: ስሜቱ ለብዙ መምህራንም ተመሳሳይ ይመስለኛል:: ለጊዜው መምህራን ከሥራቸው የሚያገኙት እርካታ፣ የሥራቸውን ፍሬ እያዩ በመደሰት ተወስኗል:: ነገር ግን፣ ይህ ሁኔታ በአስቸኳይ ሊቀየር ይገባዋል:: መንግሥት መምህራን እያበረከቱት ላሉት ታላቅ ሀገራዊ አስተዋጽኦ፣ ተገቢውን ክፍያ የሚያገኙበትን መንገድ በአፋጣኝ ማስተካከልና ከክፍያ ጋር የተያያዘውን ችግራቸውን የመፍታት ግዴታ አለበት:: መምህራን ይህንን ክቡር ሥራቸውን በአግባቡ መሥራት እንዲችሉ ምቹ ሁኔታ ከቃላት ባለፈ ሊፈጥርላቸው ይገባል::

እኔም፣ የመምህራን ለሀገር ዕድገት ለሚያበረክቱት ጉልህሚና መመስገን፣ ዕውቅናማግኘትና መከበር ይገባቸዋል እላለሁ:: እስከዛሬ ድረስ መንግሥት ለፕሮፖጋንዳ የሚያውለውን «ክብር ለመምህራን» በሚሉ ባዶ ቃላቶች ሳይሆን የመምህራንን ጥያቄ በአግባቡ እና በአፋጣኝ በመመለስ ተግባራዊ ክብር እንዲሰጣቸው እጠይቃለሁ::

ቃለ - ምልልስ

<<የኢሕአዴግ የፍትሕ ሥርዓት አስመሳይ ስለሆነ፣ በውስጡ ላሉት ሁሉ አስጨናቂ ነው>>

ተማም አባቡልጉ /ጠበቃ/

የ<<አዲስ ገጽ>> መጽሔታችን የመጀመሪያው እንግዳ፣ አንጋፋው የሕግ ባለሙያው ጠበቃ ተማም አባቡልጉ ናቸው። ጠበቃ ተማም፤ በርካታ የወንጀል፣ የሽብር፣ የጋዜጠኝነት …ወዘተ ክሶችን ለደምበኞቻቸው በመያዝ በፍርድ ቤት በመሟገት እና ሀሳቦቻቸውን በሕትመትና በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች በድፍረት በመግለጽ፣ ብሎም በተለያዩ በተጋበዙባቸው መድረኮች ላይ ጥናታዊ ጽሑፎችን በማቅረብ ይታወቃሉ። ባለፈው ዓመት የቀረበባቸውን ክስ ተከትሎ ግን፣ ፍትሕ ሚኒስቴር የጥብቅና ፍቃዳቸውን ለአንድ ዓመት ከሰባት ወራት ያህል ማገዱ የሚታወስ ሲሆን በእግዱም ላይ ይግባኝ ጠይቀው ጉዳያቸውን በአሁን ወቅት እየተከታተሉ መሆናቸውን ይገልጻሉ። የ<<አዲስ ገጽ>> ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ ኤልያስ ገብሩም ከጠበቃ ተማም አባቡልጉ ጋር በበሀገራችን ታሪካዊ እና ወቅታዊ የሕግ ነክ ጉዳዮች ዙሪያ፤ በሁለት ዕትም የሚጠናቀቅ ሰፋ ያለ ቃለ ምልልስ አድርጓል። የመጀመሪያው ክፍልም እንዲህ ቀርቧል - መልካም ንባብ!

> አሁን ላይ የባለሙያነት ባህሪ እምብዛም አይታይም። ይህ ማለት የተወሰኑ ሰዎች የሉም ማለት ሣይሆን በአብዛኛው <<በምን አገባኝ>> ስሜት ተይዞ መንግሥትን ለማስደሰት የቆመ ሲሆን ለራሱም ሆነ ለህዝቡ መብት ያለምንም ይሉኝታ ትንሽም ለመቆም ፍቃደኝነት የጐደለው ሆና መገኘቱን ለማመልከት ነው።

ጥያቄያችንን «የሕግ ሥርዓት ማለት ምን ማለት ነው?» ከሚለው ብንጀምርስ …?

ደህና፣ የፍትሕ ወይም የሕግ ሥርዓት ማለት፣ የፍትሕ አካላት የሚባሉት ፍርድ ቤት፣ ዐቃቤ ሕግና ፖሊስ ሥራቸውን ለየብቻቸውና በቅንብር (በሥርዓት) እንዴት እንደሚሰሩ የሚመለከተው ነው:: «ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዴት ይወጣሉ?» የሚለውን ይመለከታል::ፖሊስ ተጠርጣሪን ከንፁህ ዜጋ ለይቶ ይዞ፣ ምርመራ አጣርቶ፣ ለዐቃቤ ሕግ ልኮ፣ አስከስሶ ፍ/ቤትም ይሄንኑ ተቀብሎ ከውሳኔ የሚደርስበትን አጠቃላይ አካሄድና አሠራር የሚመለከት ነው::

«እነዚህ ሥራቸውን እንዴት ይሠራሉ? በምን ወይም በማን ይሠራሉ?» …ወዘተ የሚለውንና በሕግ የተቋቋመበትን ሁኔታ፤ በሕግ ያላቸውን ሥልጣንና ተግባር፣ ያንን እንዴት ይወጡ መባላቸውንና በተግባር በመሬት ላይ ደግሞ «ይህንን ሥልጣናቸውን እንዴት ይወጣሉ?» የሚለውን የሚመለከት ነው:: ለምሣሌ፣ በሕግ ለፖሊስ የዘፈቀደ እስራትና ሰውን ደብድቦ ማስረጃ የማግኘት ሥልጣን ተሰጠ/ አልተሰጠ በተግባር ያ የሚቻል ከሆነና በዚህ መልኩ ተይዞ ማስረጃ የተሰበሰበበት ሰው በዚህ ማስረጃ ፍ/ቤት ጥፋተኛ ካለው፣ ይህ ሁኔታ የዘወትር ድርጊት ከሆነ ወይም ከተደረገ፤ የፍትሕ ሥርዓቱ «አንድን ዜጋ በዘፈቀደ አስሮ እና ደብድቦ በሚገኝ ማስረጃ መሠረት የሚሰራ ነው» ተብሎ ይወሰዳል::

በአጠቃላይ፣ የፍትሕ ሥርዓት ማለት «እነዚህ የፍትሕ አካላት ሥራቸውን በግልጽ እና በጋራ እንዴት ይወጣሉ?» የሚለውን ይመለከታል :: እነዚህ አካላት ያላቸውን መዋቅራዊ ነፃነት፣ በሰለጠነና ለሙያው አስፈላጊ የሆነ የሙያና የሥነ-ምግባር ብቃት ባለው ባለሙያ መመራታቸውንም ይመለከታል:: ተቋማዊ ነፃነት በሕግም በተግባር ያላቸው መሆኑንና ወገንተኝነታቸውንም ይመለከታል::

የኢትዮጵያን የሕግ ሥርዓት፣ ካለፉት ሥርዓታት (የዘውዳዊው እና ደርግ) እንዲሁም አሁን ካለው ኢህአዴግ አኳያ እንዴት ይገልጹታል?

የኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ከአጼ ኃይለስላሴ የ1931 ዓ.ም ሕገ-መንግሥት ጀምሮ ብንመለከት ሁሉም ማለት ይቻላል፣ የሕግ የበላይነት አልነበራቸውም:: የነበረው «በሕግ መግዛት» የሚባለው ነው:: ኃይለስላሴ ሕገ መንግሥቱንና ሕጐችን የሰጡት፣ ለሚወዱትና ለሚወዳቸው ሕዝባቸው ሲሆን ይህም ያላቸው ፍቃድ (መሻት) ሕዝብ እንዲተዳደርበት ለማድረግ ያሻቸውን ያሉበት ነው::

ዝርዝር ሕጐቹ፤ የፍትሐብሔር፣ የወንጀል ሕጐችና የሥነ-ሥርዓት ሕጐቹ ከፈረንሳይና ከሌሎች ሀገሮች ስለተቀዱ ዘመናዊ የሚባሉ ነበሩ:: እነዚህ ሕጎች፣ በሕግ ሰጪው ፀሐዩ ንጉሥ ላይ አይሰራም:: ይህ በሕግ (dejure) የተቀመጠ፣ በተግባርም (defacto) የሚፈፀም ነው::ማታለል የለበትም:: ሉዓላዊ አካል (የሕጉ፣ የሀገሩና የመንግሥቱ ባለቤት) ንጉሠ ነገሥቱ ናቸው::በደርግ ጊዜም ደርጉና ሸንጎው ነበሩ:: በኢሕአዴግም የ1987 ዓ.ም ሕገ መንግሥት አንቀፅ 8 ላይ «ሉዓላዊው አካል ሕዝቡ ነው» ቢባልም በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 50 ላይ የሕዝብ ወኪል ተብሎ ከተቀመጠው የመንግሥት አካል ከሆነው ከሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጋር በማቀራረብ የሕዝቡን ሥልጣን ለእሱ በመስጠት በተግባር ፓርላማው ህዝቡን፣ አስፈፃሚው ፓርላማውን፣ ፓርቲው አስፈጻሚውን ተክተው እንዲገኙበት የተደረገበት ሁኔታ ስላለ (ስለተፈጠረ) በሕገ መንግሥት ላይም ሆነ በተግባር የሕግ የበላይነት፤ የመንግሥት ሶስቱ አካላት በግልጽ የተቀመጠ የሥልጣን ክፍፍልና ተጠባብቆ የመሥራት መርህ ስለሌለ በተግባር ሥልጣን በተወሰነ አካል እጅ ተጠቃልሎ በመግባት ሁሉም የዚህ አካል አገልጋዮች ስለሚደረጉ፣ ወይም ስለተደረጉ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና የዜጎች መብቶችና ነፃነቶች የመከበር ሁኔታ ሊፈጠር አልቻለም፣ አይችልም::

እንዴት ማለት?

ከመዋቅራዊ ነጻነት ጀምሮ፣ በተወሰነም ደረጃ በያዙት ጉዳይ ላይ ባለቤት ሆኖ ከመገኘት አንጻር ስንመለከትው፣ አሁን ያለንበት ጊዜ ዝቅተኛው ነው:: «የድሮ ዳኛ፣ የድሮ ዐቃቤ ሕግና ፖሊስ» ስንል በኃይለስላሴና ደርግ ጊዜ ከነበረው ማወዳደር ይቅርና እኔ ሥራ በጀመርኩበት ጊዜ የነበረውና ዛሬ ያለው እንኳን አይወዳደርም::

ከምን አንጻር?

በቀደም ሲል፣ የዳኛ ውሳኔ ይከበር ነበር:: ዐቃቤ ሕግ ለሕግ የመቆምና «የማይሆኑ ክሶችን አላቀርብም» የማለት ሁኔታ ነበር:: ፖሊስም በተወሰነ ደረጃ ሕግንና የፍ/ቤትን ውሳኔ ያከብር ነበር:: ይህ ማለት ግን በኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት የነበረበት ወቅት ነበር ማለት አይደለም:: እስከአሁን ያለው ሁሉ አገዛዝ ስለሆነ በሕግ መግዛት ነው የነበረው:: እየተነጋገርን ያለነው በዝርዝር ደረጃ በአንጻራዊነት ባለሙያውና ሙያው ሥራቸውን ሲከውኑ ስለሚያሳዩት ባህሪ ነው:: አሁን ላይ የባለሙያነት ባህሪ እምብዛም አይታይም:: ይህ ማለት የተወሰኑ ሰዎች የሉም ማለት ሣይሆን በአብዛኛው «በምን አገባኝ» ስሜት ተይዞ መንግሥትን ለማስደሰት የቆመ ሲሆን ለራሱም ሆነ ለህዝቡ መብት ያለምንም ይሉኝታ ትንሽም ለመቆም ፍቃደኝነት የጐደለው ሆኖ መገኘቱን ለማመልከት ነው::

በኢህአዴግ ውስጥ ያለውን የፍትህ ሥርዓት (በአጠቃላይ) በዘርፉ ለረዥም ዓመት እንደመስራትዎ መጠን እንዴት ገመገሙት?

የኢሕአዴግ የፍትሕ ሥርዓት አስመሳይ ስለሆነ በውስጡ ላሉት ሁሉ አስጨናቂ ነው:: ደርግ በሥልጣኑ ላይ የመጡበትን ለማስወገድ ሕግን አይጠቀምም:: ኃይለስላሴም ሰው በቀላሉ ሥልጣናቸው ላይ የማይመጣው ንጉሥ ስለሆኑ፣ ሲሆን ከመጣባቸውም መክረው ካልሆነም በማጋዝ …ወዘተ በሕግና ያለሕግ ያስወግዱታል:: በዚህ ረገድ እሳቸውም አስመሣይነት ነበረባቸው:: ሀገሪቱ ከነበረችበት የሕዝብ የንቃት ሕሊና ዕድገት ደረጃና ስለሕግ የበላይነት ከነበረው ዓለም አቀፍ አመለካከት የተነሳ፣ ይህ ሁኔታ በግልፅ እንዲታይና የዘወትር ተግባር መሆኑ ይፋ እንዲወጣ አልተደረገም:: አስገዳጁ ሁኔታ አልተፈጠረም::በኢህአዴግ ጊዜ ግን ድርጅቱ ራሱ «ዴሞክራሲያዊ ነኝ» በማለቱና ወቅቱም የመረጃ ዘመንና ዓለምም በአንድ ጎራ ስር ሆና ዴሞክራሲ፣ የሕግ የበላይነት፣ የመሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች መከበር የሚሰበክበት ስለሆነ፣ ኢሕአዴግ በባህሪው እነዚህን ለማስከበር ስለማይፈልግ፣ ሥልጣን ወዳጅና አድኋዊ ስለሆነ በወረቀት ላይ በጻፋቸው ሕጐች መሠረት ለመስራት አልተቻለውም:: ይህ ማለት ግን፣ የጻፋቸውም ሕጎች ምርጦች ናቸው ማለት አይደለም:: ቢሆንም በእነሱም መሠረት ቢሰራ ወይም እነሱንም ቢተረጉም የፈለገው እንደማይሆን ስለገባው ሁሉም በአፍ ስለሕግ የበላይነት እየሰበኩ፣ በሕግም ያለሕግም በትርጉም ስም ዋናው ቁምነገሩ ያ ባለመሆኑ ይህን ሁኔታ ሰጥቶ ከመንሳት ጋር ልናመሳስለው እንችላለን:: ፍ/ቤቱ በተግባር ከፖለቲካ ነጻ ሆኖ በሕግና ሕግ ብቻ በገለልተኝነት እንዲሠራና ከሚሰጠው ውሳኔ ውስጥ የግሉ ፍላጐት እንዳይኖር በማድረግ ገለልተኛ ማድረግ የሚቻለው በሶስቱ የመንግሥት የሥልጣን አካላት መካከል ግልፅ የሆነ የሥልጣን ክፍፍል በማስቀመጥ ተጠባብቀው እንዲሰሩም (cheak and balance) በማድረግ ሲሆን፤ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ (ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ እስከአሁን ስላልመጣ) የሚሆነው ሁሉ ከቃላት ጨዋታ አያልፍምና ነው እየሆነ ያለው::

በተናጠል (የዳኝነት፣ የዐቃቤያን ሕግ፣ የጠበቆችንና የፖሊስን) ትክክለኛ ሚና አሁን ላይ ከሚታዩት ነባራዊ እውነታዎች ጋር እየተመለከቱ ቢስረዱን?

የፖሊስ፣ የዐቃቤያን ሕግ፣ የጠበቆችና የዳኞች

የእሱን ያልተጻፈ ፍላጎት እንዲያስጠብቁ ለማድረግ እየሰራ ስለሚገኝ፣ በተለይ ከ1997 ዓ.ም በኋላ ሁሉም የፍትሕ አካላት ለዚህ ግልጋሎት የማይውሉትን ሁሉ ለመከርከም ዓላማ እንዲውሉ ተከርክመዋል:: ይህም በ1983 ዓ.ም የተበጀውን ሥርዓት ላበጀው ብቻ እንዲያገለግል አንሶ ከመሆኑ በተጨማሪ ነው::

ከመንግሥት አካላት መካከል አንዱ ሕግ ተርጓሚው ነው። ይሄ አካል ከማንም ተጽዕኖ ነጻ ሆኖ እንደሚሰራ በሕገ-መንግሥቱ ተደንግጓል። ሕግ ተርጓሚው ግን፤ በአስፈጻሚው አካል ቁጥጥር፣ ትዕዛዝና ተጽዕኖ ስር መውደቁ በተደጋጋሚ በኢትዮጵያ ምድር የሚሰማ ሀቅ ነው። እርስዎስ በዚህ ሀሳብ ይስማማሉ?

ሕግ ተርጓሚው ነጻ ሆኖ ስለመስራቱ መደንገጉ ሳይሆን፣ እንዴት ነጻ መሆን እንዳለበት መደንገጉ ነበርና ተገቢ ሚና፤ የሕግ የበላይነት በተጠበቀበት ሥርዓት፣ አካሄድን ከውጤቱ እኩል በመቀበል እየሰሩ ሥርዓቱን በማበልጸግ ፍትሐዊ ማኅበረሰብን ፈጥሮ ማስቀጠል ሲሆን በሕግ በሚገዛበት በሶሻሊስትና በሌሎች ፈላጭ ቆራጭነት ሥራ ይህንኑ ለማስቻል መስራት ወይም በእኛ ሀገር አስመሳይ ሁኔታ ሥር ደግሞ የተባለው እንዲሆን፣ የተጻፈው እንዲተረጎም (ለነጻነትና ለሕዝብ) መቆም የፈለገው ቢሆን ተቀብሎ ጨለማን ለማስፋፍት መስራት ናቸው:: የተቀረው ዝርዝር አፈጻጸም ብቻ ይሆናል::

በዛሬዋ ኢትዮጵያ ነጻ ሕጋዊ የፍትሕ ሥርዓት አለ ማለት ይቻል ይሆን?

በዛሬዋ ኢትዮጵያ ነጻ ሕጋዊ የፍትሕ ሥርዓት የለም::

እንደጠበቃነትዎ በርካታ የወንጀል፣ የሽብር፣ የጋዜጠኝነት

ወደ ገፅ 14 ይዞራል

> “
>
> እነአቡበከር የሕዝብ ተወካይ ሆኑ /አልሆኑ፣ ፈጸሙት የተባለው ጉዳይ እንኳን በሽብር ቀርቶ በወንጀል የማያስጠይቅ፣ የተፈቀደ ሕገ-መንግሥታዊ መብት ሲሆን አቀራረቡም ፍጹም ሕጋዊ፣ ሠላማዊና የሰለጠነ ነው።

ኤድመን ተስፋዬ

ለነፃነት እና ለዕውቀት ትኩረት ያልሰጠ ሥርዓት በኢኮኖሚያዊ ዕድገት የብዙሃኑን ኑሮ ሊያሻሽል አይችልም!

ክፍል ፩

መነሻ

ዕውቁ ህንዳዊው ፈላስፋ ኦሾ፣ ከደቀመዝሙሩ አንዱ ስለ ምክንያታዊነት በጠየቀው ጊዜ፤ ምክንያታዊነትን ከዕውቀት እና ከማሰብ ጋር በማዛመድ ሲመልስ «አንድ ሰው የሚያመዛዝን ጭንቅላት ይዞ ምክንያታዊ መሆን ሲያቅተው እንዳይገርማችሁ! ምክንያቱም ይህ ሰው ምክንያታዊ በሆነ ዕውቀት መኖር ያቃተው ሰው የሚለውን መጠሪያ የወሰደ እንስሳ ነውና» በማለት ነው::ዕውቁ ዘመን ተሻጋሪ ኢኮኖሚስት አማርታሲያን ሴን ስለምርታማነት እና ስለኢኮኖሚ ዕድገት በሚተነትኑት ፅሁፎቹ፣ ብዙውን ጊዜ ለምርታማነት ምክንያት ከሆኑት ውስጥ አንዱ በሆነው የሰው ሀይል ላይ በተለየ ትኩረት በማድረግ የሰው ሀይል ለምርታማነትም ሆነ ለኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ ሚና እንዳለው የኢኮኖሚክስ ኖቤል ሽልማት ባገኘበትም ሆነ በሌሎች ፅሁፎቹ ይናገራል::

እንደ ሴን መከራከሪያ «የሰው ሀይል ለምርታማነትም ሆነ ለኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ ሚና አለው» ሲባል ዋነኛው ምክንያት ጉልበቱ ሳይሆን ማሰብ መቻሉ ነው:: የማሰብ ፀጋውን ደግሞ ለምርታማነትም ሆነ ለኢኮኖሚ ዕድገት በግብዓትነት ለመጠቀም የማሰብ ነፃነት ያስፈልገዋል:: ይህም ማለት ነፃነት ያለው ዕውቀት (በዚህ ፅሁፍ እውቀት ሲባል በትምህርት የሚገኘውንም ሆነ ከባህል፣ ከኑሮና ከአካባቢ የሚገኘውን አካባቢያዊ (Indeginious) እውቀት ያካተተ ስለመሆኑ አንባቢ ሊገነዘበው ይገባል) ለምርታማነትም ሆነ ለኢኮኖሚ ዕድገት ዋነኛው ቅድመ ሁኔታ ነው እንደማለት ነው::

ይህን የሴን መከራከሪያ ነበራዊነት ለማረጋገጥ፣ በምንገኝበት የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ባደጉትም ሆነ ባላደጉት ሀገራት መሀከል ለኢኮኖሚ አቅም ልዩነት ዋነኛው ምክንያት የሆነውን ፈጠራ (መቼስ ፈጠራ ዕውቀት-መር በሆነ ማሰላሰል የሚከወን እንጂ ከሰማይ የሚወርድ አለመሆኑ ግልፅ ነው) በማሳየት ማቅረብ የሚቻል ይመስለኛል:: ከላይ ከተጠቀሰው የኦሾ እና የሴን ንድፈ ሀሳብ በተጨማሪ ነፃነት ያለው ዕውቀት ቀጣይነት ላለው ሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ዋነኛው ምክንያት ስለመሆኑ ነበራዊ ማስረጃ የጀርመን ኢኮኖሚ ነው::

ጀርመን ከሁለተኛው የአለም ጦርነት ማክተም በኋላ፤ ሰው በላው መሪዋ ሂትለር በተለያዩ የዓለም ሀገራት ላይ በከፈተው ጦርነት የተነሳ የሀገሪቷን የሰው ሀይልም ሆነ ቁሳዊ ሀብት አድቅቆት እንደነበር የኢኮኖሚ ታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ:: ጦርነቱ ካለቀ በኋላ ያሉት አስር እና አስራ አንድ ዓመታት የጀርመን ህዝብ በአብዛኛው መሠረታዊ የምግብ ፍላጎቱን እንኳ በበቂ ሁኔታ ሟሟላት አቅቶት የሚታትርበት ወቅት ነበር:: ከስድስት አስርተ ዓመታት በኋላ ግን አሁን ላይ የጀርመን ኢኮኖሚ ከዓለማችን ግዙፍ ኢኮኖሚ ካላቸው ሀገራት አንዱ በመሆን የአውሮፓን ኢኮኖሚ በበላይነት ይመራል:: ለዚህ ኢኮኖሚያዊ ስኬት ደግሞ ዋነኛው ምክንያት ሀገሪቷ ለዜጎቿ ነፃነት እና ዕውቀት የሰጠችው ትኩረት ሲሆን፣ ይህ ትኩረቷም በአንድ በኩል ኢኮኖሚውን ለሚመሩት ነፃ እና ገለልተኛ ተቋማት መፈጠር መንስኤ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ኢኮኖሚውን የሚመሩት ነፃ እና ገለልተኛ ተቋማት ፈጠራን ማዕከል ያደረገ ቴክኖሎጂ ለሀገሪቷ ኢኮኖሚ መሰረት እንዲሆን መንስኤ በመሆናቸው ነው::

> ለኢኮኖሚ ዕድገት ዋናው መንስኤ ምርታማነት ሲሆን ለምርታማነት ምክንያት ከሆኑት ውስጥ አንዱ የሰው ሀይል ነው፡፡ የሰው ሀይልን ለምርታማነት መንስኤ እንዲሆን ያደረገው ጉልበቱ ብቻ ሳይሆን ከጉልበቱም በላይ የማሰብ ተሰጥኦው ነው፡፡ ለምርታማነት መንስኤ የሆነው የሰው ሀይል የማሰብ ሀይሉን አበልፅጎ ለምርታማነት ምክንያት እንዲሆን ዋነኛው ግብአት ደግሞ ነፃነት ነው፡፡

ከላይ የጠቀስኳቸው የኦሾ እና የሴን ንድፈ.ሀሳቦችን ከጀርመን ሀገር የኢኮኖሚ ተሞክሮ ጋር ስንገምደው፤ እንደእኔ ዕምነት ነፃነት ያለው ዕውቀት በግለሰብ ነፃ ለሆኑ ኅብረተሰቦች እንቅስቃሴ መፈጠር መንስኤ በመሆን ኢኮኖሚን ፈጠራን ማዕከል ባደረገ የቴክኖሎጂ መሰረት ላይ በመገንባት ቀጣይነት ባለው የኢኮኖሚ ዕድገት የብዙሃኑን ኑሮ ለማሻሻል መንስኤ እንደሚሆን የሚያመላክት ይመስለኛል:: ይህም ገዢው ፓርቲ የሚከተለውን ኢህአዴግአዊ ልማታዊ መንግስት መርህ ከገዢው ፓርቲ ፖለቲካዊ ባህሪ ጋር በመገመድ ይህንንም ለፖለቲካ ፍጆታ ሳይሆን ከላይ ለጠቀስኩት አይነት ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መንስኤ ለሚሆን ነፃነት እና ለዕውቀት ገዢው ፓርቲ ያለውን አቋም ማመላከቻነት በመውሰድ ገዢው ፓርቲ የሚለፍፍለትን ተከታታይ የኢኮኖሚ ዕድገት ነባራዊነት ለመፈተሽ የሚያስችል ይመስለኛል::

ነፃ የሆኑ ኅብረተሰቦች እንቅስቃሴ ነፃነት እና ዕውቀት ቀጣይነት ላለው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ቀብድ ስለመሆኑ እንደማሳያ?

ዕውቁ ኢኮኖሚስት ዳግላስ ኖርዝ የአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ ብልፅግናም ሆነ ቀውስ ከሀገሪቱ ተቋማዊ ጥንካሬ ጋር የተገናኘ ስለመሆኑ በመግለፅ አብዛኛዎቹ ደሃ ሀገራት የድህነት መንስኤ ከገነቡት ተቋም ጥንካሬ ጋር የተገናኘ ስለመሆኑ ይተነትናል:: እንደ ኖርዝ ሁሉ የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ጋናን በጎበኙበት ወቅት አፍሪካ የማያስፈልጋትም ሆነ ያጣችው ጠንካራ ግለሰብ ሳይሆን ጠንካራ ተቋም ስለመሆኑ በመግለፅ ለአፍሪካ ሀገራት ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግር መፍትሄው ጠንካራ ተቋም መገንባት ስለመሆኑ አፅንኦት በመስጠት ተናግረዋል:: በምንገኝበት የሀያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የተቋማት ሚና ለሀገር ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግር መፍትሄ ከመሆናቸው ጋር በቀጥተኛ ሁኔታ ተገናኝ በሆነ መልኩ የሚታይ ሲሆን፣ ይህ የተቋማት ሚና ስኬት ደግሞ ተቋሙን በሚመሩት እና በሚያንቀሳቅሱት ግለሰቦች ላይ የተንጠለጠለ ነው::

ያደጉ ሀገራት ታሪክ እንደሚያሳየን ከሆነ፣ ምሁራን በዕውቀት የዳበረ ግለሰብ በመፍጠር፣ ከድህነት ለመውጣት መሳሪያ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በመፍጠር፣ ሕግ እና ደንብን አክብሮ የሚሄድ ተቋምን በመገንባት ለሀገራቸው ማኅበረሰባዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከፍተኛ ሚና መጫወታቸውን ነው:: በዚህ ረገድ ለሁለተኛው ዓለም ጦርነት መንስኤ በሆነው ሂትለር ስትመራ የነበረችው ጀርመን በሂትለር አመራር በገባችበት ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ቀውስ በአጭር ጊዜ ሀገራዊ አንድነቷን በጠበቀ መልኩ ኢኮኖሚዋን በጠንካራ መሰረት ላይ በመገንባት የአውሮፓ ግዙፍ ኢኮኖሚ ለማድረግ ምሁራን የተጫወቱት ሚና የሚጠቀስ ነው:: ምሁራን ለሀገር ኢኮኖሚ የሚጠበቅባቸውን ሚና ለመወጣት አካዳሚካዊ ነፃነት እና ከፖለቲካዊ ተፅዕኖ መውጣት ያለባቸው መሆኑን በመጥቀስ፣ ምሁራኑ ለሀገራቸው የሚያበረክቱት ሚና አሉታዊውም ሆነ አዎንታዊው ውጤቱ በመንግሥታዊው ሥርዓት ላይ የተንጠለጠለ ስለመሆኑ በጉዳዩ ዙሪያ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይናገራሉ::

ነፃነት እና ዕውቀት ቀጣይነት ላለው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ቀብድ ስለመሆናቸው የኢኮኖሚክስ ንድፈ ሀሳቦችንና የዓለማችን ዕውቅ ኢኮኖሚስቶችን ዘመን ተሻጋሪ የንድፈ ሀሳብ ትንተናዎች መነሻ አድርጎ ማየቱ ተገቢ ይመስለኛል:: በኢኮኖሚክስ አስተምህሮት ንድፈ ሀሳቦችም ሆነ በኢኮኖሚስቶች ንድፈ ሀሳብን ከሀገራት ኢኮኖሚያዊ ሁነት ጋር ተዛምዶ በቀረቡት እልፍ ጥናቶች ውስጥ ነፃነት እና ዕውቀት ቀጣይነት ላለው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ቀብድ ስለመሆናቸው ብዙ ማሳያዎች እና ክርክሮች ቀርበዋል፤ እየቀረቡም ነው:: ነፃነት እና ዕውቀት ለኢኮኖሚ ዕድገት ቀብድ ስለመሆናቸው ከሀገራችን ነባራዊ ሁነት አኳያ ለማየት፣ እንደእኔ እምነት ነፃ የሆኑ ኅብረተሰቦች እንቅስቃሴ ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚኖረውን ሚና ከዴሞክራሲያዊ መንግሥታዊ ሥርዓት ጋር በመገመድ ማየት አስፈላጊ ይመስለኛል::

የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን አይነት ወደ ጎን ትተን በሁሉም ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ የነፃነት መገለጫን ስናይ፣ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዋነኛ ማዕከል የብዙሃኑ ፍላጎት የሚገዛበት ሆኖ፣ በየትኛውም አይነት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ጥበቃ የሚደረግላቸው መብቶች ውስጥ የግለሰቦች የመፃፍ፣ የመናገር፣ በነጻነት የመደራጀት፣ ያለምንም ገደብ የመንቀሳቀስ፣ እንደ ግለሰብ የፈለገውን እምነት የማመን፣ በተመቸው ቋንቋ የመናገር፣ እንደ ግለሰብ የራስን ህይወት ለማሸነፍ የሚደረግን እንቅስቃሴ አለማስተጓጓልን፣ እንደ ግለሰብ ጥሮ ያፈራውን ንብረት ያለመነጠቅ፣ በአጠቃላይ ለዜጎች የተሰጡ መብቶችን ሳይነኩ በግለሰቡ፣ በልጁ፣ በአጠቃላይ በቤተሰቡ ጉዳይ ላይ ውሳኔ የመስጠት መብቱን፣ በአንድ ወቅት በብዙሃኑ ድምፅ ተበልጠው አናሳ አመለካከት የያዙ ሰዎች፣ እነኝህን መብቶች ተጠቅመው አመለካከታቸውን የብዙሃኑ ለማድረግ የመሞከርና በሕግ በተቀመጠው የምርጫ ሥነ-ሥርዓት ተጠቅመው የቀድሞውን የብዙሃን መንግሥት ቀይረው እነሱ ብዙሃን የመሆን ሙከራ የማድረግ መብቶች ናቸው::

> በእኔ እምነት፣ የኢኮኖሚ ዕድገት ሊኖርየሚችለውዕውቀትምነፃነትም ባላቸውነፃበሆኑኅብረተሰቦችየጋራ እንቅስቃሴ መንስኤነት የመሆኑን እውነትነት ሲረጋገጥ ነው፡፡

በተጨማሪም በየትኛውም አይነት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ጥበቃ የሚደረግላቸው መብቶች ውስጥ በፈቃደኝነት የተመሰረቱ የወል ስብስቦች (የኃይማኖት፣ የብሄር፣ የባህል፣ የሙያ ስብስቦች ...ወዘተ) በአጠቃላይ የማኅበረሰቡን እና የሌሎች ዜጎችን መብቶች በማይነካ መልኩ እስከተደራጁ ድረስ የጋራ ጉዳያቸውን ያለማንም ጣልቃ ገብነት ያለማካሄድ.ባህላቸውንና ዕምነታቸውን የመከተል እና በፍቃደኝነት የሚቀበላቸውን እስካገኙ ድረስ የማስፋፋት፣ የውስጥ ጉዳያቸውን የሚያካሂዱበትን የራሳቸውን ሕግ እና መዋቅር የመዘርጋት፣ በሚመቻቸው መንገድ ተደራጅተው በጋራ በተቀመጠው ሕግ መሠረት የጋራ ጥቅሞቻቸውን ለማስጠበቅ የመንግሥትን የጋራ ውሳኔ ለማግባባት መሞከርን፣ በተቀመጠው ሕግ መሠረት አቤቱታ የማቅረብ፣ በአደባባይም ተቃውሞ የመግለፅ መብቶችን ያካትታል::

ለኢኮኖሚ ዕድገት ዋናው መንስኤ ምርታማነት ሲሆን ለምርታማነት ምክንያት ከሆኑት ውስጥ አንዱ የሰው ሀይል ነው:: የሰው ሀይልን ለምርታማነት መንስኤ እንዲሆን ያደረገው ጉልበቱ ብቻ ሳይሆን ከጉልበቱም በላይ የማሰብ ተሰጥኦው ነው:: ለምርታማነት መንስኤ የሆነው የሰው ሀይል የማሰብ ሀይሉን አበልፅጎ ለምርታማነት ምክንያት እንዲሆን ዋነኛው ግብአት ደግሞ ነፃነት ነው::

የሰው ልጅ ያለማንም ተፅዕኖ የማሰብ ነፃነቱ ሲዳብር አዳዲስ ሀሳቦችን የማፍለቅ ችሎታው፣ አዳዲስ አሰራር የመጠቀም ድፍረቱ በአጠቃላይ ለምርታማነት ያለው ተነሳሽነቱ ይዳብራል:: በሌላ አነጋገር፣ ለኢኮኖሚ ዕድገት መንስኤ ይሆናል እንደማለት ሲሆን፣ ይህም ከምንም በላይ የሰው ልጅ ተፈጥሮ በራሱ ዴሞክራሲን እና የኢኮኖሚ ዕድገትን አንድ ላይ ለማስኬድ እንጂ የኢኮኖሚ ዕድገትን በማስቀደም «ዴሞክራሲን በኋላ» በሚል ንድፈ ሀሳብ ምቹ ስለአለመሆኑ አሳይ ከመሆኑም በላይ «መጀመሪያ ድህነትን እንቅረፍ! ዴሞክራሲ በሂደት የሚመጣ ነው» የሚለው ብሂል የአንባገነኖች መቆመሪያ ስለመሆኑ አሳይ ነው:: ከምንም በላይ ደግሞ በእኔ እምነት፣ የኢኮኖሚ ዕድገት ሊኖር የሚችለው ዕውቀትም ነፃነትም ባላቸው ነፃ በሆኑ ኅብረተሰቦች የጋራ እንቅስቃሴ መንስኤነት የመሆኑን እውነትነት ሲረጋገጥ ነው::

በልማታዊ መንግሥት ንድፈ ሀሳብ ውስጥ ነፃነት እስከየት ይሄዳል?

በምድራችን ላይ የሚገኘው ሀብት ውስን (አላቂ) መሆኑ እና የሰው ልጅ ፍላጎት ገደብ አልባ መሆኑ ማንኛውም ሰው የፈለገውን ነገር በፈለገበት ሰዓት እና ቀን እንዳያገኝ ምክንያት ከመሆኑም በላይ ለየትኛውም ግለሰብም ሆነ ሀገር ትልቁ ፈተና ከእጥረት (scarcity) ጋር የተያያዘ እንዲሆን መንስኤ ሆኗል:: በሌላ በኩልም ማንኛውም ሰው የፈለገውን ነገር በፈለገበት ሰዓት እና ቀን አለማግኘቱ የተገደበ (ውስን የሆነውን) ገቢውን፣ ሰዓቱን እና ሀብቱን ቅድሚያ ለሚሰጣቸው መሠረታዊ ነገሮቹ እንዲያውል ያስገደደው ከመሆኑ ጋር በተያያዘ እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ሀገር ትልቁ ኢኮኖሚያዊ ዳራ በዋነኛነት ከእጥረት ጋር የተገናኘ ሆኗል::

ከላይ እንደጠቀስኩት፣ እንደሀገር ትልቁ የኢኮኖሚ ዳራ በዋነኛነት ከእጥረት ጋር የተገናኘ ቢሆንም በዓለም ላይ ያሉ ሀገራት ይህንን ዳራ በአንድ አይነት የኢኮኖሚ ሥርዓት ሳይሆን የሀገሪቱን ባህል፣ ሀብት (ቁሳዊም ሆነ ሰዋዊ)፣ ታሪክ ...ወዘተ ያገናዘበ የኢኮኖሚ ሥርዓት በመከተል ከእጥረት ጋር የተገናኘውን ኢኮኖሚያዊ ዳራ ለመወጣት እንደሞከሩ እና እንደሚሞክሩ የኢኮኖሚ ታሪክ ላይ ትኩረት ያደረጉ ኢኮኖሚስቶች ይናገራሉ:: ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ፣ ኢኮኖሚስቶች አራት አይነት (ባህላዊ፣ የእዝ፣ የገበያ መር እና ድብልቅ) የኢኮኖሚ ሥርዓት እንዳለ ስምምነት ላይ ቢደርሱም፣ ከእጥረት ጋር በተገናኘ ያለውን የኢኮኖሚ ዳራ ከመፍታት እና ከመቀነስ አኳያ «ከአራቱ የኢኮኖሚ ሥርዓት አይነቶች የትኛው ነው የተሻለው?» የሚለው ላይ አንድ አይነት አቋምም ሆነ ስምምነት የላቸውም::

የምድራችን ሀብት ውስን መሆኑና የሰው ልጅ ፍላጎት ገደብ አልባ መሆኑ መንግሥታት የህዝብን ኑሮ ለማሻሻል በሚል የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ዘለቄታዊ እና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ሊያመጣ የሚችለው ሀብቱ ከሚፈስበት የኢኮኖሚ ክፍል አኳያ የሚፈሰው ሀገራዊ ሀብት በአንድ በኩል ከወቅታዊው የሀገሪቷ ህዝብ ችግር አኳያ፣ ከዘለቄታዊ ጥቅሙ አኳያ በሌላ በኩል ለመጪው ትውልድ ያለውን ፋይዳ ለትውልዱ ከሚያስረክበው ትራፊ ሀገራዊ ሀብት አኳያ ያሰላሰለ ከሆነ ብቻ እንዲሆን መንስኤ ከመሆኑም በላይ በዚህ መንገድ ዘለቄታዊ እና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት የመምጣቱን ሁነት በመንግሥታዊ ሥርዓት ባህሪ ላይ የተንጠለጠለ እንዲሆን ምክንያት ሆኗል::

የልማታዊ መንግሥት ንድፈ ሀሳብ በዋነኛነትም ሆነ በቀጥታ ማዕከል የሚያደርገው መንግሥት በኢኮኖሚ ሥርዓቱ ላይ ባለው የቁጥጥር እና የተሳታፊነት ስፋት መጠን ላይ ብቻ ነው:: የልማታዊ መንግሥት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቃት በኋላ የጃፓን እና የምስራቅ ኤሽያ ሀገራት መንግሥታት በሀገራቸው ኢንዱስትሪን ለማስፋፋት የኢኮኖሚ ሥርዓቱን ተከላካይ በሆነ መልኩ በመምራትም ሆነ በኢኮኖሚ ሥርዓቱ ላይ ተሳታፊ በመሆን የአንበሳውን ድርሻ ከመውሰዳቸው ጋር እ.አ.አ የ1980 የላቲን አሜሪካ ሀገራት የብድር ቀውስ እና ከ1997 የምስራቅ ኤሽያ ሀገራት የገንዘብ ቀውስ፣ ከዓለም አቀፋዊነት መስፋፋት እንዲሁም ኢኮኖሚን ከማረጋጋት፣ ትምህርት፣ ጤናንና መሠረተ-ልማቶችን ከማስፋፋት አኳያ መንግሥት የሚኖረውን ሚና በተመለከተ በዋሽንግተኑ መግባቢያ ሰነድ ላይ የዕርዮተ ዓለም ልዩነት መኖሩ እና ተቀባይነቱ ከመቀነሱ ጋር በተያያዘ የልማታዊ መንግሥት ሥርዓት በ20ኛው ክፍለ ዘመን ዕውቅና ያገኘ ቢሆንም፣ ከልማታዊ መንግሥት ጋር አንድ አይነት የሆነ ሥርዓት ሆላንድን የመሳሰሉ የአውሮፓ ሀገራት በ17ኛው እና በ18 ክፍለ ዘመን ስለመተግበራቸው የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ:: ይህም የሚያሳየው፣ በእኔ እምነት፤ ልማታዊ መንግሥት በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የተጀመረ እንጂ አንዳንዶች እንደሚሉት እና እንደሚያምኑት የልማታዊ መንግሥትን ንድፈ ሀሳብ ኢህአዴግ የፈጠረው አለመሆኑን ነው::

ለኢኮኖሚ ዕድገት መንስኤ የሆኑትን መሰረተ ልማት ለማስፋፋት፣ መሰረታዊ የህዝቦችን ፍላጎት ለሟሟላት እንዲሁም ኢኮኖሚውን ከዓለም አቀፋዊ ክስተት እና አቻ ካልሆነ ውድድር ለመከላከል መንግሥት በኢኮኖሚው ላይ ተሳታፊ በሚሆንበት ልማታዊ መንግሥት ሥርዓት ስኬቱ እና ክስረቱ የልማታዊው መንግሥታዊ ሥርዓት ለመድብለ ፖርቲም ሆነ ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሁም ለነፃ እና ለገለልተኛ ተቋማት መኖር ከሚያበረክተው አስተዋጽኦ እንዲሁም ለግለሰቦች እንቅስቃሴ እና ዕውቀትን በነፃነት ለመጠቀም የሚያስችል ነፃነት በሥርዓተ ኢኮኖሚውም ሆነ በሥርዓተ ፖለቲካው ከማስፈኑ ጋር የተገናኘ ነው:: ለኢኮኖሚ ዕድገት፣ ለመድብለ ፓርቲም ሆነ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሁም ለነፃ እና ለገለልተኛ ተቋማት መፈጠር እና መጎልበት እንዲሁም በአስተማማኝ የኢኮኖሚ ዕድገት የህዝቡን ኑሮ ከማሻሻል ባለፈ ህዝቡ በፖለቲካ ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ልማታዊ መንግሥት ሥርዓት መንስኤ የመሆኑን እውነትነት የልማታዊ መንግሥትን መርህ በሚከተሉ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ባላቸው የተለያዩ ፖርቲዎች አሁን ላሉበት የኢኮኖሚ ደረጃ የደረሱትን የሆላንድንእናየጃፓንንታሪክበማሳያነትማቅረብይቻላል::

በክፍል ሁለት ፅሑፌ «ኢህአዴግአዊው ልማታዊ መንግሥት ለግለሰቦች ነፃ እንቅስቃሴ እና ዕውቀትን በነፃነት ከመጠቀም አኳያ ምቹ ነውን?» የሚለውን ጥያቄ ኢህአዴግአዊውን ልማታዊ መንግሥት መነሻ በማድረግ ከነባራዊው የሀገራችን የኢኮኖሚ አዙሪት አኳያ፣ ለግለሰቦች ነፃ እንቅስቃሴና ዕውቀትን በነፃነት ለመጠቀም ምቹ ሁኔታ በሌለበት ምኅዳር የኢኮኖሚው ዕድገት ሊኖረው ከሚችለው ቅርፅ አኳያ ለማየት እሞክራለሁ::

የኃይለማርያም ኑዛዜ

አብርሃም ፍቃደ

ኢትዮጵያውያን በባህላችን፣ እንደየነገዱ የተለያየ የኑዛዜ ሥርዓት አለን፡፡ ከዋነኞቹ መካከል አንድ ግለሰብ ጤነኛ በሆነበት ዘመኑ ወደፊት የሚባለው ጉድ ይዞ የሚመጣውን ነገር በመጠራጠር የሚከናወን የቅድመ-ጥንቃቄ ኑዛዜ አንደኛው ዓይነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የእርጅና በሮች ወደ መጃጀት ሲያቆበቁቡ እማኞች በተሰበሰቡበት የሚደረግ ሥርዓት ነው፡፡

አብዛኛው ጊዜ ሊያጋጥም የሚችለው የኑዛዜ ዓይነት ግን ሦስተኛው ነው፡፡ እሱም የሞት መላዕክቶች ነፍሳችንን ለመውሰድ ከስጋችን ጋር ግብግብ በሚገጥሙበት ወቅት ሰዎች ደግሞ በበኩላችን ንብረቱን ለመውረስ በምንጣደፍበት ቅጽበት ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ኢትዮጵያ በታሪኳ የማይዳሰስ ንብረትን፣ ቁጭትን፣ ህሊናዊነትን፣ ወይንም ሞራላዊነትን፣ ተናዝዘው ያለፉ ጀግኖች አሏት፡፡ ከእነዚህም መካከል የበላይ ዘለቀ እና የመንግሥቱ ነዋይ ኑዛዜ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በመንግሥት ደረጃ የኃይለስላሴ ኑዛዜ ተጠቃሽ ነው፡፡ ምናልባት መስማት ኖሮብን ካመለጡን ትልልቅ ኑዛዜዎች መካከል የ60ዎቹ ሹማምንት (የመንግሥቱ የጥይት ሰለባዎች) አንዱ ሊሆን ይችላል፡፡

ኑዛዜ በባህሪው በውዴታ ሳይሆን በግፊት የሚመጣ ነው፡፡ በየትኛውም መልኩ ብንተነትነው የመበስበስንና የመጨረሻውን የህቅታ ዜማ የሚያንጎራጉር የድምጽ ትርጉም ይሰጠናል፡፡ ታዲያ በቅርቡ የጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝን ኑዛዜ ሰምተናል፣ «እዚህ እናወራለን እንጂ ከዚህ ከወጣን በኋላ የተለያየ የራሳችንን ኔትወርክ እንዳይነካብን እንከላከላለን» ይላል፡፡ እናም «ብቻውን የሚሚገት የሚረታው የለም» በሚባልለት ጉባዔ ውስጥ ያፈተለከ ንግግር ነው፡፡ በእርግጥ ይህ ኑዛዜ በየትኛው የግፊት ዓይነት እንደመጣ ለመገመት አስቸግሮኛል፡፡ ጤነኛ በሆኑበት ዘመን ለቅድመ-ጥንቃቄ ያሉት ይሁን፣ መጃጀት ሲገሰግስ ይምጣ፣ አሊያም በጣር ሰዓት የተፈፀመ እንደሆነ አልገባኝም፡፡

«መጀመሪያ ላይ ሥልጣናቸውን በበቂ ሁኔታ ስላደራጁ በምሉዕነት የተናገሩት ይሆን እንዴ?» ብዬ እንደማሰብ ቃጥቶኝ ነበር፡፡ ነገር ግን፣ የተጠቀሟቸውን ቃላቶች በተደጋጋሚ ስመለከታቸው ፍርሃቴን አናሩት፡፡ ወትሮ ኢህአዴጋውያን ከሊቅ እስከ ደቂቅ የሚጠቀሙባቸውን ንግግሮች አልተጠቀሙም፡፡ ለምሳሌ፡- «አንዳንዶች» አላሉም፣ «ጥቂቶች» አላሉም፡፡ ይልቅ ሁሉንም በሚያጠቃልለው በሁለተኛ መደብ ነው ምስጢሩን የጮኹት፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ እንዲናዘዙ ግፊት ውስጥ ካስገቧቸው ዋነኛ ጉዳዮች መካከል የዘመድ አዝማድ ጉዳይ አንዱ ነው፡፡ ይህንን መነሻ አድርጌ የኢትዮጵያ ድንበሮች በየትኛው ኮንትሮባንዲስቶች እንደሚደፈሩ አስታወስኩ! የተለያዩ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች በየትኛው ወገን እንደሚንቀሳቀሱ በድጋሚ አስታወስኩ! ወደሌሎቹ መሺጋገር አላስፈለገኝም፡፡ ነገር ግን እላለሁ፣ በወገናዊነት የሚሰሩ ሥራዎች አንዱን ወገን አምርሮ የመጥላት ወይንም የጽንፈኝነት እንቁላል ይጥላሉ፡፡

የእነርሱ ሐብት እየደረጀ፣ የቀሪው እየኮሰሰ በቀጠለ ጊዜ ገንዘብ ባሰፋላቸው ክንፋቸው የጣሏቸውን እንቁላሎች እያሞቁ ከርመው እንደ ኢንኩቤተር ይፈለፍሏቸዋል፡፡

ይህ ሁኔታ የሀገሩን መልካምነት ለማየት ለሚጓጓ ሰው፣ ከተደወለ የቆየ ሰሚ ያጣ ጥሪ ነው፡፡ ይህንን ዘመድ አዝማዳዊ አራሙቻ ነቅለን ካልጣልን አይታገሰንም፣ ነገ ለምልሞ ያሸብረናል፡፡ ሁለተኛው የይሆናል ግምቴ ሙስና ነው፡፡ በቅርቡ በአዲስ አበባ ዙሪያ ከሚገኙ ከተሞች ወደ አንዱ ተጉዤ ነበር፡፡ ስሙን መጥቀስ የማልፈልገው ግለሰብ «ንግድ ፍቃድ ለማደስ የአካባቢ ጥበቃ ደብዳቤ ያስፈልጋል» ተብሎ ወደቢሯቸው ጎራ ብሎ እንደነበር፤ ይህንንም ቅድመ ሁኔታ ለማሟላት ከቢሮው ኃላፊ ጋር ወደድርጅቱ እንደ ተመለሰ፣ አካባቢውን ከአንገት በላይ እንደመቃኘት ካደረገው በኃላ ደብዳቤውን ለማግኘት ሃያ ሺ ብር ጉቦ መክፈል እንዳለበት እንደባለሙብት ነግሮት ወደምሽጉ እንደተመለሰ አጫውቶኛል፡፡

በየዕለቱ ማግኘት የሚገቡንን አገልግሎቶች ለማግኘት፣ ሹማምንት ገንዘብ መጠየቅ አግባብነት ያለው ጉዳይ አስመስለውታል፡፡ «ከሹም አይጣሉም፣ ከግንብ አይታገሉም» እንዲሉ ባለፈው ዓመት መጨረሻም የፀረ ሙስና ኮሚሽን እየሰረቁ መሆኑን እያወቀ «ልማቱን ላለማደናቀፍ» በሚል የማርያም መንገድ የሚሰጣቸው ሹማምንት እንዳሉ ነግሮናል፡፡ ይህንን በሰማሁበት ወቅት፣ ምናልባት ኃላፊዎች ጠረጴዛ ላይ የሚያስቀምጡት ካሌንደር «አስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ላይ መቁጠር አቁሞ ይሆን እንዴ?!» ብዬ እንደመጠርጠር አድርጎኛል፡፡ ሦስተኛ ሊሆን የሚችለው፣ ምናልባት የህዝቡ የእሮሮ ጋን ሞልቶ እየፈሰሰ ስለሆነ ይህንን መከታ አድርገው ለቡድኑ ያስተላለፉት መልዕክት ሊሆን ይችላል፡፡ የበዙ አራተኛና አምስተኞች አሉ፡፡

መርሳት የሌለብኝ ጥርጣሬ አለ፣ እርሱም የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ስምንት ነጥብ ሁለት ሚሊየን ያደረሰው ረሃብ፣ የተባበሩት መንግሥታት በበኩሉ ከሶሪያው ቀውስ የከፋም ሊሆን ይችላል ብሎ ለገመተው የአስራ-አምስት ሚሊየን ሕዝብ የረሃብ ጉዳይም ከቁጥር ሊያስገቡት ይችላሉ፡፡ በእርግጥ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ኑዛዜ «ላያጠግቡ መጋበዝ፣ ላይገሉ ካራ መምዘዝ ነው» የድርጅቱ የወትሮ አቋም የመቀየር አቅም አልተሸከመም የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ ሥር ነቀል ለውጥ ለማምጣት ከተፈለገ ግለሰቡ ሳይሆኑ በቡድን የሚያምነው ድርጅት ይህንን ንግግር መናገር አለበት፡፡ ቡድኑ ደግሞ ይህንን ለማድረግ «ተዘረጋ» የተባለውን ኔትወርክ በፍቃዱ ለመበጠስ ፍቃደኛ መሆን ይገባዋል ይላሉ፡፡ የሆነስ ሆነና በስብሰባ የተባለው ሁሉ ይፈፀም ይሆን? ዕድሜ ይስጠንማ!!!

> <<መጀመሪያ ላይ ሥልጣናቸውን በበቂ ሁኔታ ስላደራጁ በምሉዕነት የተናገሩት ይሆን እንዴ?>> ብዬ እንደማሰብ ቃጥቶኝ ነበር። ነገር ግን፣ የተጠቀሟቸውን ቃላቶች በተደጋጋሚ ስመለከታቸው ፍርሃቴን አናሩት። ወትሮ ኢህአዴጋውያን ከሊቅ እስከ ደቂቅ የሚጠቀሙባቸውን ንግግሮች አልተጠቀሙም። ለምሳሌ፡- <<አንዳንዶች>> አላሉም፣ <<ጥቂቶች>> አላሉም። ይልቅ ሁሉንም በሚያጠቃልለው በሁለተኛ መደብ ነው ምስጢሩን የጮኹት።ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ እንዲናዘዙ ግፊት ውስጥ ካስገቧቸው ዋነኛ ጉዳዮች መካከል የዘመድ አዝማድ ጉዳይ አንዱ ነው።

በሀሳብ ልዕልና እናምናለን!
አዲስ ገፅ

ምርት እና አገልግሎትዎን
በ <<አዲስ ገፅ>>
መጽሄታችን ያስተዋውቁ!!!

የለውጥ አዋጅ...... እንቢልታው ይነፋ! ነጋሪት ይጎሰም!

ሰሎሞን ተሰማ ጀ.

Email: solomontessemag@gmail.com

እደግመዋለሁ፡፡ የለውጥ አዋጅ፣ ይታወጅ! እንቢልታው እየተነፋ፣ ነጋሪቱም እየተጎሰመ፣ በለውጥ ረጅም ጎዳና ላይ ለመዝመት እንነሳ! ረጅሙን ጉዞ፣ እልህ አስጨራሹን ጉዞ፣ አሁኑኑ እንጀምረው፡፡ አዎን! ነጋሪቱ ይጎሰም! እንቢልታውም ይነፋ! ለለውጥ የተዘጋጃችሁ ሁሉ፣ ማቄን ጨርቄን ሳትሉ፣ አቅማችሁ የፈቀደውን፣ ቤታችሁ ያፈራውን፣ ስንቅና ትጥቅ ይዛችሁ ውጡ! ለውጡ፣ ያለእያንደንዳችን በጎ አስተዋፅኦ ፍጹም አይሳካምና ኑ ውጡ፡፡ ኑ! ታገፈጡ፡፡ ለውጥን ራሱንም ተጋፈጡት! እንቢልታው ሲነፋ፣ ነጋሪቱም ሲጎሰም፣ በሰመመን እንቅልፍና ዱካክ ውስጥ ሆናችሁ፣ የቀን ቅዠት ከሚነጣችሁ፣ “ኑ! ውጡ!” ይላችኋል ለውጡ!

የለውጥ አዋጅ ሲታወጅ፣ ነጋሪቱ ሲጎሰም፣ እንቢልታውም ሲነፋ፣ በሰመመን ድብርት ውስጥ፣ ካለ ሆኖ የሚያንቀላፋ፣ ወየውለት፡፡ ዝቅ ብሎ አንገቱን! ከፍም ብሎ ባቱን! ይቆርጠዋል-የታሪክ ሰይፍ፣ ይወገዳል ከመጪውም ሰልፍ! አዎን! ትልቅ ታሪክ ያለን፣ ለሺህ ዘመናት የኖርን፣ ለጽድቅና ለክብር፣ ቀን ከሌት የተጋን፣ ትልቅ ሕዝብ ነን፤ ማንም ያልደፈረን፡፡ አሁንም ቢሆን፣ አንገታችንን ያልደፋን፣ በክብር ተመልተን፣ ልዕልናችንን ይዘን፣ ወደፊት የምንጓዝ፣ ዘላለማዊዎች ነን፡፡ ዓለም ስትለወጥ፣ ከዘር አባዜ ወጥታ፣ የእያንዳንዱን ሰው መብት፣ እኩል በኩል ገምታ ስትሰጥ፤ ባረጀና ባፈጀ ወግ ውስጥ ታስረን፣ በዘር አባዜ ስንገላመጥ፤ በዓለም ዓቀፍ ሴራ ጥርስ ውስጥ፣ እንደማንስለቀጥ ምንም ዋስትና የለንም፡፡ ስለዚህም፣ የለውጡ አዋጅ እንዲታወጅ፣..... ነጋሪቱ ይጎሰም! እንቢልታውም ይነፋ!

የአዋጁን ጥሪ ለመስማት፣ ካለ የማዳመጥ ችግር ያለበት፤ የለውጡን ዘማች ሰልፈኞች ለማየት፣ ካለ የማየት ችግር ያለበት፣ ቱርጁማን ይቀጠርለታል፤ ነገር ግን፣ መከተል አለበት፡፡ ለውጡ ማንንም አይመርጥም፤ ማንንምም አይጥልም፡፡ የታሪክ ሚዛን ነው፤ ሁሉንም ይሰፍራል፡፡ የታሪክ ጎዳና ነው፤ ሁሉንም ያስኬዳል፡፡ የታሪክም ሰልፍ ነው፤ ሁሉንም ይጣራል፡፡ “ኑ! ተቀላቀሉኝ፣ እንዳትቀሩብኝ” ይላል፡፡ የምንጓዘው ወደ ግለሰብ ነፃነት ነው፤ የምንዘምተው ወደእኩልነት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በሕግ ፊት እኩል ወደምንዳኝበት፤ እያንዳንዳችን በሀገር ጉዳይ ላይ እኩል ወደምንተችበት፤ እያንዳንዳችን በብሔራዊ ጥቅማችን ላይ እኩል ወደምንሰማበት፤ ወደዚያ መፃኤ ግብ፣ ባንድነት የምንተምበት ሰዓት አሁን ነው፤ የለውጥ አዋጅም የሚታወጅበት፡፡ አልሰማሁም ብሎ የሚቀር ካለ፣ አላየሁም ብሎም የሚያመነታ ካለ፣ ከፍርድ አያመልጥም፤ ምን እንጦሮጦስ ቢሰጥም፡፡ ፍርዱ የታሪክ ነው፤ ትዕዛዙም አዋጅ ነው፡፡ አዎን! ነጋሪቱ ይጎሰም! እንቢልታውም ይነፋ!

የአዛውንቶችና የአንጋፋዎች ተግሳጽና ምክር የሚደመጥበት፤ የጎልማሶችና የባልቴቶች ሚና የሚወደስበት፤ የወጣቶችና የታዳጊዎች አቅም ጎልቶ እሚወጣበት ወቅት፣ አሁን ነው፡፡ አሁን ነው፣ አዲሱንና ግዙፉን ኢትዮጵያዊነት የምናድሰው፡፡ ያሻንን የምናመርትበት፤ የሚያዋጣንንም የምንነግድበት፤ የሚያስፈልገንን የምንገበይበት፤ ልባችን የወደደውን የምንቀስምበት፤ የፈቀድነውንም የምንጽፍበት፤ ማለት ያለብንንም የምንናገርበት ወቅት እንዲመጣ ከፈለግን፣ የለውጥ አዋጁ መታወጅ አለበት፡፡ የአዋጁም ማብሰሪያ፣ እንቢልታው ይነፋ! የሰልፉም ማጀቢያ፣ ነጋሪቱ ይጎሰም! ኢትዮጵያዊነት ጸንቶ እንዲኖር፣ ከዓለም እስከ-ዓለም፣ እንቢልታው ይነፋ! ነጋሪቱም ይጎሰም!

ለውጡ አርበኞችን ይሻል፤ የታጠቁትን በእውቀትና ክህሎት፡፡ ለውጡ ከያኒያን ይሻል፤ ከስር ከስር ተከታትለው የሚያነውሩት፡፡ ለውጡ ገንቢዎችን ይሻል፤ ግሩም መሠረት የሚጥሉለት፡፡ ለውጡ አንጥረኞች ይሻል፤ አሸምንሙነው የሚያስጌጡት፡፡ ለውጡ ዘማሪዎች ይሻል፤ ግነን-ፍነን የሚሉት፡፡ ለውጡ ፈካሪዎች ይሻል፤ የዕለት ውሎውን የሚዘግቡለት፡፡ ለውጡ ተኳሾችን ይሻል፤ እንዳይናቸው ብሌን የሚጠብቁት፡፡ ለውጡ ቀሳውስትን ይሻል፤ ሑዳዴን የማይዙለት፡፡ ለውጡ ሼኪዎችን ይሻል፤ ረመዳን የሚፆሙለት፡፡ ለውጡ ዘማሪዎችና ዘያሪዎችን ይሻል፤ በየእምነታቸው የሚታደሙለት፡፡ ቆንጃጅትንና ጉብሎችንም ይሻል፤ ጉዞውን የሚያስቀጥሉለት፡፡ አዋጁ ትዕዛዝ ነው፤ ማንም የማይቀርበት፡፡ ስለዚህም፣ ነጋሪቱ ይጎሰም!እንቢልታውም ይነፋ!ለአዲስ ዘመን፣ ለአዲስ ተስፋ!

በስደትና በእንክርት አዙሪት፣ በባዕድ አገር የምንሳቀቅበት፤ በቀቢፀ-ተስፋ ውስጥ ሆነን፣ ጉፋያ አካላችንን የሚወዘውዝበት፤ በቆዳችን ቀለምና በክሳታችን የምንለካበት፤ ሰብዓዊ ክብራችን ታውቆ፣ በምልዓት የምንገንበት፤ ያ ዘመን እንዲጀመር፣ ጎሑም እንዲቀድ፤ አዋጁን አዳምጠን፣ አለብን ምላሽ መስጠት፡፡ ሥራዎችን ተከፋፍለን፤ መሪዎችን አስቀድመን፤ አማካሪዎችን መርጠን፤ ከሳሽና ፈራጆችን፣ አቃቤዎችን ይዘን፤ ስንቅ አቅራቢዎቻችንን፣ አበዛዎቻችንን አውቀን፤ ቀያሾቻችንንና ተላሚዎቻችንን አደራጅተን፤ ሊቃፈሮቻችንንና ለሕገ-ደንባችን፣ ከልባችን ታዝዘን፤ አንጋሽና ቀዳሾችን፣ ወይዛዝርቱንም ይዘን፤ ወደማይቀረው መፃኤ-ዕድል በጋራ መሄድ አለብን፡፡ ይህ ነው፣ ምኞታችን! ይህም ነው፣ ራዕያችን! የቁም ቅዠታችንንና የቁም ሰመመናችንን፣ እንደጦስ ዕቃ ጥለን፤ በአዲስ መንፈስ፣ በአዲስ ወኔ፣ በብጽአት ተመልተን፤ ወደምሉው ዘመን፣ በድል መጓዝ አለብን፡፡ ስለዚህም፣ እንቢልታው ይነፋ! ነጋሪቱም ይጎሰም!

ነጋሪቱ ሲጎሰም፤ እንቢልታውም ሲነፋ፣ ያኔ ደማችን በትክክል ይሞቃል፣ ወኔያችንም ይግላል፡፡ ለውጥ በባሕሪው፣ ደመ-ቀዝቃዛነትን ይጠላል፡፡ እንደለውጥና እንደነውጥ ያሉት ክስተቶች፣ ደመ-ቀዝቃዛነትን አጥብቀው ይንቃሉ፡፡ ረጋ ብሎ የሚያስብ እንጂ፣ ረግቶ የሚቀርን፣ ለውጣችን አይፈልግም፡፡ ስለዚህም፣ ደመ-የሚንተከተክ፣ ወኔው የጋለ፣ ቅስሙም ያየለ፣ የብረት ቆሎ ነኝ፣ እንቢኝ! እያለ፣ የሚንተገተግ የንግግር ክህሎት ያለው፣ ጋዜጠኛና ያደባባይ ተናጋሪ፣ በእጅጉ ይፈለጋል፡፡ እጅግ ትጉህና እጅግ ብርቱ የሆኑም ሳይንቲስቶች፣ ከልክ በላይ ያስፈልጉናል፡፡ያሸነፉትን ሕዝብ፣ በጠላትነት የማያዩ፣ ያጋዟቸውን ሕዝቦች፣ እንበቀል የማይሉ፣ በታሪክ ሕሊና ውስጥ፣ መርምረው የሚምሩ፤ በሥነ-ምግባር አዛቸው ውስጥ፣ ደግነትን የሚያበስሩ፤ ጥላቻን ተራምደው፣ በቀልን የሚሽሩ፤ የለውጥ ሰልፈኞች፣ በሺሆች የሚቆጠሩ፤ ውለው አድረውም፣ ሚሊዮኖች የሚያፈሩ፣ ቢሊዮኖች የሚመሩ፣ ኢትዮጵያውያን ይፈለጋሉ፡፡ ዛሬውኑ ጉዟቸውን ያለማመንታት የሚጀምሩ፡፡ ማቄን ጨርቄን የማይሉ፤ ስንቄን ወርቄን ለለውጡ አዋጣለሁ የሚሉ፤ አሁኑኑ ይፈለጋሉ፡፡ ስለዚህም፣ ለለውጡ አዋጅ ማብሰሪያ፣ እንቢልታው ይነፋ! ነጋሪቱም ይጎሰም! ድዉ! ድም! ድዉ! ድም!

ኑ! ወደ አዲሱ ዘመን፣ በምልዓትና በኩራት፣ ዛሬውኑ እንትመም፡፡ ድዉ! ድም! ኑ! የዘረኝነትንና የጎጥን ጥንባሳ፤ የሕግ-ጥሰትንና የመድሎን ነቀርሳ፤ በዕርቀ-ሰላምና በምሕረት ወላንሳ፤ ዳግም እንዳያገረሽ፣ መቼም እንዳይነሳ፤ አድርገን እንደምስሰው፣ ከምድረ-ገጽ ሐበሻ፡፡ ኑ! ባንድነት ሆነን፣ የትውልዶችን ያድሎ ሰንሰለት፣ እግረ-ሙቃችንን በጣጥሰን፤ ባልቴትና መበለቷን፣ ባለትዳር ሆነች ፈቷን፣ ላጤም ሆነች ሳዱላ፣ ባለቡቅሯንም ይዘን፤ ለወንዶቹ የምንሰጠውን፣ ለሴቶቹም አካፍለን፤ የጋራ ዕድላችንን፣ በጋራ እንድንወስን፤ አሁኑኑ እንቀሳቀስ፣ አሁኑኑ እንትመም፡፡ነጋሪቱ ይጎሰም! ይበል ድዉ! ድም! ወላጆቻቸውን በስደት፣ በበሽታና በጣዕረ-ሞት፤ የተነጠቁ ወጣቶች፣ ወላጅ አልባም ሕፃናት፤ አሳዳጊ የሌላቸው፣ የእጓለ-ማውታናት፤ ሞጋሳ ሆኑ ጉዲ-ፈቻ፣ ቃልቻም ሆኑ ቦረንቲቻ፤ በባሕልና በቋንቋቸው፣ እኩል ወደሚማሩበት፤ ኹሉ-በኩሉኺት፣ የሆነችን የእኩል ቤት፤ በውዴታ እንድናቆም፣ በፍቃደ ሃያል ስሜት፤ መንቀሳቀስ አለብን፡፡ ስለዚህም፣ እንቢልታው ይነፋ! ነጋሪቱም ይጎሰም! ድዉ! ድም!

ይኼንን ጀብዷችንን፣ ከስር ከስር ተከታትለው፤ ለዓለም የሚያበስሩን፤ ይኼንን ድላችንን፣ በመቅረጽ-የሚቀዱልን፣ ጋዜጠኞች፣ አርታኤዎች፣ ዘጋቢዎችና ፀሐፍት፣ ደራሲያንና ተዋንያን፣ ፀሐፌ-ተውኔቶች፣ የፊልም አዘጋጆችና የፊልም ሞያተኞች፣ አሁኑኑ ይፈለጋሉ፡፡ ሰልፈኞችን ባፍላ-ወኔ፣ በግጥምና በዜማ፣ የሚያወድሱና የሚያሞግሱ፣ የለውጥንም መንፈስ፣ ተግተው የሚቀሰቅሱ፣ ሙዚቀኞችና ዳንኪረኞች፤ ገጣሚና አዝማሪዎች፤ አሁኑኑ ይፈለጋሉ፡፡ ለለውጡ ዘፀአት፣ ጉዞ ስንጀምር፤ ሙሴና አሮንን፣ አሲዘናቸው በትር፤ ክርስቶስና ኤልያስም፣ ሲመለከቱ ወደምድር፤ ነብዩ ሞሐመድም፣ ሲፈቅዱልም ከይር፤ ያኔ እናውቀዋለን፣ መለፈፉን አዲስ ተዓምር፡፡ አላህ አልነው እግዚአብሔር፣ የዘላለም ስውር ምስጢር፤ ሰልፋችንን ተቀላቅሎ፣ ይሻገራል ወደ አልማር፤ በረከትና ረድኤትን ወደምንሸምንበት ሀገር፡፡ ሳንራብና ሳንጠማ፣ ሳናዝንና ሳንከፋ፤ ሳንሞትና ሳንገል፣ ሳንነሳና ሳንደፋ፤ ወደ አብርሆቱ ስፍራ፣ ወዳሰረጽነው ተስፋ፤ ልንደርስ አንችልም፣ ከቶ አንቁረጥ ተስፋ፡፡ ስለዚህም፣ ይታወጅ የለውጥ አዋጅ! ይንደቅደቅ እንቢልታው ይነፋ! ይጋም ነጋሪት ይጎሰም፡፡ ይበል ድዉ! ድም! ድም!

አሁን ያለንበት ዘመን፣ አሁን የደረስንበትም፤ ባባጣና ጎርባጣ፣ በገደልና ሰርጥም፤ በባሕርና ሸለቆ፣ ሸንተረርና ስምጥም፤ አልፈንና ተርፈን ነው፣ በጃንጥላ አልወረድንም፡፡ገዢዎቻችንም በሙሉ፣ እንደመና አልወረዱም፡፡ ስዩመ-እግዜር ነን ያሉት ሆኑ፤ ስዩመ-ሕዝብ ዲሞክራትም፤ ላሉት ክብር ለመብቃት፣ በፓራሹት አልዘለሉም፡፡ የጫኑትን ሃሳብ ይዘው፤ ሸንተረርና ኮረብታውን፣ እንደገመረ ቧጠው፣ እንደፍልፈል ጉድጓድ ምሰው፣ እንደጃርትም ጭስ ታጥነው'ንጂ፤ ዩፎዎች አይደሉም፣ የፈለሱ ከማርሱ ዓለም፡፡ እንቢልታው ሲነፋ! ነጋሪቱ ሲጎሰም! ልቡ ትር-ትር ሳትል፤ ለሰልፉ ወኔው የሚግም፤ ወደ ሙሉው የአልማር ምድር፣ በክብር የሚገባ፣ በሐሴት ለመኖር፤ አሁኑኑ ይነሳ፣ ዛሬውኑ ይጀምር፡፡ ኃያል ሕዝቦች ሆነን፣ በአፍሪካም ሆነ በመላው ዓለም ገነን፣ እንድንወጣ ካስፈለገን፤ ያያት ያባቶቻችንን ሐጢያት መዘክዘክ ትተን፤ ላልተፈጸመ ታሪክ፣ ሐውልት ማቆም ንቀን፤ ላልተሰራውም ግፍ፣ ጣዖት ከማምለክ ታቅበን፤ ራሳችንን እንደጴጥሮስ፣ ለምስዋትነት አጭተን፤ የለውጡ አዋጅ ሲለፈፍ፣ እንቢልታው ሲነፋ፣ ነጋሪቱ ሲጎሰም፤ በጋራ እንንቀሳቀስ፤ ከቶ አንቁረጥ ተስፋ!

አዎን! እንቢልታው ይነፋ! ነጋሪቱም ይጎሰም! ትናንትና ነጋሪትና እንቢልታዎችን ሠርተናል፡፡ ዛሬ ደሞ፣ የሠራናቸውን እንቢልታዎች እንነፋቸዋለን፤ ያበጀናቸውንም ነጋሪቶች እየጎሰምን አልማር ወደተሰኘው ምድር እንነጉዳለን፡፡ ነገም፣ ኃያል ሕዝብ ሆነን፣ በዓለም መድረክ ላይ በምልዓት እንታያለን፡፡ ኃያል ሕዝቦች ሆነን፣ እምቅ የሆነውን የራሳችንን ሀብት፣ ለቀጣይ ትውልዶቻችን በመቆጠብ፤ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል ከሚል፣ የወደል አህያ ብሒል ወጥተን፤ እንደሰው ሰብዓዊ፣ እንደ መላዕክትም አማናዊ፤ ሆነን የለውጡን አዋጅ መታዘዝ አለብን፡፡ እናም፣ እንቢልታው ይነፋ! ነጋሪቱም ይጎሰም! ይበል ድዉ! ይበል ድም! ድም! ዛሬውኑ እንነሳ! አሁኑኑ አንትመም! በዘመን ጎርፍ ውስጥ፣ ከምንሆን እርም! ይነፋ እንቢልታው! የጎሰም ነጋሪቱ! ይበል ድዉ! ድም! ምድርና ሰማዩ በወኔ እስኪግም! ግግግግግግም!

ስለምልክት ቋንቋ አንዳንድ እውነታዎች

ኢያሱ ኃይሉ(ዶ/ር)
/በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የምልክት ቋንቋ ባለሙያ/

ይህ ጥያቄ እስከ1960 ዓ.ም ድረስ የበርካታ የሥነ-ቋንቋ ተመራማሪዎች ጥያቄ ነበር:: ጥያቄው ሊመለስ የቻለው፣ ቀደም ሲል የሰዎችን የቋንቋ ባህርያት ከሌሎች የመግባቢያ ዘዴዎች የሚለይበትን ቻርለስ ሃኬት በተባለ አሜሪካዊ የሥነ-ቋንቋ ተመራማሪ የዘረዘራቸውን ወደ 13 ያህል ባህርያትን (ለምሳሌ- ዘፈቀዳዊነት (arbitrariness)፣ ትርጉም-አዘልነት (semanticity)፣ ምርታማነት (productivity)፣ በባህል መተላለፋዊነቱን (cultural transmission)፣ በጊዜና በቦታ ስለሌሉ ማውራት መቻሉ (displacement) ...ወዘተ መነሻ በማድረግ ዊልያም ስቶኪ (የሥነ- ምልክት ቋንቋ አባት) የተባለ አሜሪካዊ በምልክት ቋንቋ ላይ ምርምር አድርጓል::

ቀደም ሲል ሃኬት በንግግር ቋንቋ ላይ ያካሄደው ምርምር ውጤታማ ስለነበር ስቶኪም በምልክት ቋንቋ ላይ (በአሜሪካ ምልክት ቋንቋ) ላይ ምርምሩን አካሂዶ «ቋንቋ ነው ወይስ አይደለም?» የሚለውን የረጅም ጊዜ ጥያቄ ፈትቷል:: ከ13ቱ ባህርያት ውስጥ ምልክት ቋንቋም ሁሉንም ባህርያት ያላሟላው አንዱን ብቻ ነበር:: ይህም ቀደም ሲል በሃኬት ቋንቋ ማለት «በድምጽ ላይ ብቻ የተመሰረተ ነው» የሚል እንደምታ በማኖሩ ነው:: ስቶኪ ግን ቋንቋ ማለት ድምጽን ብቻ መሠረት ያደረገ ብቻ ሳይሆን በአካል ክፍሎች እንቅስቃሴና «በዕይታ ላይ ጭምር የተመሰረተ ነው» ብሎ አክሎበታል:: ዛሬ በዓለም ላይ ከስቶኪ ፈር ቀዳጅ ምርምር ጀምሮ በርካታ ምርምሮች እየተደረጉ ይገኛሉ:: ሆኖም ግን፣ በአሁኑ ጊዜ በምልክት ቋንቋ ላይ የሚታየው ጥናትና ምርምር ትኩረቱን ያደረገው በሰዋሰውና አወቃቀሩ በተለይም በመስማት የተሳናቸው የቋንቋ አጠቃቀም ዙሪያ ነው:: «ቋንቋ ነው፣ አይደለም?» የሚለውን ክርክር ግን እምብዛም ጥናትና ምርምር ባልተካሄደባቸው ሀገራት ይስተዋላል:: ለዚህ መፍትሄው በሌሎች ሀገራት የተደረጉትን መነሻ ጥናቶች ማየቱ ተገቢ ነው::

ምልክት ቋንቋ መቼ ተጀመረ?

የምልክት ቋንቋ አጀማመር ልክ እንደ ሌሎች ቋንቋዎች «በዚህ ጊዜ እና ቦታ ተጀመረ» በማለት ትክክለኛውን ጊዜ ለማስቀመጥ የሚደረጉ ጥናቶች ገና በሂደት ላይ ናቸው:: በሀገራችን ላይ የምልክት ቋንቋን አጀማመር ከመስማት የተሳናቸው ትምህርት አጀማመር ማለትም ከ1950ዎቹ ጀምሮ ያለውን ታሪክ እንጂ ከዚህ ቀደም ተብሎ ያለውን ታሪክ በጥናት ያሳየ መረጃ የለም:: ሆኖም ግን የመስማት የተሳናቸው በነበሩበት ዘመን ሁሉ ይፋዊ ባልሆነ አጠቃቀም ምልክት ቋንቋን ይጠቀሙ እንደነበር መገመት ይቻላል:: ስለሆነም የምልክት ቋንቋ አመጣጥ ልክ እንደሌሎቹ የድምጽ ቋንቋዎች ሁሉ አመጣጣቸው ከሰው ልጆች አመጣጥ ታሪክ ጋር እንደሚገናኝ መገንዘብ ይቻላል:: ምናልባትም ሀገራችን ኢትዮጵያ የሰው ዘር «ሉሲ ወይም ድንቅነሽ» መገኛ እንደመሆንዋ መጠን አመክንዮው የሚያሳየን የቋንቋዎች ምንጭም ልትሆን እንደምትችል መገመት ይቻላል:: ሉሲም ብትሆን መስማት የተሳናት ልትሆን ትችላለች:: ይህ ከሆነ ደግሞ የምልክት ቋንቋ ዕድሜ ይህን ያህል ረዘመ ብንልስ?

ምልክት ቋንቋ አፍ መፍቻ ሊሆን ይችላል?

> አንድ መስማት የተሳናው የምልክት ቋንቋ አፍ መፍቻው ከመሆኑም ባሻገር ልሳነ - ብዙ ሆኖ የማደግ አጋጣሚን ነው፡፡በርካታ ኢትዮጵያውያም መስማት የተሳናቸውም የምልክት ቋንቋ አፍ መፍቻቸው ሆነው ማደግ እንደሚችሉ የሚታይ ዕውነታ ነው፡፡

መልሱ አዎ ነው:: ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ በዓለም ላይ ካሉት መስማት የተሳናቸው 10 ከመቶ የሚሆኑት የሚወለዱት መስማት ከተሳናቸው ወላጆቻቸው ነው:: የተቀሩት ደግሞ ከሚሰሙ ወላጆች ነው:: 10 ከመቶ የሚሆኑት ህጻናት ከወላጆቻቸው እየሰሙ የሚያድጉት የምልክት ቋንቋን ነው:: ምክንያቱም ድምጽን ሰምቶ የማደግ ሁኔታው አነስተኛ ስለሆነ ነው:: ስለሆነም የምልክት ቋንቋ ተፈጥሯዊ አፍ መፍቻቸው ይሆናል ማለት ነው::

በሌላ በኩል ደግሞ ከመስማት የተሳናቸው ወላጆች የሚወለዱ የሚሰሙ ህጻናት (CODA –Children of Deaf Adults) - እነዚህም በተመሳሳይ መልኩ የምልክት ቋንቋ አፍ መፍቻቸው ሆኖ ሊወለዱ እንደሚችሉ ይታያል:: በሀገራችን ያለውም ነባራዊ ሁኔታ ይኸው ነው::

ሁለቱንም የሚያመሳስላቸው ልሳነ-ክልዔ ወይም ልሳነ-ብዙ ሆነው የማደግ ዕድላቸው ሰፊ ነው::ይህም የሆነበት ምክንያት የአፍ መፍቻን ከቅርብ ወላጆቻቸው፣ ሁለተኛ ቋንቋን ከአካባቢ፣ ሶስተኛን ቋንቋ ደግሞ ከት/ቤት ተምረው ስለሚያገኙት ነው::

ከግል ልምዱ በመነሳት፣ በእንግሊዝ ሀገር ካጋጠሙኝ አንድ የምልክት ቋንቋ ፕሮፌሰር - እሱም መስማት የተሳነው - ከእሱ አንስቶ ወደ ኋላ ሰባት ትውልድ ድረስ ወላጆቹ መስማት የተሳናቸው ነበሩ:: እናቱ የኒውዚላንድ ምልክት ቋንቋ ይችሉ ስለነበር ለመማር አልከበደውም:: በቤት ውስጥ የሚጠቀሙበት ቋንቋ የአውስትራሊያ ምልክት ቋንቋ - የአፍ መፍቻው ሲሆን በሂደት በትምህርት ቤት እንግሊዘኛን ተማረ::

ካደገ በኋላ ወደ እንግሊዝ በመምጣት የእንግሊዝ ምልክት ቋንቋን ተምሮ በአስተርጓሚነትም (ዴፍ ኢንተርፕሬቲንግ) ይሰራል:: የአሜሪካን ምልክት ቋንቋም አቀላጥፎ መናገር ይችላል:: ይህ የሚያሳየው አንድ መስማት የተሳናው የምልክት ቋንቋ አፍ መፍቻው ከመሆኑም ባሻገር ልሳነ-ብዙ ሆኖ የማደግ አጋጣሚን ነው:: በርካታ ኢትዮጵያውያም መስማት የተሳናቸውም የምልክት ቋንቋ አፍ መፍቻቸው ሆነው ማደግ እንደሚችሉ የሚታይ ዕውነታ ነው::

ይህንን ሀሳብ የሚያጠናክርልን እስከዛሬ በዓለም ላይ ከተከሰቱት አንዱ የሆነው - የኒኳራጓ ምልክት ቋንቋ ነው:: ለመስማት የተሳናቸው ትምህርት ቤት ከመጀመሩ በፊት (1970ዎቹ) መስማት የተሳናቸው እርስ በርስ የሚገናኙበት ሁኔታ ስላልነበረ በተበታተነ ሁኔታ ነበር የሚኖሩት:: ቋንቋውን የሚጠቀሙት በቤት ቋንቋነት ብቻ በተወሰነ ደረጃ ነበር:: ነገር ግን፣ እርስ በእርስ ይግባቡ ስለነበር ትምህርት ቤት ተከፍቶ የመገናኘት አጋጣሚው ሲፈጠር እንደአንድ ማኅበረሰብ የራሳቸውን ቋንቋ ማዳበር ጀመሩ:: ምንም እንኳን መምህራን የሚያስተምሯቸው ከጣት ፊደል ያለፈ ባለመሆኑ ተማሪዎቹ ግን የራሳቸውን ቋንቋ በማዳበራቸው ምክንያት መምህራኑ ሊረዷቸው እንዳልቻሉ አንዳንድ ጽሑፎች ይጠቁማሉ::

በቀጣይ ምልክት ቋንቋን የሚመለከቱ መረጃዎች በዚህ ዓምድ ይቀርባሉ:: ለሚደርሱን ግብረ-መልሶች ምስጋናችን ያላቀ ነው::

የርሃቡ ነገር፤ ''ግመል ሰርቆ አጎንብሶ''

ብርቱካን አሊን ያየ ኑሮን አያማርርም !



አቤ ቶኪቻው
Abetokichaw@gmail.com

የዛሬ አምስት ዓመት ይፋ የተደረገችው ያቺ አስማተኛ ዕቅድ ትዝ ትልዎታለች ወዳጄ ...ምነው እንኳ «ዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን» ተብላ ከአምስት ዓመት በኋላ ሀገሪቷ ከማንም እርዳታ የማትቀበል የጥጋብ ሀገር ትሆናለች፤ስንል ምቀኛን አይኑ ደም ይልበስ አይነት ያቀድናት አስማተኛ ዕቀድ፤ ይሄኔ «እንዴት ይረሳል እንዴት ይረሳል ተረሳሽ ወይ...» እያሉ በሆድዎ ሲያንጎራጉሩ ታውቆኛል።

ትዝ ይልዎት እንደሆነ፣ በመንግሥታችን ላይ ትልቅ እምነት የሰነቅን ሰዎች ከአምስት ዓመት በኋላ ድራሹ ይጠፋል የተባለው ድህነት ድንገት ማስታወሻ ሳንይዝ ጠፍቶ ጉድ እንዳያደርገን በመስጋት መከራችንን እና ጉስቁልናችንን ይዘን ፎቶ ቤት እየሄድን የማስታወሻ ፎቶግራፍ ሁሉ ስንነሳ ነበርኮ ...ታዲያ የዛኔ የታጠበው የጉስቁልናችን ፎቶግራፍ እና ከአምስት ዓመት በኋላ የደረስንበት የአሁኑ ስዕላችን መመሳሰሉ፤ የዛን ጊዜ «ፎቶግራፈኛው አጭበርብሮን ነው ...ወይስ ድራሹ ይጠፋል» የተባለው ድህነት ዛሬም ጓዳችን አለ... ብዬ ብጠይቅ መቼም «የኔ ጌታ ፖለቲካ አታናግረኝ...» ብለው ጆሮ ዳባ አይሉኝም።

እኔ የምለው፣ ድሮ ድሮ ፖለቲካ የሚባለው ነገር በጣም በትንሹ የአቶ መለስን የጸጉር ሁኔታ መተቸት ነበር... እርሳቸውም፤ «ጸጉሬን እንዳሻችሁ መተቸት ትሸላላችሁ እንዳሻችሁ መሸለት ግን አትችሉም» ብለው ለሀገሬው ህዝብ መብት ሰጥተዋል ተብሎ ይነገር ነበር። (በቅንፍም እርግጥ ጸጉሬን አላሉም መላጣዬን ብለዋል... ብዬ መልካም ገጽታ ከማጠፉ ቃላባይ ተብዬ ስሜ ይጥፋ ብዬ ነው) ከቅንፋችን ስንወጣ ዛሬ ዛሬ «ራበኝ» ማለት ብቻውን ትልቅ ፖለቲካ ሆኗል አሉ። ፖለቲካ ብቻም ሳይሆን፤ «ራበኝ»፣ «ራባቸው»፣ «ተራቡ»፣ «ሊራቡ ነው»... ብሎ ማለት ድብቅ የፖለቲካ አጀንዳን ከሚያራምዱ እንደ ኒዮ ሊበራል ካሉ የሀገሪቱን መልካም ሲያዩ አይናቸው ደም የሚለብስ ቡድኖች እንደ አንዱ የሚያስቆጥር ታላቅ ወንጀል ነው! (ያው አሉ ነው... አሁንማ ርቀን እኮ ርግጠኛ መሆንም ቸገረን...)

በነገራችን ላይ ወዳጄ እኔ አሁን ያለሁባት ሀገር የ«ኒዮ ሊበራል» ፖለቲካ ሃሳብ መስራች የሆነችቱ እንግሊዝ ላይ ነው። እና ስለ «ኒዮ ሊበራል» ምንነት በቅጡ የመረዳት እድሉ ገጥሞኛል... ይሄንን ሃሳብ ያመጣችው ሴትዮ ማርጋሬት ታቸር ትባላለች። ይች ሴት በእንግሊዝ ሀገር ፖለቲካ ውስጥ በጣም አነጋጋሪ ከሚባሉት መካከል ነች ...እንደውም እኮ ያስታውሷታል፤ ባለፈው የእኛ ጠቅላይ ሚኒስትር የሞቱ ሰሞን ነበር እርሷም የሞተችው ...ታድያ ምንም እንኳ የሞተች ጊዜ ሀገሪቱን ሲያስተዳድር የነበረው ኮንሰርቫቲቭ የተባለው የራሷ ፓርቲ ቢሆንም '«አስር ሺህ በአነስተኛ እና ጥቃቅን የተደራጁ ወጣቶች» ለቀብር ማስፈጸም እንዲሰለፉ አልተደረገላትም፤ ቀብር የወጣ ወጣ፣ የቀረም ቀረ፤ ያለቀሰም አለቀሰ እምባ እምቢ ያለውም ዝም አለ ...ኧረ «እሰይ ስለቴ ሰመረ'» ብሎ ሁሉ የጨፈረ ነበረ ...ነገር ግን ማንም በለቅሶው ላይ አልተሳተፍክም ተብሎ፤ ወይም ፓርቲያችን በሀዘን ተኮራምቶ እያለ አንተ ፊትህ ላይ ደስታ ይነበብ ነበር ተብሎ የታሰረም ክስ የተመሰረተበትም አልነበረም።

እና እንዳልኩዎት፣ ሴትዮዋ በእንግሊዝ ታሪክ ውስጥ አነጋጋሪ የተባለች ጠቅላይ ሚኒስትር ነበረች፤ ከርሷ በፊት የመንግሥት ይዞታ የነበሩትን ተቋማት ሁሉ ወደ ግል አዛውራ «ፕራይቬታይዜሽንን» ለእንግሊዝ በስፋት ያስተዋወቀችው እርሷ ናት። ልክ እኛ ሀገር ፕራይቬታይዜሽንን መለስ እና ኢህአዴግዬ እንዳስተዋወቁን ማለት ነው። መንግሥት ለሰራተኛ ማኅበራት ሲያደርገው የነበረውን ድጎማ አስቀርታ «የራሳችሁ ጉዳይ» አይነት ፖሊሲም ነበራት፤ ይሄም ከኢህአዴግዬ ፖሊሲ ጋር ተመሳሰለብዎ እንዴ...? (የለሁበትም) ይቺ ጠቅላይ ሚኒስትር በበርካታ ምስኪን ዜጎች ዘንድ «ይድፋሽ ይገልብጥሽ» የተባለች ብትሆንም በርካታ ሃብታሞችን በማፍራት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ከመሬት አንስታ ከፍታ ላይ አድርሳዋለች የሚሏት ወገኖች አሉ። ነገር ግን፣ በዛውም ልክ የሥራ አጥን ቁጥር በመጨመር የገበያን ዋጋ ከፍፍፍ በማድረግም ብዙዎች እርስኩሲት ይሏት ነበር። (በበኩሌ ስለ ኒዮ ሊበራል ጽንሠ ሀሳብ ባለቤቷ ታቸር ስሰማ ይቺን ሴትዮ የት ነው የማውቃት እያልኩ ሳንሰላስል ሁልጊዜም ኢህአዴግዬ ከነ ቀሚሷ ጎርደድ እያለች ነበር የምትመጣብኝ....) እና ምን ለማለት አካባቢ ነው... ያሉኝ እንደሆነ ድፍረቴን አሰባሴ የመታው ይምጣ ብዬ ስናገር፤ በተለይ ከደመሰሰችው ደርግ ጋር ስትነጻጸር ራሷ ኢህአዴግ እልም ያለች ኒዮ ሊበራሊስት ናት!!! (ደሃን አፈር የምታሰበላ ሀብታምን ደግሳ የምታበላ ማለት ነው ባጭሩ)

> እንዴ ይሄው ትላንት የርሃብ አደጋ አንዣቦብናል ...እንጃልን መሰንበቻውን፤ ብለው ለውጪ ጋዜጠኛ የተናገሩ ሰዎች፣ ዛሬ በሀገር ውስጥ ጋዜጠኞች ወረራ ተደርጎባቸው እነርሱ እርዳታ ሲጠብቁ ጥያቄ የተሸከሙ ጋዜጠኞች እና መልካም ገጽታ ገንቢዎች ልጇ የሞተባትን ሴትዮ ሀዘኗ የሀገር መልካም ገጽታን እንዳያጠፋ ጸዓዳ አልብሰው፣ ፊቷን በቫዝሊን አውዝተው ፈገግታ ከራሳቸው ሰጥተዋት ፎቶ ሲያነሷት አልሰነበቱም እንዴ... <<የቆቦዋን ብርቱካን ያየ ኑሮን አያማርርም>> እያለ የሀገሩ ሰው ሁሉ እየተረተ ነው ሲባል ሁሉ ሰምቻለሁኮ!

ኡ ኡ... ወዳጄ ይቅርታ ፖለቲካ አበዛውብዎ... እና እርስዎ እንዴት ኖት...? ኢደራ፤ እርፈው ጮክ ብለው «ደህና ነኝ እግዜር ይመስገን...» ብለው ይመልሱልኝ፤ ነገር እንዳያመጡብኝ! «ጻሐዩ መንግሥቴ እያለ ምን እሆናለሁ ብለህ ነው... ቀጥ አድርጎ ይዞኛል... አንቀባሮኛል...» ብለው ጎረቤት ሀገር በተለይ ይቺ ኤርትራ እንድትሰማ አድርገው ይመልሱልኝ። አለበለዚያ፤ እንዴት ኖት ታድያ... ባልኩዎ ጊዜ «ምንም አልል ብቻ ትንሽ...» ብለው ያቅማሙ እንደሆነ ነገ ያሀገሩ ጋዜጠኛ መቅረጸ ምስሉን እና መቅረጸ ድምጹን እንደ ክላሽንኮቭ ወድሮ መጥቶ «እንዴት ኖት ሲባሉ፤ ምንም አልል ብቻ ትንሽ...?» ብለው ያሉት ምንም ለማለት ፈልገው ነው? ይሄንን ንግግርዎን የሀገሪቱን ልማት ሲያዩ አይናቸው ደም የሚለብስ ግለሰቦች እና ድርጅቶች በመጥፎ እየተረጎሙት የሀገራችንን መልካም ገጽታ እያጠለሹ ነው ....እና ምንም አልል ብቻ ትንሽ .... ብለው ሲሉ ምን ለማለት ፈልገው እንደሆነ ቢያብራሩልን ...ተብለው ...ብቻ ትንሽ ጥጋብ እና ፍስሃ እየተጫወተብኝ ነው.... አስብለው በቴሌቪዥን ከመተላለፍዎ በፊት ካሁኑ ለማንኛውም ሰላምታ... ሞቅ ያለ፣ በፈገግታ የታጀበ ምላሽ በመስጠት ሀገራዊ ግዴታዎን ይወጡ!

እንዴ ይሄው ትላንት የርሃብ አደጋ አንዣቦብናል ...እንጃልን መሰንበቻውን፤ ብለው ለውጪ ጋዜጠኛ የተናገሩ ሰዎች፣ ዛሬ በሀገር ውስጥ ጋዜጠኞች ወረራ ተደርጎባቸው እነርሱ እርዳታ ሲጠብቁ ጥያቄ የተሸከሙ ጋዜጠኞች እና መልካም ገጽታ ገንቢዎች ልጇ የሞተባትን ሴትዮ ሀዘኗ የሀገር መልካም ገጽታን እንዳያጠፋ ጸዓዳ አልብሰው፣ ፊቷን በቫዝሊን አውዝተው ፈገግታ ከራሳቸው ሰጥተዋት ፎቶ ሲያነሷት አልሰነበቱም እንዴ... «የቆቦዋን ብርቱካን ያየ ኑሮን አያማርርም» እያለ የሀገሩ ሰው ሁሉ እየተረተ ነው ሲባል ሁሉ ሰምቻለሁኮ!

እና ወዳጄ እንኳንስ ርስዎ ሊያማርሩ እና ኑሮውን የሚያማርር፣ በሰላምታ ጊዜ ቀልጠፍ ብሎ ደህና ነኝ ይመስገነው... ምን ጎደለብኝ በማለት ፈንታ ምንም አልል ብቻ... ብሎ የሚያቅማማ ያዩ እንደሆነ ጥቆማ በማድረግ የሀገርዎ ገጽታ እንዳይበላሽ የበኩልዎን ያደርጉ እንደሆነ እሰየው ካልሆነ ውርድ ከራሴ!

ቁምነገር ግን ወዳጄ፤ ይሄ የዘንድሮ ድርቅ ነገር እንዴት ነው ...ከዛሬ አራት ወራት በፊት ጀምሮ ባላገሩ ከብቶች ሲረግፉበት ሥልጣናቸውን ይማረውና አቶ ሬድዋን ሁሴን «ከብቶቹ የሞቱት ቶሎ ውሃ የማያጠጣቸው በማጣታቸው ነው'» አሉን፤ እሺ ባለሥልጣን ናቸው ያሉትን በጄ እንበላቸው፤ ብለን ዝም አለን። ሌሎችም ምን ከብቶች ብቻ ብለው በየ ኢንተርኔቱ የተጎሳቆሉ ዜጎችን ፎቶግራፍ፣ ወደ ከተማ ፈልሰው በልምና ላይ የሚገኙ ባላገሮችን ፎቶግራፍ፣ ከዛም አልፎ በየራዲዮ ጣቢያው የድረሱልን ጥሪን የሚያሰሙ ዜጎችን ድምጽ አሰሙን። ባለሥልጣኖቻችን ግን ይሄኔም፤ «ድርቅ እንጂ ርሃብ የለም፤ ርሃቡን ለመመከት መንግሥታችን በቂ ሃይል አለው» አሉን። (ነይ ቅንፍ በሉልኝ፤ እና በቅንፍ... በሌላ በኩል ደግሞ ረጂ አካላት ለድርቁ በቂ ድጋፍ አልሰጡንም እያሉ በሌላ በኩል ሲያጉረመርሙ የምንሰማቸው ባለሥልጣናትም አሉ) በርካታ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና አጋጣሚውን አግኝተው ርሃቡ አለ የተባለበት ቦታ ሄደው የዘገቡ ጋዜጠኞች እንዳሳዩን እና እንደነገሩንም ቢያንስ ቢያንስ ድርቁ በጣም የከፋ ርሃብ ይዞ እየመጣ ነው።

ታድያ ይሄን ጊዜ መንግሥታችን ጉራውን ተወት አድርጎ፣ ለእነ አባይ ግድብንም ሆነ ለእነ አባይ ጸሐዬን የሚዋጣውን ወጪ ገታ አድርጎ ምናለ ለወገን እንድረስ ጎበዝ እንረዳዳ ብሎ ቢል ምን ነውር አለው! (ለነ አባይ ጸሀዬ የሚዋጣውን ወጪ ያልኩት ከአባይ ግድብ ጋር ስማቸው ስለተገጣጠመልኝ ጨዋታው እንዲያምር ብዬ እንጂ ከአባይ ግድብ መዋጮ ላይ እነርሳቸው ድርሻ አላቸው ለማለት ፈልጌ እንዳይመስልብኝ አደራ...)

በጥቅሉ በዚህ በቴክኖሎጂ ዘመን የአስራ አምስት ሚሊዮን ህዝብን ርሃብ መደበቅ ማለት ግመል ሰርቆ አጎንብሶ ነውና መንግሥቴ ጥሞና ሰጥቶ እንዲያስብበት አደራ እላለሁ ብሏል ብለው ይንገሩልኝ ወዳጄ.....(ራስህ ንገር አሉኝ እንዴ...)

እስቲ ለዛሬ እዚህ ላይ ይብቃኝ እና ሌላ ጊዜ ሰላም ያገናኘን ብዬ ልሰናበትዎ...

አማን ያሰንብተን!

‹‹አላየንም፣ አልሰማንም፣ አንናገርም››

ሃና ረጋሳ

በሀገራችን ስለግብረ-ሰዶም ምንነት እንኳን በቅጡ የማያውቁ ብዙ የኅብረተሰብ ክፍሎች በመኖራቸው መንግሥት ይህን እንደ አንድ ማኅበራዊ ቀውስ ወስዶ በጊዜ ግንዛቤ ማስጨበጥ እና በዚህ ነገር ኅብረተሰቡን እየበከሉ የሚገኙትን ወንጀለኞች ተመጣጣኝ የሆነ እና አስተማሪ የሆነ ፍርድ በመስጠት መስራት እንዳለበት ይሰማኛል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 19 ላይ እንዲህ ሰፍሯል፡-

«ለሰዶምና ገሞራ በሚባሉ ስፍራዎች ውስጥ እጅግ ሀጢያት ሰፍኖ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም በእነዚህ ሀጢያተኞች እጅግ ተቆጣ፡፡ እነዚህ ህዝቦችም በተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት ተለክፈው ነበር፡፡ እግዚአብሔርም በሰዶምና ገሞራ ከተሞች ላይ እሳትና ዲን ከሰማይ አዘነበ፡፡ እነዚህን በተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት ተለክፈው የነበሩትን የሶዶምና ገሞራ ህዝቦች ደመሰሰ»

እንግዲህ ግብረ-ሰዶም (Homo sexuality) በተመሳሳይ ጾታ መካከል የሚደረግ ግንኙነት ማለት ነው፡፡ ግብረ-ሰዶም በሀገራችን ኢትዮጵያ በባህልም በኃይማኖትም የተወገዘ ነገር ቢሆንም ባደጉ ሀገሮች ግን ለምሳሌ አሜሪካ፣ ስዊድን፣ እንግሊዝና ደቡብ አፍሪካ የመሳሰሉት ደግሞ ህጋዊ ጋብቻ መፈጸም እንዲችሉ በሕጋቸው ላይ አስፍረዋል፡፡

በታህሳስ ወር 2004 ዓ.ም የወጣው የኒውዮርክ ታይምስ ዘገባ፣ አሜሪካ ለደሃ ሀገራት የምታደርገው ልገሳ (ዕርዳታ) ለሰዶማዊያን መብቶች መጠበቅ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ያማከለ እንደሚሆን ገልጻለች፡፡ ለተቋማቱም የሚሰጡት እርዳታ፣ ከዓላማቸው ጋር ለሚመሳሰሉት እንደሚሆን አስታውቀዋል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ስዊድንም ዕርዳታ የምትለግሳቸው እንደኢትዮጵያ በመሳሰሉ ታዳጊ ሀገሮች ግብረ-ሰዶም ወንጀል መሆኑን ወቅሳ፤ የተመሳሳይ ጾታ ግንዛቤ እንዲሰርጽ እና ወንጀል መሆኑ እንዲቀር እንደምትሰራ «ሲዳ» በተባለው የዕርዳታ ሰጪ ድርጅቷ ድህረ-ገጽ በኩል ከዓመታት በፊት ይፋ አድርጋለች፡፡

የሰው ልጅ ለአንድ ሀገር ትልቅ ሀብት መሆኑ እሙን ነው፡፡ ከተቃራኒ ጾታ ጋር የሚደረግ ግንኙነትም ትውልድ እንዲበዛና እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡ ሰዶማውያን ከሚወገዙበት ምክንያቶች ዋነኛው የትውልድ ምክነት ስለሚያስከትል ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ትውልድ ሊቀጥል አይችልም፡፡

ሰዶማዊነት ለትውልድ ምክነት ከመዳረጉም በተጨማሪም ለከፍተኛ የሥነ-ልቦና ቀውስ እና ለተለያዩ በሽታዎች እንደሚዳርግ የህክምና ባለሙያዎች ይገልጻሉ፡፡ ከሚያስከትላቸው በሽታዎች ውስጥም የትልቁ አንጀት መቁሰል፣ ኪንታሮት፣ የፊንጢጣ መሰንጠቅ፣ የጉበት በሽታና ኤች.አይ.ቪን ለመሳሰሉት በሽታዎች እንደሚያጋልጥ በዘርፉ ጥናትና ምርምር ያደረጉ ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡

ባለሙያዎቹ እንደሚገልጹት ከሆነ፣ ሰዶማዊነት ተፈጥሯዊ ክስተት ሳይሆን ሰዎች ወደዚህ ህይወት በብዛት የሚገቡት በልጅነታቸው በሚደርስባቸው ሥነ-ልቦናዊ ቀውስ እና ማኅበረሰቡ በሚያሳድርባቸው ተጽዕኖ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ አንድን ወንድ ህጻን እንደሴት ማሳደግ ማለትም በአለባበስ፣ስማቸውንበሴትበመጥራትናበመሳሰሉትነው፡፡

ግብረ-ሰዶም በሃገራችን ኢትዮጵያ በባህልም፣ በሃይማኖትም የተወገዘ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ግብረ-ሰዶም ወንጀል መሆኑን በወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 629-632 ላይ እንዲህ ሰፍሯል፡-

«ማንም ሰው ከእርሱ ጋር አንድ ዓይነት ጾታ ካለው ሌላ ሰው ጋር ግብሩ ተቃራኒ የሆነ ግብረ-ሰዶም ወይም ለንጽህና ወይም ለመልካም ጠባይ የሆነውን ሌላ ድርጊት የፈጸመ እንደሆነ በቀላል እስራት ይቀጣል፡፡»

ነገር ግን፣ ወንጀሉን የሚያከብዱ ዝርዝሮችም ተቀምጠዋል፡፡ ለምሳሌ፣ ድርጊቱ የተፈጸመበት ግለሰብ ከ18 ዓመት በታች ሆኖ ሲገኝ ወይም ድርጊቱ የተፈጸመበት ሰው በሥነ-ልቦና ቀውስ ህይወቱን ካጠፋ በቅጣት ማክበጃ እስከ 15 ዓመት ፅኑ እስራት እንደሚያስቀጣ በወንጀል ሕጉ ከአንቀጽ 626-632 ሰፍሯል፡፡

ግሎባል አቲቲዩድስ የተባለ ድርጅት በ2007 እ.አ.አ አደረኩት ባለው ጥናት፤ ከ44 ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ ከማሊ ቀጥላ 97 በመቶ ህዝቧ ሰዶማዊነትን እንደሚያወግዝ አስታውቋል፡፡

ይህ ሁሉ የሆነባት ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ፣ «ሰዶማዊነት ምን ደረጃ ላይ ነው ያለው?» ብለን ስንጠይቅ፣ በጣም የሚያስደነግጥ ነገር ነው የምንሰማው፡፡ በከተማችን አዲስ አበባ ብቻ ከ40ሺህ በላይ የሚገመቱ ሰዶማዊያን እንደሚገኙ ይነገራል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን፣ ከዓመታት በፊት «በሴቭ ዘ ችልድረን ካናዳ» እና "በብራይት ፎር ችልድረንስ አሶሴሽን» ትብብር የተካሄደ ጥናት እንዳመለከተው፣ በአዲስ አበባ ከሚፈጸሙ የአስገድዶ መደፈር ወንጀሎች መካከል 22 በመቶ የተፈጸሙት በወንዶች ላይ ነው፡፡ (አሁን ቁጥሩም ጨምሮም ሊሆን ይችላል) እነዚህ ወንዶች የተደፈሩትም ተመሳሳይ ፆታ ባላቸው ሰዎች ነበር፡፡

ለዚህ ሰዶማዊነት ተጋላጭ ከሆኑት የኅብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ አብዛኞቹ ራሳቸውን መከላከል የማይችሉ ህጻናት፣ አካል ጉዳተኞች፣ እርዳት የሌላቸው አረጋዊያንና በጎዳና ተዳዳሪነት ህይወታቸውን የሚመሩ የኅብረተሰቡ አካላት ዋነኞቹ የጥቃቱ ሰለባዎች ናቸው፡፡

በዚህ ጨለማ ህይወታቸውን እየገፉ የሚገኙ ወገኖች፣ ለዚህ ነገር እንዴት እንደተዳረጉ ሲገልጹም፤ አብዛኞቹ በልጅነታቸው በቅርብ የቤተሰብ አካል፣ ጓደኞችና መምህራኖቻቸው ጥቃት (ግፊት) እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

ታዲያ ይህ ከፍተኛ ሥነ-ልቦናዊ እና ማኅበረሰባዊ ችግር እያስከተለ የሚገኝ እውነታ ሥር እየሰደደ፣ ባህላችንን እየበረዘና እያጠፋ እንዲሁም የኃይማኖትን ሕግ የሚቃረን ሆኖ ሳለ ስለምን «አላየንም፣ አልሰማንም፣ አንናገርም» ብለን በራችንን ዘግተን ቁጭ አልን?!

እኔ እንደሚገባኝ ከሆነ «ሰዶማዊነት የኢትዮጵያ ችግር አይደለም» የሚባልበት ጊዜ ያለፈ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ብዙ ነገሮች ድብቅ ነው እንጂ በመዲናችን ሰርግ ደግሰው ጋብቻ እየፈጸሙና ሀገራችን ውስጥ ማኅበር መስርተው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ፡፡

ስለዚህ ምን ይደረግ? ዝምታው ይሰበር! ኤች.አይ.ቪ. ሲሸፋፈንና ሲድበሰበስ ምን ያህል ጥፋት እንዳደረሰ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡ በመሆኑም ያኔ ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ላይ በአንድነት ከግለሰብ እስከ መንግሥት ድረስ መነቃቃት መፍጠር እንደተቻለ ሁሉ፤ አሁንም በግብረ-ሰዶም ዙሪያ አንድነታችንን አሳይተን ከመካከላችን ቀርፈን ማውጣት ይኖርብናል፡፡ አለበለዚያ ግን ውጤቱ ምን ሊያስከትል እንደሚችል ለማየት ጥቂት ዓመታት ብቻ መጠበቅ ነው፡፡

በመጨረሻም በሀገራችን ስለግብረ-ሰዶም ምንነት እንኳን በቅጡ የማያውቁ ብዙ የኅብረተሰብ ክፍሎች በመኖራቸው መንግሥት ይህን እንደ አንድ ማኅበራዊ ቀውስ ወስዶ በጊዜ ግንዛቤ ማስጨበጥ እና በዚህ ነገር ኅብረተሰቡን እየበከሉ የሚገኙትን ወንጀለኞች ተመጣጣኝ የሆነ እና አስተማሪ የሆነ ፍርድ በመስጠት መስራት እንዳለበት ይሰማኛል፡፡

እንዲሁም ወደዚህ ህይወት ሳይፈልጉ ገብተው እየተሰቃዩ ያሉትን ወገኖችን ከማግለል ይልቅ በሥነ-አዕምሮ የህክምና ባለሙያዎች ህክምና የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል፡፡በመንግሥትደረጃምሆነበኅብረተሰቡ ዘንድ አለበለዚያ ግን ይህን ጉዳይ «ሳይቃጠል በቅጠል» ብለን ሁላችንም ካልተረባረብንበት እና ሀገራችን ስትጠፋ ዝም ብለን ከተመለከትን ኅብረተሰቡም ከታሪክ ተጠያቂነት መንግሥትም ከህሊና ፍርድ የሚድን አይመስለኝም፡፡

የፊልም ፖስተር Vs የቤተሰብ ፎቶ

ደረጀ ታደሠ

አንድ ፊልም በደራሲው ምናብ ውስጥ ተወልዶ፣ በዳይሬክተሩና በስሩ ባሉት የተለያዩ ባለሙያዎች ስር አልፎ ለዕይታ ይቀርባል፡፡ በዚህ ሂደትም ውስጥም ታሪኩን የሚገልጽና የሚመጥን፣ ዋነኛው ዓላማው ፊልሙን ማስተዋወቅ የሆነ ፖስትር መስራት የተሟላ ፊልም መገለጫ ነው፡፡

የፊልም ፖስተር የማስታወቂያነት ዓላማውን በሚገባ ሊያሳካ የሚችለው፣ ሙያዊ አሰራሩንና ጥበባዊ ልኩን ጠብቆ የተሰራ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ይህ ካልሆነ ግን፣ መጽሐፍ በሽፋኑ እንደማይለካው ሁሉ፤ ከፊልሙ ዋና ታሪክ ደረጃ ዝቅ፣ አልያም ከፍ ካለ ተመልካቾቹን ከማበሳጨት በተጨማሪም ፊልም ሰሪውን በጅምላ ከማስወቀስ አይተርፍም፡፡

የፊልም ፖስተር በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ታሪካዊ ዳራ ስንመለከት እ.አ.አ በ1990 ዓ.ም "Projection Artistries" ለተሰኘ አጭር ፊልም በጁለስ ቸሬት የተሰራው ፖስተር በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የመጀመሪያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የዚህ አጭር ፊልም ፖስተር፣ የፊልሙን አንድ ክፍል በፎቶ መልክ ይዞ ፊልሙ የሚቀርብበት ሰዓት ተጽፎበት በቴአትር ቤት በር ላይ በሰው ተይዞ የሚታይ ነበር፡፡ በሙሉ ፊልም (Feature Film) ደረጃ ግን የመጀመሪያው እ.አ.አ 1895 "L' Arroseur Arrose" ለተሰኘው ፊልም በማርሴለን አውዞል አማካኝነት የተሰራ ፖስተር ነው፡፡ ከዚህ ዘመን በኋላ የፊልም ፖስተር ስራ በባለሙያዎቹ ዘንድ ትልቅ ተቀባይነት አግኝቶ በሰፊው መዘውተር ጀመረ፡፡ በየወቅቱ ጥበባዊ ፋይዳው ከፍ እያለ፣ የራሱ መለኪያ ወጥቶለት አሁን ባለው ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ እዚህ ጋር ታዲያ ሁለት ጥያቄዎችን መነሳታቸው አይቀርም፤ የመጀመሪያው የጥባዊ ፋይዳ ምንነት ሲሆን በሁለተኛነትም የመለኪያ መስፈርቶቹ ምንነት ነው፡፡ ከሁለተኛው ጀምረን በአጭሩ መልስ እንስጥ፡፡

የፊልም ፖስተር በጥሩነት አልያም በተቃራኒው ሊፈረጅ የሚችለው በመለኪያ መስፈርቶቹ ሲመዘን ነው፡፡በዚህም ዋና ዋናዎቹ የልኬት መሠረታዊያን የሚከተሉት ናቸው፡፡

ትኩረት ሳቢነት፡- የገጸ-ባህሪያት አንዳች እንቅስቃሴ ወይም ዋነኛ ሴራውን ተንተርሰን ሲሰራ በከፍተኛ ደርጃ ትኩረት ይስባል፡፡

ከመንገር ማሳየት፡- የፊልሙን ዋነኛ ጭብጥ በገጸ-ባህሪ አልያም በሌላ ቁስ እንደአስፈላጊነቱ አቅርቦ (close-up) በትክክለኛ ምስል ወይም በስዕላዊ መግለጫ ማሳየት፡፡ ይህም ፊልሙ ስለምን እንደሆነ ፍንጭ ይሰጣል፡፡

ፍላጎት መጨመር፡- የፊልም ፖስተር ተመልካች፣ ፊልሙን እንዲመለከት ፍላጎቱን የሚጨምር መሆን አለበት፡፡ የፊልም ፖስተር ተመልካቹን ወደ ታሪኩ በመጋበዝ «ምን እና እንዴት ሆነ?» የሚል ጥያቄ የሚያጭር መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ለጥያቄዎቹ መልስ ለማግኘትም ፊልሙን መመልከት የውዴታ ግዴታ ይሆንበታል፡፡

ወጥነት ያለው፡- የፊልም ፖስተር ወጥነት ያለው፣ በማንኛውም ጊዜ የፊልሙን ታሪክ ወክሎ ሊቆም የሚችል፣ ግልጽና ትክክለኛ መልዕክት የሚያስተላልፍ መሆን አለበት፡፡

አግባብነት ያለው፡- የፊልም ፖስተር ፊልሙ ከያዘው ታሪክ ጋር የሚሄድና ፊልሙን የሚያመለክት መሆን አለበት፡፡ ይህ ካልሆነ ግን አግባብነት ይጎድለዋል ማለት ነው፡፡

የፊልም ፖስተር መሠረታዊ መለኪያ ነጥቦቹ ከላይ የቀረቡት ናቸው፡፡ ታዲያ እነዚህን መለኪያ መስፈርቶች ካወቅን በቀላሉ ጥበባዊ ፋይዳውን መገንዘብ ያስችለናል፡፡ በዚህም ፊልሙን በትክክለኛው መንገድ ማስተዋወቅ፣ የፊልም ተመልካቹን ማማረክ፣ ማርኮም ሲኒማ እንዲመጣ አልያም ዲቪዲ (DVD) ውን እንዲገዛ ውስጣዊ ፍላጎት መፍጠር፣ የሰራነውን ፊልም ስለምን እንደሆነ መጠቆም ... ወዘተ፡፡ ይህ ፋይዳውም የፊልም ሰሪውን ከማሳደግ አንጻር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

ቀጥለን የፊልም ፖስተር ስንሰራ ወይም ለመስራት ስናስብ መገንዘብ የሚገቡን ዋና ዋና ነጥቦችን በአጭሩ እንመልከት፡፡

ድባብ፡- የፊልሙ አጠቃላይ ድባብ ምንድን ነው? ለመስራት ያቀድነው ፖስተር ምን አይነት ፊልም የሚወክል ነው? ፖስተር ከመስራታችን በፊት ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ማግኘት አለብን፡፡ ፊልሙ በድርጊት የተሞላ (Action) ወይም አስፈሪ (Horror) ከሆነ ጨለም (ጠቆር) ያለ ድባብ ያስፈልገናል፡፡ ፊልሙ አስቂኝ ከሆነ ደግሞ የበራና የደመቀ ድባብ መፍጠር ይገባል፡፡

ጽሑፍ፡- የፊልሙን ርዕስ ጨምሮ በፖስተር ላይ የምንጽፋቸው ነገሮች በጣም ወሳኝ ናቸው፡፡ ፊልሙ መሪ ቃል (tag line) ያስፈልገዋል፡፡ አዘጋጁ፣ ደራሲው፣ ፕሮዲውሰሩ፣ ዋና ዋና ገጸ-ባህሪያትን ወክለው የሚጫወቱ ተዋንያውያንን፣ በፊልሙ ዝግጅት ሂደት ሰፊ ቦታ የነበራቸው ባለሙያዎች ስምና የሥራ ድርሻ መጻፍ ይኖርበታል፡፡

ምስል፡- ይህ የፊልም ፖስተር ዋነኛ ገጽታ በመሆኑ ጎልቶ መታየት ይኖርበታል፡፡ምናልባት በሙሉ ፊልም ውስጥ ለፖስተር የሚሆን ጥሩ ምስል ከሌለ በተምሳሌታዊነት ሊቆም የሚችል ሌላ ምስል መጠቀም እንችላለን፡፡

እንግዲህ እስከአሁን ድረስ የፊልም ፖስተር መሠረታዊያንን ተመልክተናል፡፡ይህንኑ ጥበባዊ ሁኔታ ተንተርሰን በሀገራችን የሚሰሩ የፊልም ፖስተሮችን ጠቅለል አድርገን በወፍ በረረ እንቃኝ፡፡

በሀገራችን የሚሰሩ የፊልም ፖስተሮችን ከላይ በቀረቡት መሠረታዊያን ልኬት ብመዝናቸው አብዛኞቹ ከጥራት በታች ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በርግጥ በተወሰነ ደረጃ አልፎ አልፎ ብቅ የሚሉ፣ ጥበባዊ ገጽታቸው የተሻለ የሚባል ፖስተሮች የሉም ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን፣ በየጊዜው ከሚወጡ ፊልሞች አንጻር ኢምንት ናቸው፡፡

በአብዛኛው በግሌ የምታዘባቸው የሀገራችን የፊልም ፖስተሮች ችግር መልዕክት ላይ ነው፡፡ ፖስተሮቹ የሚያስተላልፉት መልዕክት የለም፡፡ የፊልሙን ድባብ ሆነ ዘውግ መጠቆም የማይችሉ፣ በደፈናው የገጸ-ባህርያትን ምስል አልያም የተዋንያኑን ፎቶ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ፖስተሩን ለሚመለከት ሰው «ፊልሙ እንደዚህ ዓይነት ነው?» የሚል ጥቆማ የመስጠት አቅም የላቸውም፡፡ ተመልካቹ በፍቃዱ፣ ወድዶ እንዲገደድ የሚያደርግ የጥራት ደረጃ በሰፊው ይጎድላቸዋል፡፡

«ከጥሩ የፊልም ፖስተር በስተጀርባ፣ መልዕክት ወይም ሀሳብ መኖር አለበት» ይላል የፊልም ፖስተር አርቃቂ የሆነው ፕሩዴንሲዎ፡፡ ይህ መልዕክት ወይም ሀሳብ ፖስተሩን ለሚመለከተው ሰው የሚያስተላልፈው ነው፡፡ በዚህ መንገድ አብዛኞቹ የሀገራችን የፊልም ፖስተሮች ቢለኩ መልሱ «ምንም!» ይሆናል፡፡ በርግጥ ፖስተር ሊያስተላልፍ የሚችለው መልዕክት ከፊል ታሪክ፣ ዝግጅትና ዘውግ የሚጨልፍ ነው፡፡ [ስለዚህ ሶስት ነገሮች በቀጣይ ህትመቶች በሰፊው የምንመለከትው ይሆናል] ከሶስቱ ነጥቦች ቢያንስ አንዱ ደረጃውን ጠብቆ ካልተሰራ የፖስተር መልዕክታዊነት ከየትም ሊመጣ አይችልም፡፡ ምክንያቱም ንጹህ ውሃ ለመጠጣት አስቀድመን የመቅጃውን ንጽህና መጠበቅ ይኖርብናልና ነው፡፡

ተዋንያኑ ሰብሰብ ብለው የተነሱትን፣ አልያም ገጸ-ባህሪያቱ ምክንያት አልባ የሆነና ምንም ነገር የማይገልጽ አንዳች እንቅስቃሴ ሲያደርጉ የሚያሳይ ምስል በፖስተር ማውጣት በሀገራችን በስፋት የሚዘወተር ተግባር ነው፡፡ በላያቸው ላይ የሚጻፉትን ጽሁፎችን አውጥተን ብንመለከት ከፊልም ፖስተርነት ይልቅ ቤተሰባዊ ፎቶነታቸው ጎልቶ ይታየናል፡፡ አንድ ቤተሰብ ወይም ጓደኛሞች ስብስብ ብለው የተነሱትን የማስተዋሻ ፎቶ እንጂ ጥበባዊ ፋይዳ ያለው የፊልም ፖስተር አይመስሉም፡፡

ለዚህ ክስተት ዋነኛ ምክንያት ተደርጎ የሚወሰደው (በዚህ ዘርፍ ብቻ የሰለጠነ ባለሙያ አለመኖሩ እንዳለ ሆኖ) በግድ የለሽነትና ጥራዝ ነጠቅ በሆነ ድፍረት መስራቱ ነው፡፡ እኔም ይህንን ደፍሬ እንድጽፍ ያስገደደኝ ነገሩ ትኩረት፣ጥንቃቄና ማስተዋልን እንጂ የግድ የሌለንን ነገር የሚጠይቅ አለመሆኑ ነው፡፡ቢያንስ የተለየ ትምህርትና እውቀት ሳያስፈልገን ባለን ነገር ላይ ትንሽ ንባብ አክለን በትኩረት ብናብ የተሻለ ነገር መፍጠር እየቻልን ከባድ ድፍረትና ግደሌሽነት ውጪ በየትኛውም መንገድ ሊታይ ይችላል፡፡በርግጥ ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ ስራ ለመስራት በመስኩ የተማረ ባለሙያ ቢኖር የተሸለ ነበር፡፡ ነገረ ግን የባልሙያ አለመኖር ጥሩ ስራ ከመስራት ሊያግደን አይገባም፡፡ ሌላው ይቅርና በዚህ ዘርፍ የተጻፉ መጽሐፍን ብናነብ አጉል ድፍረታችንን ገፎ ለልኬት የሚያበቃ ነገር እንድንሰራ ያስችለናል፡፡

በፊልም ፖስተር ውስጥ የምናካትታት እያንዳንዱ ነገር ምክንያት ሊኖራት ይገባል፡፡በዘፍቀደ የምናድረው ነገር መኖር የለበትም፡፡ ከምንመርጠው ምስል እስከ ፅሑፋችን ዘዴና ዘይቤ ከጀርባ ምስል እስከ ቀለም አይነትና ምጣኔ ከገጸባህሪው እንቅስቃሴና የፊት ገጽታ እስከ ቁስ አቀማመጥና አወቃቀር ምክንያት ሰጥተን በሃሳብ አስተሳስረን መስራት ይኖርብናል፡፡

በርግጥ በዘርፉም በተራቀቁትም ሀገራትም ጥንቅቅ ብሎ ያለቀለት ስራ ብዙም አይገኝም፡፡ እንደ ጸጉር ስንጠቃ ተፈልፍላ የምትወጣ ክፍተት ትኖራለች፡፡ይህ ግን በእኛ ሀገር ከሚታየው የፈጠጠና ያገጠጠ ሀቅ አንጻር ሲታይ ገና ብዙ መስራት እንዳለብን የጠቋመናል፡፡እናም ይህን ጥበብ ለማሳደግ በርትተን ማንበብ ከተቻለም መማር፣እርስ በርስ ልምድ መለዋወጥ እና ከስህተታችን መማር ይኖርብናል፡፡

ለምንወደውና ለምናከብረው ሙያ ይቺን ትንሽ መስዋት ብንከፍል ቢያንስ የቤተሰብ ማስተዋሻ ፎቶን "የፊልም ፖስተር" ብለን ከመለጠፍ እንታቀባለን፡፡

መልካም ጊዜ!

የኢሕአዴግ የፍትሕ ሥርዓት... ከ ገፅ 15 የዞረ

...ክሶችን ይዘው እንደተከራከሩ ይታወቃል፡፡ በእነዚህ ተግባራዊ ተሞክሮዎ፣ ዜጎች በፖሊስ ተጠርጥረው ከመያዝ ጀምሮ በፍርድ ሂደት ውሳኔ እስከማግኘትና በማረሚያ ቤት ሰብዓዊ መብቶቻቸውን እስከመከበር/አለመከበር ያለው እውነታ ትክክለኛውን የሕግ መርህ የተከተለ ነው ወይስ አይደለም? ወይስ ሁለቱንም የቀላቀለ (ሕግን ማክበርና እንደአስፈላጊነቱ መጣስ)?

ሁለቱን የቀላቀለ ነበር፡፡ ነገሮች ሲከሩ ሙሉ በሙሉ ሕገ-ወጥ ይሆናል፡፡ በአገራችን ላይ መንግሥት በማይፈልጋቸው ሰዎች ላይ የተወሰዱት እርምጃዎች፣ እስራቶችና አያያዞች ተመሣሣይና ሁላቸውም ሕገ - ወጦች ሲሆኑ፤ ይህንን የፈጠረው በአሁኑ ጊዜ ያለው የፍትሕ አካላቱ አመለካከት (attitude) ይመስለኛል፡፡ መንግሥት የጠላቸው ሰዎች፣ የዚህ ሀገር ዜጎች በመሆናቸው ብቻ ሳይሆን ሠው በመሆናቸው የተወሰኑ መብቶች ነፃነቶችና ያሏቸውምና እነዚህም ሊከበሩላቸው የሚገቡ አድርጉ ያለመመልከት ችግር አለ፡፡

ይህንንም የፈጠረው አመልካከት ለራሳችን፣ ለሙያችን፣ ለዜግነታችን፣ ለሰውነታችን የሰጠነው ወይም እንድንሰጥ የተደረገው ዝቅ ያለ አመለካከት ነው፡፡ በዚህች ሀገር ያለው አብዛኛው ራሱን የመጥላትና የማይረባ አድርጉ የመመልከት ሁኔታ ተፈጥራል፤ ይህም በሥራውና ከሌላው ጋር ባለው ግንኙነት ላይ ይንፀባረቃል፡፡ ሁሉም ተጠርጣሪው መብት ያለው አይመስላቸውም፡፡ ከጠበቃ ጋር ለማገናኘት ሲጠየቁ እንኳን፣ የተጠርጣሪውን ቃል ከተቀበሉ በኋላ እንዳይመችህ አድርገው፤ ሰዓቱን አጣብበው ወዘተ ነው የሚያገኙህ፡፡ ከዚህ የምትረዳው፣ በዚህ የተጠራጠሪው (የታሳሪው)ን መብት መፍቀድ ሙሉ በሙሉ አምነውበት ሳይሆን ለማስመሰል የሚያደርጉት መሆኑን ነው፡፡ አለቆቻቸውም አይቆጧቸውም፡፡ በአንዳንድ ቦታ ደግሞ ማን አለቃ፣ ማን የበታች እንደሆነ እንኳን መለየት አትችልም፡፡ በአጠቃላይ፣ «ሕዝብ መብትና ነጻነት አለው» ብሎ፣ ከልብ አምኖ፣ በዚያ መሠረት የሚሠራና ለዚህ የቆመ ፖሊስ እኔ አጋጥሞኝ አያውቅም፡፡ በግል ደረጃ ግን ብዙ ጥሩ ሰዎችን፣ ፖሊሶችን አውቃለሁ፡፡ ሁሉንም ግን አንድ የሚያደርጋቸው፣ ግልጽ ላልሆነ ወገን ጥቅም እንጂ ለሁላችንም በእኩልነት ያለመቆማቸውና እንዲቆሙም የማይገደዱ መሆናቸውን ነው፡፡

የሙስሊም ጉዳዮች መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት፣ በእነኡስታዝ አቡበከር አሕመድ የክስ መዝገብ በነበሩ ተከሳሾች ላይ ባለሳለፍነው ከረምት ወር፣ የፌዴራሉ ፍርድ ቤት እስከ 22 ዓመት የሚደርስ የእስር ቅጣት ጥሎ ነበር፡፡ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላም፣ በአዲስ ዓመት ዋዜማ አምስት ያህል ተከሳሾች «ይቅርታ» በሚል ምክንያት መለቀቃቸው ይታወሳል፡፡ አጠቃላይ የፍርድ ውሳኔውም ሆነ አምስቱም «ይቅርታ» በሚል መፈታታቸውን «የፖለቲካ ውሳኔ ነው» በሚል ብዙ ኢትዮጵያኖች እናምናለን፡፡ በእነአቡበከር እስር እና ክስ ላይ የተመለከቷቸው መሠረታዊ የሕግ ጥሰቶች ምን ምን ናቸው?

እንኳን በምን መመዘኛ የተወሰኑ ሰዎች ተለያተው በምህረት እንደወጡ መረዳት ይቅርና እስከዛሬ እነአቡበከር አሕመድ ምን አጥፍተው እንድታሠሩና አሁንም ድረስ ታስረው እንደሚገኙ እኔ መረዳት አልቻልኩም፡፡ እነአቡበከር የሕዝብ ተወካይ ሆኑ /አልሆኑ፣ ፈጸሙት የተባለው ጉዳይ እንኳን በሽብር ቀርቶ በወንጀል የማያስጠይቅ፣ የተፈቀደ ሕገ-መንግሥታዊ መብት ሲሆን አቀራረቡም ፍጹም ሕጋዊ፣ ሠላማዊና የሰለጠነ ነው፡፡

ሕገ መንግሥት ሕግ ነው፣ ሥራ ላይ መዋል ያለበት ሕግነው፡፡ በእኛ ሀገር ግን እንዲመለክበት እንጂ እንዲተረጉም ወይም በሥራ ላይ እንዲውል ያልተፈለገውን ሕገ መንግሥት በተግባር ሥራ ላይ እንዲውል መንግሥትን ወጥረው የጠየቁት የመጀመሪዎች ሰዎች ስለሆኑ ይህ ምሳሌነታቸው ስላልተወደደላቸው የታሠሩ ይመስለኛል - እነአቡበከር፡፡

በወንጀል ሕግ መርህ፣ ለመንግሥት በግልጽ ያልተፈቀደ ሁሉ የተከለከለ ሲሆን ለተከሳሽ ግን ያልተከለከለ የተከሳሽ (burden) ከፍ ማድረግ በወንጀል ሕግ መርህ በትርጉም ሰም ማለት ነው፣ አይቻልም፡፡ በእኛ ሀገር እየተፈጸመ ያለው የመንግሥትን ለተከሳሽ፣ የተከሳሽን ለመንግሥት አቀያይሮ የመንግሥትን ጫና አሳንሶ የተከሳሹን የማክበድ ሁኔታ ነው፡፡ ፍፁም ሕገ ወጥ የሆነ አሠራር ነው፡፡

ፍጹም ሠላማዊ፣ ሕጋዊ፣ ሰብዓዊና ጨዋ መሆናቸው ደግሞ «ይኸው አላልንም» ብለው ለሌላው ማሳየትን የዘወትር ተግባር ላደረጉ ወገኖች ምቹ ሁኔታ ባለመፍጠሩ ሁሉንም ነገር ዓይን ባወጣ መንገድ በመፈጸም እንዲጋለጡ በማድረጉ ያሰሯቸውን ወገኖች የበለጠ ያበሳጫቸው ይመስለኛል፡፡ በእነአቡበከር ክስ ላይ የተፈጸሙትን የሕግ ጥሰቶች ሳይሆን፣ የትኛው የሕግ ጥሰት ያለመሆኑን ብትጠይቀኝ ይሻላል፡፡ እኔ እነአቡበከር ጋር ሄጄ ፍ/ቤቱ ወይም ፖሊስ ጣቢያ፣ ወይም ወህኒ ቤት በቴሌቪዥን ይሁን በሬዲዮ ወይም በጋዜጣ ስለእነሱ ተነግሮ መብታቸው ሳይጣስ የቀረበትን ሁኔታ አላስታውስም፡፡ በሥርዓቱ እንደእነርሱ የተጠላ ወገን አይቼ አላውቅም፡፡ የሚገርመው ግን፣ እነሱ ለማንም ያንን ያህል የመረረ ጥላቻ የሌላቸው መሆኑ ነው፡፡ የሚጠሉት ሰውን ሣይሆን ኢ-ፍትሐዊነትን ነው፡፡ ይህንን የነገርኩት አንዱ ወዳጄ ግን፣ «እኛ እንወዳቸዋለን» ብሎኛል፡፡ ፈጣሪ የወደደውን ነውና ሰውም የሚወድደው ፈጣሪም ይወዳቸዋል ብዬም አምኛለሁ፡፡

የኢትዮጵያን የፍትሕ ሥርዓት ፍጹም እርቃኑን ያስቀረው የሙስሊሙ እንቅስቃሴና የእነአቡበከር አሕመድ በፍ/ቤት እና በሕጋዊ መልኩ መብታቸውን ለማስከበር ያደርጉት እንቅስቃሴ መሆኑን አምናለሁ፡፡ ውሳኔ ከተለፈባቸውም በኋላ ለሌላው ሰው በሁለተኛ ቀን የሚሠጠው የውሳኔ ግልባጭ ሳይሰጣቸው ከአምስት ወራት በላይ መቆየቱም የእነሱን ሁኔታ የተለየ መሆኑን ያስረዳል፡፡

እኔ አሁን ስላለንበትም ሁኔታ ለመረዳትም (ለማወቅ) ይሁን መፍትሄ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የእነአቡበከር አሕመድንና የሙስሊም ኢትዮጵያኑን የመብት ጥያቄና አቀራርብን በጥልቀት መመርመር በቂው ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ምናልባት፣ እንደሀገር ንሰሃ መግባት ካለ፣ ያንን ማድረግ ያለብን በእነአቡበከር ላይ ስለሆነው ጉዳዩ ይመስለኛል፡፡

ሕጉ የሚለው ከዚህ ተቃራኒውን ነው፡፡ በፍ/ቤት የተወሰነበት ግለሰብ ይግባኝ አቅርቦ ባለበት ወቅት፣ ጉዳዩ (ይግባኙ) የመጨረሻ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ በበታች ፍ/ቤትም በዋስ ከነበረ፣ የዋስትና ጥያቄ አቅርቦ ተፈቅዶለት ውጪ ሆኖ መከራከር ስለመቻሉ ነው፡፡ ይህ የተከሳሹ መብት እንጂ የመንግሥት አይደለም፡፡ በወንጀል ሕግ መርህ፣ ለመንግሥት በግልጽ ያልተፈቀደ ሁሉ የተከለከለ ሲሆን ለተከሳሽ ግን ያልተከለከለ የተከሳሽ (burden) ከፍ ማድረግ በወንጀል ሕግ መርህ በትርጉም ሰም ማለት ነው፣ አይቻልም፡፡ በእኛ ሀገር እየተፈጸመ ያለው የመንግሥትን ለተከሳሽ፣ የተከሳሽን ለመንግሥት አቀያይሮ የመንግሥትን ጫና አሳንሶ የተከሳሹን የማክበድ ሁኔታ ነው፡፡ ፍፁም ሕገ ወጥ የሆነ አሠራር ነው፡፡

ከአንድ ዓመት በላይ በሀገራችን ትልቅ መነጋገሪያ ከሆኑት ጉዳዮች መካከል አንዱ፣ የግንቦት ዋና ፀሐፊ የሆኑት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ከየመን አየር መንገድ በሀገሪቷ የደህንነት ሃይሎች ተይዘው ለኢትዮጵያ መንግሥት ተላልፈው መሰጠታቸው መሆኑ እሙን ነው፡፡ አቶ አንዳርጋቸው ኢትዮጵያ ከደረሱ በኋላ ፍ/ቤት መቅረብ እንዲችሉ እህታቸው ከእንግሊዝ መጥተው በስልክ እርስዎን ለጥብቅና እንዳነጋገርዎት ሰምቻለሁ፡፡ ስለዚህ ጉዳይ በጥቂቱ ቢነግሩን? ከዚያም በኋላ ሰውየው በፖሊስ ፕሮግራም ተቀራርቶ መሠራቱ በግልጽ በሚስተዋል ዶክመንተሪ ፊልም ላይ ሲናገሩ ከመታየታቸው ውጪ ፍርድ ቤት አልቀረቡም፡፡ በትክክል የት እንደታሰሩም በግልጽ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ በዘመድ አዝማድም በግልጽ ሲጠየቁ አልታየም፡፡ ሌሎች በሽብር ወንጀል ተጠርጥረው የተከሰሱ ዜጎች «በክሱ ላይ ስማችን ከአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ጋር ስለተጠቀሰ እሳቸው መከላከያ ምስክር ይሁኑልን» ብለው ጉዳያቸው እየታየ በሚገኘው ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተደጋጋሚ ቢያመለክቱም የቃሊቲ ማረሚያ ቤት «አቶ

→

በአቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ላይ የተፈፀመው ሁሉ፣ ምንም ዓይነት የዓለም አቀፍም ሆነ የሀገርውስጥሕግድጋፍየሌለውከሞራልም ከግብረገብነትም ሆነ ከኃይማኖት አንጻር ሃጢያት የሆነ፣ ጸያፍና ነውረኛ ድርጊት ነው፡፡ ምንም የሕግ ድጋፍ የለውም፡፡

አንዳርጋቸው ቢቃሊቲ የሉም» የሚል መልስ በጽሑፍ ለችሎቱ አቅርቦ ነበር፡፡ ከሕግ መርህ አኳያ አቶ አንዳርጋቸው ላይ እየሆነና እየደረሰ ያለው እውነታ ምንድን ነው?

ለአቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ጠበቃ እንድሆንላቸው በታላቅ እህታቸው ተጠይቄ ፍቃደኝነቴን ገልጬላቸዋለሁ፡፡ እርሳቸውም ከሌሎች የቤተሰቦቻቸው አባላት ጋር አውሮፓ ሄደው ተነጋግረው የወሰኑትን እንደሚያሳውቁኝ ነግረውኝ ሳይደውሉ ቀርተዋል፡፡ በዚህ መካከል እኔ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን፣ ውሳኔዎችን፣ ስለ አያያዛቸው መረጃዎችን፣ ስለ ሕጋዊነቱ ...ወዘተ አስፈላጊ የሆኑ ዓለም አቀፍ ሕጎችን፣ ስምምነቶችን፣ ስለዚያ የተጻፉት'ን ...ወዘተ በማሰባሰብ በተግባርም ሥራው'ን እንዴት እንደምከውነው ዕቅድ እና ቅደም ተከተል አውጥቼ የወረቀት ላይ ሥራውን ወደ ማጠናቀቅ ደርሼ ነበር፡፡ ከዚያ በኃላ ማንም ደውሎም ይሁን በአካል ቀርቦ የጥብቅና ክፍያ ውል መፈጸምን ጨምሮ ሥራውን ቀጥል ባለማለቱ፣ ምናልባትም ለሌላ ጠበቃ ሰጥተው ይሆናል ብዬ ትቼዋለሁ፡፡ በጥብቅና ሥራ ላይ ይህ በብዛት ያጋጥማል፡፡

በዚህ አጋጣሚ የተረዳሁት፣ የአቶ አንዳርጋቸው አያያዝ እና ቀጥሎም የተፈፀመባቸው ሁሉ ምንም አይነት የሕግ ድጋፍ የለውም፡፡ ዝርዝሩን ለመርዳት ያዘጋጀሁትን ወስደህ ማየት ትችላለህ፡፡

በአቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ላይ የሆነውና እየሆነ ያለውን፣ ከሳቸው ጋር በተያያዘ እየተፈፀመና እየተባሉ ያሉት ሁሉ፤ አንተ የጠቀስካቸውን ጨምሮ አንዳቸውም ሕጋዊ አይደሉም፡፡ በሕግ በኩል የጠበቃ እገዛ አግኝተው ቢሆን ኖሮ፣ «ምንም ማድረግ አይችልም» ተብሎ ታስቦም ከሆነ እስከአሁን ድረስ በአካል አግኝቶ ማነጋገርን ጨምሮ፣ ከእሳቸው ጋር በተያያዘ የሆነው ሁሉ ሕጋዊ ትርጓሜው በግልጽ ተቀምጦ መብታቸውን የጣሱ ሁሉ፤ ቢያንስ ቢያንስ ሕጋዊ መስለው በመቅረብ በአደባባይም በቀላሉ ያደረጉትን ወይም ያሉትን ለማለት ባልቻሉ ነበር እላለሁ፡፡

ቢያንስ ቢያንስ ግለሰቡ እንደዜጋም እንደሰውም ይህ ይገባቸው ነበር፤ አሁንም ያገባቸዋል፡፡ ጠበቃ ሊመደብላቸው ይገባል፡፡ በጠበቃ፣ በቤተሰብ፣ በወዳጅ ዘመድ፣ በሐኪም፣ በኃይማኖት አባት መጎብኘት ይኖርባቸዋል፡፡ የሚፈጸምባቸው አዋራጅና ተገቢ ያልሆነ አያያዝ ማለትም፣ ስለሳቸው ፊልም ቀርጸው በአደባባይ በቴሌቪዥን ለሕዝብ ማቅረብን እና የመሳሰሉትን ሊቆምላቸው ይገባል፡፡ በቁጥጥር ሥር ያዋሏቸው ወገኖች፣ እነዚህን ሊያሟሉላቸው ሕጋዊ ግዴታ አለባቸው፡፡ እነዚህን ያለሟሟላትና ግለሰቡን በተገቢው ሁኔታ ክብሩን ጠብቆ ያለመያዝ ሕጋዊ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡ እነዚህን መፈጸም ብቃትን፣ ጥንካሬንና ሰውነትን እንጂ ድክመትን አያሳይም፡፡ ያለመፈጸም ግን ያንን ያሳያል፣ ያስጠይቃል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዶ/ር ቴዎድሮስ አድሃኖም፣ ከጥቂት ወራት በፊት ከአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ጋዜጠኛ ትዝታ በላቸው ጋር ባደረጉት ቃለ-ምልልስ፣ «አንዳርጋቸውን ወደናዝሬት ወስደን ልማቱን እያሳየነው ነው፡፡ መጽሐፍም ጽፎ ጨርሷል፡፡ ኢህአዴግ ቂም በቀለኛ አይደለም፡፡ ...» የሚል ይዘት ያለው አስተያየት ሰጥተው ነበር፡፡ ከሕግ አኳያ፣ የታሰረ ሰው ከታሰረበት እየወጣ ልማት የሚያይበት አግባብ አለ ወይ? በታሰረ ሰው ላይ ፖለቲካዊ ትርፍ ማድረግስ ሕጋዊ ድጋፍ ይኖረው ይሆን?

የታሠረ ሠው ወጥቶ ልማት ለማየት የሚችለው ራሱ ለልማት ሥራ በክፍያ ...ወዘተ ከሄደ ብቻ ነው፡፡ የታሰረ ሰው ሙሉ ክብሩ፣ ስብዕናው፣ ደህንነቱ ...ወዘተ ተከብሮ ከቤተሰቡ፣ ከጠበቃው፣ ከሐኪሙ፣ ከዘመድ፣ ወዳጆቹ፣ ከኃይማኖት አባቱ፣ ... ወዘተ ጋር በሚገናኝበት ሁኔታ መያዝ እንዳለበት በሕገ መንግሥት አንቀፅ ከ19-22 ላይ ተደንግጎ እንገኛለን፡፡ ማንም ሊቀልድበት ቀርቶ በቴሌቪዥን ሊያሣየው አይችልም፡፡ ሰው የሚሰቀል ቢሆን እንኳንከነሙሉ ክብሩነው ያሊፈጸምበት የሚገባው፡፡ ማንም በእሱ ላይ የፖለቲካ ጨዋታ ሊፈጽምበት አይችልም፡፡ በአቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ላይ የተፈፀመው ሁሉ፣ ምንም ዓይነት የዓለም አቀፍም ሆነ የሀገር ውስጥ ሕግ ድጋፍ የሌለው ከሞራልም ከግብረገብነትም ሆነ ከኃይማኖት አንጻር ሃጢያት የሆነ፣ ጸያፍና ነውረኛ ድርጊት ነው፡፡ ምንም የሕግ ድጋፍ የለውም፡፡

የእርስዎ ከጥብቅና ስራዎ ለአንድ ዓመት ከሰባት ወራት መታገድ እንደምታው ምንድን ነው? ጉዳይዎስ ምን ደረጃ ላይ ይገኛል? ወደተከበረው ሥራዎ እንዴትና መቼ ይመለሳሉ ብሎ መጠበቅ ይቻላል?

የእኔ ዕግድ ጉዳይ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ቀርቦበታል፡፡ ዕግዱ ተሽሮ ወደሥራዬ እመለሳለሁ ብዬ እጠብቃለሁ፡፡ ዋናው ቁም ነገር የሚመስለኝ ግን፣ ኢትዮጵያ የሁላችንም ሆና ሁላችንም የተፈጠርንበትን ወይም የነፍሳችንን ጥሪ ወይም ይሆነናል ያልነውን ሙያና ሥራ የሌላውን ተመሳሳይ መብት ሳንጋፋ የፈለግነውን ያህል አርቀን ለማሳደግ የራሳችን ስንፍና ካልሆነ በቀር ሌላ ውጫዊ ገደብ የማይኖርበት ወደ ማድረግ ማቅረብ መቻላችን ነው፡፡ ሰው እንደየስሜቱ በተሰማራበት ሁሉ በሚገባ አፍርቶ፣ ሀገራችንም በእኛ ማድረግ የምታድግ መሆን መቻሏ ነው፡፡ ሆነን የምናደርጋት፣ በቅተን የምናበቃት፣ የበቃችንና የሆነች ሀገር እንጂ የሚፎክርላት ጠጋኝ ፕሮፖጋንዳ የማያሻት ነጻነት፣ ፍትሐዊነት፣ እኩልነት የሰፈነባት ሀገር መሆኗ ነው፡፡

ከዚህ ቅጽበት ጀምሮ ይህ እንዲፈጠር ደግሞ አንዳችን ለሌላኛችን ጠበቃ ሆነን መቆም መጀመር ይኖርብናል፡፡ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለሁሉም እና ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ መብትና ነጻነት፣ እኩልነትና ጥቅም፣ ደህንነት ...ወዘተ ጠበቃ ነኝ ብሎ ለራሱ ነግሮ፣ አምኖ በተግባር መንቀሳቀስ መጀመር ይኖርበታል፡፡ በማንም ላይ የመብት ጥሰት ሲፈጸም፣ በመንግሥቴ፣ «በእኔ ላይ ተፈጸመ» ብሎም መቀበል መቻል ይኖርበታል፡፡ ይህ ሲሆን ሀገራችን የሁላችንም ትሆናለች፡፡ የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ፣ የሁላችንም መብቶችና ነጻነቶች በእኩልነት የተከበሩባት ትሆናለች፡፡ ያ ሲሆን ከነሙሉ ክብሩ ጠበቃነት፣ ዳኝነት፣ ፖሊስነት፣ ዐቃቤ ሕግነት፣ ደህንነት፣ ሠራዊትነት ይገኙና የሚያስከብሩና የተከበሩ ይሆናሉ፡፡ ክብር ሁሉንም በእኩልነት ማገልገል ነውና፡፡

እስከዚያው ድረስ ግን የደረጃ ጉዳይ እንጂ ሁላችንም የፈለግነውን ከመሆን ታግደናል ብዬ ስለማምን በዚህ ረገድ እምብዛም አንበላለጥም፡፡ በዚህ ረገድ የእኔው ሁኔታ የተሻለ የሚሆነው የማንቃት ሁኔታ ስላለበት ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ ከሀገሬ ላይ ማንም ሊያግደኝ ይችላል ብዬ የማላምን መሆኔን ሁሉም እንዲረዳልኝ እፈልጋለሁ፡፡ ሁላችንም በዚህ ማመን አለብን፡፡

ይቀጥላል

የማኅበረሰብ ድረ ገጽ ቆይታችን ትርፍና ኪሳራ

ዩሐንስ ሞላ

ከአዲስ ነገር ጋር የመተዋወቅ መዘዝ

ብዙ ጊዜ ብርቅ የሚሆን ነገር እጅ ላይ ሲገባ ይዞ የሚመጣው የተለየ አባዜም ይኖራል። ለምሳሌ፣ ቴሌቪዥን ከስንት አንዱ ቤት የሚገኝ ብርቅ የነበረ ጊዜ፣ ቴሌቪዥን ባላቸው ቤቶች ዘንድ፣ ቴሌቪዥኑ የሚያገኘው እንክብካቤና፣ ለመመልከት የሚሄዱ ህፃናት የሚያዩት አበሳ አይዘነጋም። ቲቪው ይወለወላል፣ እንደሌማት በዳንቴል ይሸፈናል፣ እየታየ 'ሞቀ አልሞቀ' ተብሎ ትኩሳቱ ይለካል፣ ቅልጥ ባለ አጓጉዊ ፕሮግራም መሀል... ቆይ 'ይቀዝቅዝ' ይባልና ይጠፋል። (እነሱ እንዴት አይጓጉ እንደነበር ይገርመኛል?) ከሚጠበቀው ፕሮግራም ቀደም ብሎ የጎረቤት ህጻናት ቤት በማፅዳትና በመላላክ ያግዛሉ.... ሌላም ሌላም፤ አጀቡ ብዙ ነበረ።

የማቀዝቀዣ (refrigerator) ቴክኖሎጂ ትውውቅ ብርቅ የነበረ ጊዜ፣ «ኡፍ እንዴት ይሞቃል? እስኪ የፍሪጁን ቁልፍ ስጪኝ አየር ልቀበል» ሳይባልም አልቀረም። ተንቀሳቃሽ ስልክ የተዋወቀ ጊዜም፣ በሰልፍ የተገዛችው 'ዳስተር' ስልክ ወገብ ላይ ሻጥ ተደርጋ ስንቱ ላይ ተሸለለ? ስንት ተማለለ? ስንቱ ተንጎማለለ? የሀብትንና የማንነትን ደረጃስ አልመተረም? የስልክ ቀፎ ብርቅ ሲሆንስ፣ ስንት ቀፎ ተገላበጠ? - ሲሆን በእጅ፣ ሲቀር በዐይን።

ፌስቡክ ብርቅ የነበረ ጊዜ፤ ማለቴ አሁን... ብርቅ ስለሆነ ሰው በየቦታው «ፌስቡክ ከፍቼ...» «ፌስቡኬ ላይ...» ይባላል። አማራጭ የወሬ ምንጭና ማስተላለፊያ ሆኖም ያገለግላል። ከዚህ ቀደም የሥነ-ጽሑፍ ባለሞያው ቴዎድሮስ አጥላው «ስለ ፌስቡክ እና የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍ ያስተዋልኩት» ብሎ በሰየማት መጣጥፉ ላይ፣ «ፌስቡክ በአጭሩ በእያንዳንዱ የህይወታችን ጉዳዮች ላይ ጣልቃ የምናስገባው፣ ወይም ጣልቃ ገብቶ የምናገኘው ዓለም ነው:: አቋማችንን፣ የመጻፍ ብቃታችንን፣ ቁንጅናችንን፣ ጭንቀቶቻችንን፣ ደስታዎቻችንን፣ ድንፋታዎቻችንን፣ ሽሙጦቻችንን፣ ነቆራዎቻችንን፣ የስታይል ምርጫዎቻችንን፣ የውሸት ማንነቶቻችንን፣ ማስመሰላችንን፣ ቅን አሳቢነታችንን፣ ዋልጌነታችንን፣ ኃይማኖታችንን፣ ዘረኝነታችንን፣ ገርልፍሬንዶቻችንን፣ ልጆቻችንን፣ ሚስቶቻችንን፣ የሚያስደንቁንን፣ የሚያስቁንን፣ ... ወዘተርፋችንን ሁሉ በግልጽም ይሁን በስውር የምናሳይበት ዓለም ነው::» ብሎ ገልጾት ነበር።

የselfie (በራስ እጅ የተነሳ የራስ) ፎቶ ብርቅም አለ (የተለያዩ አገራት በአንሺዎቹ ላይ የሚደርሰውን የአደጋም ሆነ፣ ሌሎች አገራዊና ማኅበራዊ ስጋቶች በመግለጽ፣ ሰልፊ መነሳትን የሚከለክሉ ህጎችን እየደነገጉ ነው)፤ ደግሞ አለ... - የsmart phone (የዘንጦ ስልክ) ብርቅ። ሰው ሁሉ ፎቶ እያነሳ፣ ቪዲዮ እየቀረፀ የመዘገበውን ወደ ማኅበረሰብ ትስስር ገጾች ጎራ ብሎ ያጋራል። እየጨሰና እያጨሰ ለጓደኞቹ ያሳያል። የኢንተርኔት፣ የselfie እና የቀፎ ብርቅነት ባንድ ላይ ገጥመው፣ ከኮልኮሌ እስከ ረቂቅ ፎቶና ቪዲዮ የማኅበረሰብ ትስስር ገጾችን ስለሞሉት፣ ነባር ተጠቃሚዎችን ወሰድ መለስ ያደርጋቸዋል። መቼም የእኛ ሰው፣ መቅረጹን ይቻል እንጂ፣ ይቀረፅለት እንጂ... ስልኩ ባትሪው አይለቅበት እንጂ... ኔትወርኩ አይጥመምበት እንጂ... ሰዉ እንዳያያዘ፣ አቦሬውንም ምኑንም ያየ ያሰበውን ሁሉ ቀርፆ፣ ፎቶ አንስቶና በቃላት አቀናብሮ ሳያጋራም አይቀር። ሆኖም «ሰርዶ ኃይለኛ ንፋስን አጎንብሶ ያልፋል» እንዲባል፣ የነገሮች ወረትና መዘዞቻቸውን እስኪያልፍ ድረስ ባላየ ለማለፍና ድፍርሱ እስኪጠራ፣ ለተወሰነ ጊዜ ራስን ገለል ለማድረግ የታደሉ፣ ብዙ ቆይተው ብዙ ማትረፍና ብዙ ማስተረፍ ይችላሉ።

ፌስቡክ ነፍስ ነገር...



Facebook, please!
I am trying to study!
Check me!
Check meeeee!
facebook

የማኅበረሰብ ትስስር ድረ-ገጾች የሰው ልጆችን በማቀራረብ ረገድ እየተጫወቱ ያሉት ሚና ትልቅነት ተንታኝ አያሻውም። ተጠቃሚዎቹም ሀሳባቸውን በደግነትና በነፃነት እንዲያካፍሉ ረድቷቸዋል። የማያቋርጠው የፌስቡክ 'what is in your mind...?' ጥያቄውን በመመለስ ሰበብም አዕምሯቸውን ለመረዳት እና ሀሳባቸውን ለመግለፅ የሚሞክሩ ብዙ ናቸው። ሰዎች በፃፉት ነገር ላይም ሀሳባችንን እንሰጣለን። ከዚህም ባሻገር ሀገርን፣ ባህልና ችሎታን ከማስተዋወቅና ለሌሎች ከማጋራት አንጻርም የማኅበራዊ ትስስር ገጾች ያላቸው አስተዋጽኦ ይህ ነው አይባልም። በማኅበረሰብ ትስስር ድረ ገጾች ብቻ የሚተዋወቁ ሰዎች ፊት ለፊት ተገናኝተው፣ ከወዳጅነት አልፈው ብዙ ነገር ሲሰሩ፣ ወዳጅነታቸውን ሲያጠነክሩ ተመልክተናል። በተለይ እንደእኛ አገር ባሉ የነጻ ሚዲያ እጥረቶች ላሉባቸው አገራት ነዋሪዎች፣ ከፌስ ቡክ መራቅ እንደ መታፈን ነው። ማረከ አልማረከ፣ ጣፈጠ አልጣፈጠ፣ ታየ አልታየ... ሳይሉ እንደልብ የሚሆኑበትን ቦታ በገዛ ፈቃድ ትቶ መራቅ መወሰን፣ ልሳንን በራስ ፈቃድና እጅ የመዘጋት ያህል ጨቋኝ ውሳኔ ነው። በተለይ የሚናፍቁትና የሚያጎድል ብዙ መኖሩን ሲያስቡ ጭቆናው ይበልጥ ገንኖ ይታያል። ያም ሆኖ መገለሉ የሚሰጠው የጥሞና ጊዜም አለና በዚህ ወቅት የተዘጉበን ልሳናት ናፍቆት እንደ አዲስ ይቀሰቀሳል። በሌላ ሰው ጉልበትና ሀይል የተዘጉ ልሳናትና የታፈኑ አንደበቶች ጉዳይም ከማኅበረሰብ ትስስር ገጾች በራቅን ጊዜ ይበልጥ ይገናል። ቢሆንም፣ ቆይተው መጥተው «በአዲስ መልክ ሥራ ጀምረናል»ን ሳያስነግሩ አሰላለፍ የሚቀይሩ ብዙ ተጠቃሚዎች አሉ።

ፌስቡክ ስንቱን ጉድ የማሰማቱን/የማሳየቱን ያህል፣ ብዙ ጉድ ጋርዶልናል። ብዙ ቆዳዳ ሸፍኖልናል። በብዙ የመከራ ቀናት ተጠቃሚዎቹን እርስ በርስ አጽናኝ ተጽናኝ አድርጎ አስተዛዝኗል። ከብዙ ዓይነት ሰዎችና ጉዳዮች ጋር አቀራርቧል። ብዙ ዓይነት ችግሮች እንዲቀረፉ አግዟል። ብዙ ሰዎችን ለመታዘብና፣ ማንነትን ለመፈተሽ ፌስቡክ ዓይነተኛ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል። ሰው ሲመጣ፣ ሰው ሲሄድ አብሮ ሀሳብ ይመጣል፣ ሀሳብ ይሄዳል። ልማድ ይረሳል፣ ልማድ ይተካል። ጸሐፊዎች ይታሰሩ ይሆናል፣ ጽሑፍን ግን ማን ችሎ ያስራታል? እውነት ተናጋሪዎች ይገላሉ ይሆናል፣ እውነትን ግን ማን ያገኛታል? ጨኸቶች ቢታፈኑስ፣ ልሳናት ላይ ማን ይሰለጥን ዘንድ ይችላል? ስጋ ቁም ስቅሏን ብታይ፣ ነፍስን ግን ማን ያገኛታል? ታዲያ ለታፈኑ ድምጾች፣ ፌስቡክ ነፍስ ነገር ነው። የ'cyber' ዓለም እስትንፋስ ሰው ኖረም አልኖረም ጽዋው አይሞላምና አሰራርና ሰራተኛ እየቀየረ ወደፊት ይጓዛል። በፌስቡክ ብዙ ዓይነት የማስተባበር ሥራዎች ተካሂደዋል። ከቀልብ ማሰባሰብ እስከ ገንዘብ ማሰባሰብ ድረስ የደረሱ ቁም ነገሮች ተከናውነዋል። እንደውም እንደእኛ ባሉ ሀገራት የአጠቃቀማችንም ችግር ተጨምሮበት እንጂ፣ ከጠቀመንም በላይ ይጠቅመን ዘንድ በተቻለው ነበር። ፌስቡክ ባይኖር የሚዳፈኑ ጉዶች፣ ፌስቡክ ባይኖር የማይጻፉ ጽሁፎች፣ ፌስቡክ ባይኖር የማይሰሙ ድምጾች፣ ፌስቡክ ባይኖር የማይታዩ መልኮች፣ ፌስቡክ ባይኖር የማይዘጋጁና የማንታደማቸው መድረኮች፣ ፌስቡክ ባይኖር ተከብረው የሚኖሩ ቀላሎች፣ ፌስቡክ ባይኖር ተዘንግተው የሚኖሩ ክቡዶች፣ ፌስቡክ ባይኖር እንኳን ሰው ባለቤቱም ሳያውቃቸው ይቀሩ የነበሩ የፈጠራ መልኮች... ወጥተዋል። ሰው ያለበት የማሳየት አባዜ የማሳያ ሜዳው ሲኖር ይበልጥ ይበረታልና ብዙ አይተናል፤ ብዙም አሳይተናል።

የማኅበረሰብ ትስስር ድረ ገጾች እኩይ አጠቃቀም መዘዞች

በ140 ፊደላት በተለይ ትኩስ ትኩሱን ከሚቀነበበው ትዊተር አንስቶ፣ ከርሞም የሚላመጠውን ሽንጣም ሽንጣሙን ለማጋራት እስከሚፈቅዱት ድረ ገጾች፤ ወግ፣ ግጥም፣ ልብ ወለድ፣ ሙዚቃ፣ ወቅታዊ ጉዳዮች፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ትንታኔዎች፣ ስፖርቱ፣ ጡዝጦዛው ሁሉም በያይነት ዓይነቱ ከሞላባቸው የማኅበረሰብ ትስስር ድረ ገጾች፣ እንኳን ሲበሉ ሊታዩም የማይበቁም ሞልተዋል። አጠቃቀም ካላማረ ግልብነቱም የዚያን ያህል ነው። አንዴ ማኅበሩን ለተቀላቀለ ሰው ኢንተርኔት ባለበት ቦታ ላይ የማኅበረሰብ ትስስር ድረ-ገጾች በቀላሉ መገኘት ከመቻላቸው (accessibility) ጋር ተያይዞ ጉዳዮቻችንን እንደጻፍናቸው (እንደወረዱ) እንድናጋራ ስለሚያረገን፤ ቢያንስ እኛ ጋር ቆይተው እንዲበስሉ አንፈቅድላቸውም። ከዚህም ሌላ ይሆናሉ ያልናቸውን ስናጋራ የሚኖሩ አስተያየቶችም አንዳንዶቻችንን ወደኋላ ስለሚጎትቱን፤ ሁሉን ነገር የማጋራት አባዜ ውስጥ ይጥለናል። በመካከሉም ምስጢርና ቁም ነገር ይላላሉ። መብሰልና መለወጥ ይጠፋል። መከባበር ትቀጥናለች። ግልብ ሆነን ላይ ላዩን እንኖራለን። አካባቢያችንንም በአግባቡ እንዳንመለከትና ነገሮችን እንዳንመረምር እንጋረዳለን። የlike እና የcomment ገቢ ያሰክረንና እርስ በርስ እንኳኮታለን። ከእኛም አቅም ገጽታችንን ለመገንባት የወዳጆቻችንን ገጽታ እናፈራርሳለን። ታዲያ በዚህ ግርግር መሀል የምንናገረው አብዛኛው ነገር ከ'ብዬ ነበር' ያለፈ ውጤት ላይኖረው ይችላል። በዚህ የተነሳም ረከተን የተግባር ሰውነታችን ተፈትኖ ይወድቃል። በርግጥ ፀሐፊው ነጻነቱን ተጠቅሞ የጻፈውን አንባቢውም ነጻነቱን ተጠቅሞ ባተረፈበት ልክ አስተያየቱን ቢሰጥ አግባብ ነው።

እኛ የሚሰጠውን አስተያየት የምንመለከትበት ዐይን ግን የራሳችንን መንገድ ብሎም የሀሳብን ነጻ ፍሰት እድገት ይወስነዋል። ያም ሆኖ ግን አንባቢው የሚመለከተው ችግር እያለ፣ እየጎረበጠ፣ ቅር እያለ ...ባለበት ሁኔታ ላይ ችግሩን ደፍሮ መጠቆም ባይችል እንኳን በከንቱ ቢያወድስ የተሻለ ማደግ የሚችል ወዳጁን ያቀጭጨዋል። ባለፈው ዓመት በተደረገ አንድ ጥናት ላይ፤ ከአልኮል መጠጥ፣ ጣፋጭ ምግቦች፣ የዘንጦ ስልኮች (smart phone) እና ሌሎች መዝናኛዎች መካከል ምረጡ ከተባሉ የአንድ መስሪያ ቤት ሰራተኞች መካከል፣ 90 ከመቶ ያህሉ ስልኮቻቸውን መርጠው እንደነበር ታውቋል። ከእነሱ መካከል 35 በመቶ ያህሉ ደግሞ፣ ለተወሰኑ ሰዓታት ስልኮቻቸውን ካልያዙ ራቁት የመቆም ያህል እንደሚሰማቸው ገልጸዋል።

እንደሚገመተውም፤ ከስልክም ሆነ መሰል ቁሳቁሶች ጋር የጠነከረ ቁርኝት መፍጠሩ ከእድሜ ጋር የሚያያዝ ነው። ወጣትነት ላይ ትስስሩ ከፍ ያለ ሆኖ፣ እድሜ በጨመረ ቁጥር እየቀነሰ ይሄዳል። ከዚህም ባሻገር፤ ከመገናኛ ቁሶች ጋር በተያያዘ የተለያዩ ችግሮች በተለያዩ ጊዜያት ይፋ ቢደረጉም አጠቃቀምን በማስተካከል ረገድ ብዙም ለውጥ አይታይም። የዘንጦ ስልኮች ተጠቃሚዎች የትራፊክ አደጋን በማባባስ ረገድ ከጠጥቶ አሽከርካሪዎች ጋር ሊፎካከሩም ይችላሉ። ከዘንጦ ስልኮች ባሻገር ደግሞ በመደበኛው ተንቀሳቃሽ ስልክም፣ የጽሑፍ መልዕክት በመላላክ ወቅት የሚደርሱ አደጋዎች ብዙ ናቸው። ሌሎች ሰዎች ላይ ጉዳት ከማድረስ ባሻገር፤ በራስም የሰውነት ጤና ላይ የሚፈጥሯቸው ችግሮች አሉ። ይሄኔ ነው፣ ዘንጦ ስልክ ላይ የማኅበረሰብ ትስስር ገጾችን የመጠቀም ልምድ ሲጨመር «በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ» ማለት።

ይቀጥላል

ዜና

በኢዩኤል ፍሥሐ

አቃቤ ሕግ በተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮቹ ላይ የጠየቀው ይግባኝ ያስቀርባል ተባለ

ከሐምሌ 1 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ በእስር ላይ የሚገኙትና በፌዴራሉ አቃቤ ሕግ የሽብርተኝነት ክስ ተመስርቶባቸው በፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 19ኛ ወንጀል ችሎት በነፃ የተሰናበቱት፤ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች የነበሩትና በተመሳሳይ የክስ መዝገብ ውስጥ ከአመራሮቹ ጋር የሚገኘው አቶ አብርሃም ሰለሞን፣ ላይ አቃቤ ሕግ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት የጠየቀው ይግባኝ እንደሚያስቀርብ ፍርድ ቤቱ ገለጸ::

ሕዳር 6 ቀን 2008 ዓ.ም የተሰየመው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፤ በተቃዋሚ ፓርቲ አመራር በነበሩት አቶ አቶ የሺዋስ አሰፋ፣ አቶ አብርሃ ደስታ፣ አቶ ሐብታሙ አያሌው፣ አቶ ዳንኤል ሺበሺና በሌላኛው ተከሳሽ በአቶ አብርሃም ሰለሞን ላይ አቃቤ ሕግ የጠየቀባቸውን ይግባኝ መመርመሩን ገልፆ፤ «ይግባኙ ያስቀርባል» በማለት ውሳኔውን አስተላልፏል:: ፍ/ቤቱ ዝርዝር ሁኔታውን በንባብ ሳያሰማ ይግባኙ እንደሚያስቀርብ ብቻ በመግለፅ ተከሳሾቹ በአካል በመቅረብ የቃል ክርክር እንዲያደርጉ ለህዳር 29 ቀን 2008 ዓ.ም ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል::

«በእነ ዘላለም ወርቅአገኘሁ» የክስ መዝገብ ውስጥ ይገኙ ከነበሩት 10 ተከሳሾች መሃል አምስቱ ተከሳሾች፡ - አቶ የሺዋስ አሰፋ፣ አቶ አብርሃ ደስታ፣ አቶ ሐብታሙ አያሌው፣ አቶ ዳንኤል ሺበሺና አቶ አብርሃም ሰለሞንን ከተመሰረተባቸው የሽብርተኝነት ክስ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 19ኛ ወንጀል ችሎት ነሐሴ 14 ቀን 2007 ዓ.ም «በነፃ ተሰናብተዋል» በማለት ብይን ማስተላለፉ ይታወሳል:: የሥር ፍርድ ቤቱ በነጻ ያሰናበታቸው አምስቱም ተከሳሾች ከእስር እንዳልተለቀቁ ይታወቃል::

አቶ አብርሃም ጌጡ መደበኛ ክስ ተከፈተባቸው ፍ/ቤቱ በዋስ እንዲወጡ ውሳኔ አስተላልፏል

በቀድሞ የመኢአድ ፕሬዚዳንት አቶ ማሙሸት አማረ ካቢኔ ውስጥ የውጪ ግንኙነት ኃላፊ በመሆን ሲያገለግሉ የነበሩት፤ አቶ አብርሃም ጌጡ ሕዳር 7 ቀን 2008 ዓ.ም ከተከላካይ ጠበቃቸው አቶ ብሩክ ደረጀ ጋር በአራዳ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት 5ኛ ወንጀል ችሎት ቀርበው፤ የቀረበባቸውን ክስ ፍ/ቤቱ በንባብ አሰምቷል::

መንግሥት አይኤስን ለማውገዝ በጠራው ሰልፍ ላይ አመፅና ሁከትን ለማነሳሳት ሞክረዋል፣ የሃሰት ወሬዎችን በመንዛት ሕዝብን ለአመፅ እንዲነሳ አድርገዋል፣ «የቋራ አምበሳ» በሚል የፌስ ቡክ አካውንታቸው «አንድን ማኅበረሰብ የሚያጠለሽ ቃል እየተጠቀሙ ቅስቀሳ ሲያደርጉ ነበር» የሚሉ ክሶች በአቃቤ ሕግ በኩል እንደቀረበባቸው ለመረዳት ተችሏል:: የተከሳሹ ተከላካይ ጠበቃ አቶ ብሩክ ደረጀ፣ ፍ/ቤቱ ለደምበኛቸው የዋስትና መብታቸውን እንዲስያከብር ጠይቀዋል:: «ደምበኛዬ የተከሰሰበት አንቀፅ የዋስትና መብት ስለማያስከለክል፤ እንዲሁም ቋሚ የመኖሪያም ሆነ የሥራ አድራሻ ስላላቸው፤ የዋስትና መብታቸው እንዲከበርላቸው እንጠይቃለን ሲሉ ፍ/ቤቱን ጠይቀዋል:: ፍ/ቤቱ የተከሳሹን ወርሃዊ ገቢ ከጠየቀ በኋላ በ5000 ብር የገንዘብ ዋስትና በዋስ እንዲወጡ ፈቅዷል::

አቶ አብርሃም፣ ይህ መደበኛ ክስ ከተከፈተባቸው በፊት በሽብር ክስ ተከሰው ለአምስት ጊዜያት ያህል በአራዳ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቀርበው፤ የጊዜ ቀጠሮ እየተጠየቀባቸው ቆይተዋል:: ተከሳሹ ከሰኔ 12 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ በአምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ታስረው የቆዩ ሲሆን፤ ሐምሌ 16 ቀን 2007 ዓ.ም ወደ ፌደራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ማዕከል (ማዕከላዊ) ተዘዋውረዋል:: አቶ አብርሃም በማዕከላዊ ከፍተኛ ድብደባ እንደተፈፀመባቸው መናገራቸው የሚታወስ ነው:: ማተሚያ ቤት እስከገባንበት ሰዓት ድረስ አቶ አብርሃም ከእስር እንዳልወጡ ለማወቅ ችለናል::

<<በእነሚካኤል ያሬድ>> መዝገብ ሥር የሚገኙት ተከሳሾች መከላከያ ምስክሮቻቸውን አሰሙ

በኮሚኒኬሽን መ/ቤት ትሰራ የነበረችው ወ/ሪት ማህሌት ኤርሲዶ ድብደባ እንደተፈፀመባት ለፍ/ቤቱ አስረድታለች

መንግስት አይኤስን ለማውገዝ በጠራው ሰልፍ ላይ «ስብሳባን አውከዋል» የሚል ክስ የቀረበባቸው በሚካኤል ያሬድ መዝገብ ሥር ከሚገኙት ተከሳሾች ውስጥ፤ መከላከያ ምስክሮቻቸውን ካላሰሙት 6 ተከሳሾች መሃል 3ቱ ምስክሮቻቸውን አሰሙ::

ሕዳር 7 ቀን 2008 ዓ.ም በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት 5ኛ ወንጀል ችሎት ከቀረቡትና መከላከያ ምስክሮቻቸውን ካሰሙት መካከል 11ኛ ተከሳሽ ወ/ሪት ማህሌት ኤርሲዶ፣ 13ኛ ተከሳሽ ወ/ሪት ረህማ ጀማልና 14ኛ ተከሳሽ አቶ አንዷለም መሃሪ ይገኙበታል:: በዚህ መዝገብ ሥር ከሚገኙትና ብይን ካላገኙት 14 ተከሳሾች መሃል መከላከያ ምስክሮቻቸውን ያላሰሙት 11ኛ፣ 12ኛ፣ 13ኛ፣ 14ኛ፣ 17ኛ እና 18ኛ ተከሳሾች ይገኙበታል:: ፍ/ቤቱ የእነዚህን መከላከያ ምስክሮች ለመስማት ተሰይሞ የነበረ ቢሆንም፤ የሶስቱን ምስክሮች ብቻ አድምጧል:: በዕለቱ 12ኛ እና 17ኛ ተከሳሾች መከላከያ ምስክሮቻቸውን አሟልተው ስላላቀረቡ ተለዋጭ ቀጠሮ እንዲሰጣቸው ፍ/ቤቱን ጠይቀዋል::

በዕለተ ማክሰኞ ሕዳር 7 ቀን 2008 ዓ.ም በችሎቱ በመገኘት መከላከያ ምስክሮቿን ካስደመጠችው መካከል አንዷ የሆነችውና በኮሙኑኬሽን ፅ/ቤት ትሰራ እንደነበር የገለፀችው ወ/ሪት ማህሌት ኤርሲዶ፣ የተከሳሽነት ቃሏን በምትሰጥበት ጊዜ ድብደባ እንደተፈፀመባትና ሌሊት ላይ በአምስት ወንድ ፖሊሶች ምርመራ እንደተካሄደባት ለፍ/ቤቱ አስረድታለች:: በደረሰባት ድብደባ የተነሳም ጆሮዋን አሁንም ድረስ እንደሚያማትና ባላነበበችው ወረቀት ላይ ለመፈረም እንደተገደደች ለፍ/ቤቱ ገልፃለች:: ተከሳሿ ይህ ሁላ ድርጊት ተፈፀሙብኝ ያለችው ቃሌን ሰጠሁበት ባለችው ወረዳ 9 ፖሊስ ጣቢያ መሆኑን ጠቁማለች:: ወ/ሪት ማህሌት የቀረበብኝን ክስ ለመከላከል ይረዱኛል እንዲሁም ድብደባ እንደተፈፀመብኝ ያስረዱልኛል ያለቻቸውን አራት መከላከያ ምስክሮች ለፍ/ቤቱ አሰምታለች:: ከአራቱ መከላከያ ምስክሮች መካከል አብረዋት በወረዳ 9 ፖሊስ ጣቢያም እንዲሁም አሁን በምትገኝበት ቃሊቲ ማረሚያ ቤት ታስረው የሚገኙት ወ/ሪት ራህማ ጀማልና ወ/ሪት ቤዛዊት ግርማ ለተከሳሿ በመከላከያ ምስክርነት በመቅረብ ቃላቸውን ለፍ/ቤቱ ሰጥተዋል::

ቤዛዊትም ሆነች ራህማ ወ/ሪት ማህሌት፣ ድብደባው ተፈፅሞባት ስትመጣ በሰውነቷ ላይ የሚገኘውን ሰንበር እንዳሳየቻቸው ለፍ/ቤቱ በሰጡት የምስክርነት ቃላቸው ገልፀዋል:: ወ/ሪት ማህሌት በዕለቱ የተከሰስኩበትን ድርጊት እንዳልፈፀምኩ ያስረዱኛል ያለቻቸውንና በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት በሰላማዊ ሰልፉ ላይ አብረውኝ ነበሩ ያለቻቸውን ሁለት ግለሰቦችም በመከላከያ ምስክርነት አሰምታለች::

ከወ/ሪት ማህሌት ኤርሲዶ በመቀጠል መከላከያ ምስክሮቿን ያቀረበችው 13ኛ ተከሳሽ ወ/ሪት ራህማ ጀማል የተከሳሽነት ቃሏን ከሰጠች በኋላ በዕለቱ አብረውኝ ነበሩ ያለቻቸውንና የቀረበብኝን ክስ ለመከላከል ያስችሉኛል ያለቻቸውን 3 ምስክሮች አሰምታለች::ሶስቱም ምስክሮች በተመሳሳይ መልኩ ተከሳሿ በክሱ ላይ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት አብረዋት እንደነበሩ ለፍ/ቤቱ አስረድተዋል:: በምስክርነት የቀረቡት የተከሳሿ መከላከያ ምስክሮች በዕለቱ በቁጥጥር ስር አብረዋት ውለው እንደነበርና በንጋታው አሻራ ሰጥተው መለቀቃቸውንና እሷ ግን ከእነሱ ተለይታ እንዳልተለቀቀች ለፍ/ቤቱ በሰጡት የምስክርነት ቃል አስረድተዋል:: ከወ/ሪት ረሃማ ጀማል ቀጥሎ 14ኛ ተከሳሽ አቶ አንዷለም መሃሪ፣ የተሳሽነት ቃሉን ከሰጠ በኋላ ክሴን ለመከላከል ያረዱኛል ያላቸውን ሁለት ምስክሮች አሰምቷል::

18ኛ ተከሳሽ የሆነችውና በዛሚ ኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያ ትሰራ የነበረችው ጋዜጠኛ ቤዛዊት ግርማ መከላከያ ምስክሮችን አቅርባ የነበረ ቢሆንም፤ ፍ/ቤቱ ምስክሮቿን ሳያደምጥ ቀርቷል:: ቤዛዊት ምስክሮቼ ተማሪዎች ስለሆኑ ላይመቻቸው ስለሚችል ይሰሙልኝ ብትልም፤ ፍ/ቤቱ የ12ኛ እና የ17ኛን ተከሳሾች ምስክር ለማድመጥ በድጋሚ መሰየሙ እንደማይቀር በመግለፅ ምስክሮቿን ለመስማት ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቷል:: በዚህም መሰረት የ12ኛ ተከሳሽ ወ/ሪት ምስለ ሀይሉ፣ የ17ኛ ተከሳሽ አቶ አብዱልከሪም ሽኩር እንዲሁም የ18ኛ ተከሳሽ ወ/ሪት ቤዛዊት ግርማን መከላከያ ምስክሮች ለማድመጥ ተለዋጭ ቀጠሮ ለህዳር 30 ቀን 2008 ዓ.ም ሰጥቷል::

መከላከያ ምስክሮቻቸውን ካሰሙት ስምንት ተከሳሾች መሃል 19ኛ ተከሳሽ አቶ ሰለሞን ካህሳይ ብቻ በእለቱ ብይን አግኝተዋል:: ፍ/ቤቱ አቶ ሰለሞን ካህሳይን ጥፋተኛ በማለት በሶስት ወር ቀላል እስራት እንዲቀጡ በይኗል::አቶ ሰለሞን ፍ/ቤቱ ካስተላለፈባቸው ቅጣት በላይ በእስር ጊዜ እንዳሳለፉ ለማወቅ ተችሏል:: መከላከያ ምስክሮቻቸውን ባሰሙት ቀሪ ተከሳሾች ላይ ፍ/ቤቱ በሚቀጥለው ቀነ-ቀጠሮ ብይን ይሰጣል ተብሎ ይጠበቃል:: «በእነ ሚካኤል ያሬድ» ክስ መዝገብ ሥር ከሚገኙት 19 ተከሳሾች መሃል 5ቱ የቀረበባቸውን ክስ መከላከል ሳያስፈልጋቸው ፍ/ቤቱ በነፃ እንዳሰናበታቸው ይታወሳል::

አሁንም ያልፀዳው ቤት - የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን

ፍርድያውቃል ንጉሴ
firdyawkal@gmail.com

እንደመንደርደሪያ

በአፍሪካ ካሉ የሀገራት የእግር ኳስ ፌዴሬሽኖች ቀደምት የሆነው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የተቋቋመው በ1936 ዓ.ም ነው:: የሚገርመው የአህጉሪቷ የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን እንኳን የተቋቋመው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ከተቋቋመ ከ13 ዓመታት በኋላ (በ1949 ዓ.ም) መሆኑ የኢ/እ/ፌ ምን ያህል በዕድሜ አንጋፋ እንደሆነ የሚያረጋግጥ ነው::

የሚገርመው ግን፣ አይደለም ለተቋም ለሰው ልጅ እንኳን «ዕድሜን የመሰለ ትምህርት ቤት የለም» በሚል ዕድሜን ተከትሎ የሚመጣው ዕውቀት ቢገለጽም የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌደሬሽን ግን የዕድሜውን ያህል በብስለት የሚመራ፣ የተደራጀ እና ከዘመኑ ጋር የሚራመድ እንዲሁም በዘመኑ የአመራር አስተምሮት የሚመራ ተቋም ሊሆን ቀርቶ «የባሰ አታምጣ» እንደሚባለው የፌዴሬሽናችን ሽበት እንደው ያለብስለት መሆኑ በተደጋጋሚ እየታየ ነው::

ይህ ፌዴሬሽን በየአምስት ዓመቱ ግልጽ ባልሆነ መልኩ በሚካሂደው የምርጫ ሂደት የተለያዩ አመራሮችን ቢያፈራርቅም «ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥ» እንደሚባለው ሰርክ አሳፋሪ ከሆኑ ስህተቶች ሳይፀዳ፣ ዘወትር ከአንድ ተቋም የማይጠበቁ ስህተቶችን እየሰራ ይህው አሁን ያለንበት ደረጃ ላይ ደርሰናል::

በተለይ በተለይ ሰሞኑን ዝርክርክነት በተጠናወተው በዚህ ተቋም ምክንያት ሉሲዎቻችን ከወዲሁ ከ2016ቱ የካሜሮኑ የአፍሪካ ዋንጫ ውጪ መሆናቸው ተረጋግጧል:: ይህ ክስተት ደግሞ በሀገራችን ሰሞናዊ ትኩሳትን የፈጠረ አነጋጋሪ አጀንዳ ሆናል:: በዛሬው ጽሑፌ እኔም ይህንን የሰሞኑን ክስተትና በተጣይ መደረግ ስላለባቸው አካሄዶች ጥቂት እላለሁ:: በመጀመሪያ ግን ስለእህቶቻችን ይህን ማለት ወደድኩ::

ክብር ለሉሲዎች

እውነት እንነጋገር ከተባለ፣ በሀገራችን ውስጥ እግር ኳስ እንደስፖርት መዘውተር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከአሁን ባለው ሂደት በአንጻራዊነት ውጤታማ የሆንነው በወንዶች ሳይሆን በሴቶች እግር ኳስ ነው ብል ማጋነን አይሆብኝም:: ምክንያቱም አንደኛ እነርሱ ወደ መድረኩ ብቅ ካሉበት አጭር ጊዜ አንጻር ያጣጣሚቸው በርካታ ስኬቶች፤ ሁለተኛ ደግሞ ከእነርሱ ጋር በተያያዘ እና ምንም ሳንለፋ እንደዕድለኛ ገበሬ ሳንዘራ ነውና ያሳጨዱን::

በርግጥም እነዚህ ሴቶቻችን እጅግ በጣም ጀግናዎች ናቸው:: ለእነሱ ክብር እንስጥ ብንል እንኳን ከሀ እስከ ፐ ያለውን የፊደል ገበታችን ይበቃናል ብዬ አላስብም::

ታዲያ እነርሱ እንዲህ በራሳቸው ጥረት ውጤታማ ሆነው፣ ውጤታማ ባደረጉን በዚህ ወቅት እኛ ለእነሱ የተቻለንን ሁሉ ማድረግ ሲጠበቅብን፣ ይባስ ብሎ በትልቅ ውድድር ላይ እንዳይወክሉን፣ እነሱም የመጫወት ጥማታቸውን እንዳይቆርጡ ይህን አይነት ስህተት መስራት እንኳን የስፖርቱ የበላይ ጠባቂ ከሆነ ተቋም ቀርቶ ከግለሰብ እንኳን የማይጠብቅ በጣም አሳፋሪና እጅግ ዘግናኝ የሆነ ክስተት ነው::

ከዚህ በፊት በነበሩ የፌዴሬሽን አመራሮች ወቅት፣ ከቢጫ ካርድ ጋር ከተያያዘው ጉዳይ አንስቶ በርካታ ስህተቶች ሲሰሩ አይተናል:: ግን ይኼኛው ስህተት ከሌሎቹ ሁሉ የሚለየው በሌሎቹ ወቅት ወዲያውኑ ወይ ማስተባበያ ሲሰጥባቸው አሊያም ህዝቡ በይፋ ይቅርታ ሲጠይቅ በዚህ በአሁኑ ፌዴሬሽን ግን ይቅርታ መጠየቁ ቀርቶ ማስተካከያ እንንለመስጠት ከሁለት ሳምንት በላይ መቆየቱና በተቃራኒው ምንም እንዳልተፈጠረ ዝም መባሉ፣ እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ ሀገርን ከመናቅ፣ ህዝብን ከመናቅ፣ ባንዲራን ከመናቅ ውጪ ምንም የተለየ ትርጉም የማይሰጠው ነው::

ለአንድ ሀገር ደግሞ ከዚህ በላይ ውርደትና ውድቀት የለም:: እንዴ! ጎበዝ! አንድ ትልቅ ሀገራዊ ተቋም መሰል ስህተትን ሰርቶ፤ በስህተቱ ማግሥት ዝምታን የሚመርጥ ከሆነ ነገ ከነገ ወዲያ ይህ ስህተት ላለመደገሙ ምን ዋስትና አለን? ሃይ የሚለው የመንግሥት ተቋምስ የለም? ይህ ሀገራዊ ተቋም ነገሮችን በዚህ መልኩ ከከወነ ነገ ከነገ ወዲያ ግለሰቦች መሰል ተግባራትን ቢፈጽሙ የምንናገርበት ምንስ አንደበት ይኖረናል?

እኔ ግን እላለሁ፣...እናንተ ሉሲዎች ትልቅ ክብርና ምስጋና ይገባችኃል! ...እናንተ ሉሲዎች ህልማችሁ በንዝህላሎች ቢቀጭም እመኑ ገና ብዙ ርቀት ትጓዛላችሁ! ...እናንተ ሉሲዎች የእኛ የኢትዮጵያውያንና የሀገራችን የኢትዮጵያ ኩራትና ግርማ ሞገስ ናችሁ! ...እናንተ ከናንተ የሚጠበቀውን ዘወትር ከአቅማችሁ በላይ ትወጣላችሁና የዘላለም ክብር ይገባችኃል!

የነጺላጦስ ጨዋታ

ካሜሮን ለምታዘጋጀው ለ2016ቱ የሴቶች የአፍሪካ ዋንጫ ላይ መሳተፍ የሚፈልጉ ሀገራት በምድብ ማጣሪያው ድልድል ላይ ይካተቱ ዘንድ ለየኮንፌዴሬሽኑ አባል ሀገራት ካፍ የማረጋገጫ ደብዳቤ እንዲልኩ ጠይቆ የነበረ ቢሆንም የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ግን ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ዝምታን መምረጡን ተከትሎ ሉሲዎቹ ከ2016ቱ የአፍሪካ ዋንጫ ውጪ መሆናቸውን ካፍ ባለፈው ማክሰኞ ጥቅምት 23 ቀን አረጋግጧል::ይኼ ሒደት ደግሞ ፌዴሬሽኑ ምን ያህል ነገሮችን በአግባቡ የመከወን አቅም እንደሌለው የሚያሳብቅ ነው::

ከዚህ ከተከሰተው ችግር በላይ የሚገርመው ነገር ስለችግሩ ፌዴሬሽኑ ከሳምንት ጊዜ በላይ ምንም አለማለቱ እና ለጥፋቱ ኃላፊነቱን የሚወስድ አካል መግለጫ እስከተሰጠበት እስከ ዕለተ ሐሙስ ድረስ በውል አለመታወቁ ነው::

በሀሙስ የመግለጫው ወቅትም ከዚሁ ጋር በተያያዘ «ጥፋተኛ ናቸው» በማለት አንድ የፌዴሬሽኑ ሥራ አስፈፃሚና ሁለት ተቀጣሪ ሰራተኞች መታገዳቸውና መሰናበታቸው ነው የተገለፀው:: የሚገርመው፣ እነዚህ ሶስት ግለሰቦች ሁሉም ጉዳዩ እነርሱን እንደማይመለከትና መታገዳቸው አግባብ እንዳልሆነ ገልፀዋል:: ሥራ አስፈጻሚው ግለሰብ፣ እንዲያውም በዚህ ዙሪያ በግላቸው ጋዜጣዊ መግለጫ በመጥራት ጉዳዩን ያስረዱ ሲሆን፤ ከሁለቱ ተሰናባች ሰራተኞች መካከል አንዷ የሆነችው የአይቲ ባለሙያዋም፣ ይህ ጉዳይ መፈጸሙ እርሷን እንደማይመለከትና በዚህ ዙሪያ ምንም ደብዳቤ ከፌዴሬሽኑ ሳይደርሳት ስለተወሰነባት ውሳኔ እንኳን እንደሌላ ሰው ከጋዜጣዊው መግለጫ በኋላ መስማቷን ለኢትዮፒካሊንክ የሬዲዮ ፕሮግራም ተናግራለች::

ይህ አካሄድ ደግሞ በፌዴሬሽኑ አመራሮች መካከል የ«እከክልኝ ልከክልህ» ነገር እንዳለ በሚገባ የሚያረጋግጥ ነው:: ዘመናችን ከድሮው የማኔጅመንት ሥርዓት ወጥቶ በሊደርሺፕ የአመራር ብቃት በሚተዳደርበት በዚህ ዘመን ላይ ይህ ፌዴሬሽኑ መሰል ስህተትን ሰርቶ ስህተቱን መሸፋፈኑ፤ መደባበቁና በኋላ ላይም ምንም ፈር የሌለው፣ ያልጠራና ለማንም አስተማሪ ያልሆነ እርምጃን መውሰዱ ምን ያህል ኋላ ቀራዊ አመራርን እንደሚተገብር የሚያሳብቀቅ ነው::

በአንድ ተቋም ውስጥ መሰል ስህተት ሲፈጸም፣ ለጥፋት ሰሪው አካል ተገቢ የሆነ፣ ወቅታዊና ስሜታዊ ሳይሆን፣ ሚዛናዊ የሆነ ግብረ መልስ መስጠት የሚቻለው፣ በመጀመሪያ ነገሩን ወዲያውኑ በግልጽነት ይፋ አውጥቶ መወያየት እና ጉዳዩን በሚገባ መፈተሽ ሲቻል እንደሆነ በዓለማችን በአመራር ጥበብ አስተምህሮት ስመጥር የሆነው ስቴቨን አር ኮቬይ ይናገራል::

ይህ ካልሆነ ግን፣ ውጤቱ ከፍተኛ ውድቀት እንደሆነ ግልጽ ነው:: ከዚህ አንጻር የፌዴሬሽኑ አመራሮች ነገሮችን በአግባቡ አስተውለው፣ ተገቢውን እርምጃ ካልወሰዱ በስተቀር ሌላው ቀርቶ መሰል ስህተቶች ነገ ላይ ስላለመደገማቸው ምንም ዋስትና የለም:: በተለይ በተለይ፣ የፌዴሬሽኑ አመራሮች ይህን የመደባበቅ እና «ከደሙ ንፁህ ነኝ» አይነት ጲላጦሳዊ አካሔዳቸውን ካላስወገዱ ነገ ላይ ነገሮችን አባብሶ «ምነው በእንቁላሉ ጊዜ...» ማስባሉ አይቀሬ ይሆናል::

ሶስቱ መፍትሔዎች

የፌዴሬሽኑ አመራሮች ውስጥ የቅንነት መንፈስ ካለ፣ እንደውም ይህንን አጋጣሚ ለመልካም ዕሴት ሊያወሉት ይችላሉ:: «እንዴት?» እንደዚህ አይነት ስህተቶችን የሚሳሳቱት፣ አንድም ሁሉም የሥራ ክፍል የየራሱን የሥራ ድርሻ ባግባቡ ስለመወጣቱ ሁለቱም በተቋሙ ውስጥ ተከታታይ ግምገማ (tentative evaluation) ባለመከናወኑ ነው::

ከዚህ በኋላ ግን መሰል ስህተቶች እንዳይደገሙ እና በቀጣይ ሌሎች ሥራዎች ላይም ተመሳሳይ ጋሬጣዎች እንዳይደቀኑ ፌዴሬሽኑ ሁለት ነገሮች ላይ አበክሮ መስራት ይጠበቅበታል::

አንደኛ፡- እያንዳንዱ የሥራ ሂደት በውስጡ የማያልፉ ሥራዎችን እንዴት እንደከወኑ በየሳምንቱ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ማድረግ እና ከዚህ በኋላ እንደተቋም በየአስራ አምስት ቀኑ አጠቃላይ ግምገማ ማከናወን:: ተቋማት እንዲህ በሚያደርጉበት ጊዜ ይለናል ስቴቨን አር ስቬይ ... «ተቋማት እንዲህ ማድረግ በሚጀምሩበት ሰዓት ሁሉም ሰራተኞች በንቃት እና በሙሉ የኃላፊነት ስሜት ልክ እንደ አለቃ ስለ ሥራቸው መጨነቅ እና ሥራቸውን በአግባቡ መስራት ይጀምራሉ::» (Stephen R. Covey, the 7 habits of highly effective people pp. 227)

ሁለተኛ፡- «በምን ስሌትና በምን ቀመር ነው ጠቅላላ ጉባዬ ሳይጠራ የስራ አስፈፃሚ የሆነና የተቋሙ ቋሚ የሆኑ ሁለት ሰራተኞች የሚሰናበቱት?» በእርግጥ ካጠፉ እንደ ተቋሙ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ነው መስተናገድ ያለባቸው:: ግን አሁን እየሰማናቸው ያሉት ነገሮች፣ የግለሰቦቹን ጥፋተኝነት የሚያረጋግጡ አይደሉም::ከዘጠና ሁለት ሚሊየን በላይ ሰዎችን የሚወክለው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽንም እንደ ግዙፍ ተቋምነቱ በምንም አይነት መሰል ክፍተቶች ሊታዩበት አይገባም::

ደግሞ የዘመናችን የአመራር ንድፈ-ሐሳቦችም (Leadership Theories) ይህን አካሔድ አይደግፉትም::ከዛ ይልቅ፣ መሰል ስህተቶች ሲከሰቱ የዘመኑ አካሔድ በሚፈቅደው መሰረት ነገሮችን በአግባቡና በሰከነ ስሜት፣ እንዲሁም ከአለቃ እስከ ምንዝር ለሁሉም ግልፅ በሆነ መልኩ ነው ስህተቱ መፈተሽ፣ ከዛም ክፍተቶች መሞላት ያለባቸው::

...ይህ እንዲሆን ደግሞ በዋናነት የፌዴሬሽኑ አመራሮች ወደ ኋላ መለስ ብለው አጠቃላይ መተዳደሪያ ደንባቸውን እንደገና መከለስና ከዘመኑ ጋር አብሮ የሚራመድ አድርጎ ማርቀቅ ይጠበቅባቸዋል:: ነገር ግን፣ ችግር በተከሰተ ቁጥር ለማንም ግልፅ ባልሆነ መልኩ እንደው ብድግ ብሎ፣ መሰል እርምጃዎችን መውሰድ ከፋይዳው ይልቅ ህፀፁ፤ ከፅድቁ ይልቅ ኩነኔው ያመዝናል:: ትርፋም ትርፍ የለሽ ነው::

ሶስተኛ፡- የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌደሬሽን እንደ አንድ ተቋምነቱ በመጀመሪያ ትኩረት መስጠት ያለበት ለአንድ ሰሞናዊ ውጤት ሳይሆን አጠቃላይ ያንን ውጤት ስለሚያመጣው የሥራ ሂደት /method/ መሆን አለበት:: ይህንን የአሰራር ሒደት ደግሞ አስተካክሎ ግቡን መምታት የሚቻለው ደግሞ ከላይ የተጠቀሰው ወቅታዊው ክትትል እና ግምገማ ሳይቋረጥ ሲዘልቅ ነው:: እነዚህ ካልተተገበሩ ግን ምን እንደሚበጀን ለመናገር ይከብዳል::



ዮዲት መላኩ የግንባታ ማጠናቀቂያ ስራዎች ተቋራጭ

YODIT MELAKU GENERAL FINISHING WORKS

0911-63 34 81 0911-111472 0118681747

ሥራዎቻችን

Our Works

የአሉሚኒየም
የጂፕሰም
ባልስትሬድ
የኳርትዝ ቅብ
የቤት ውስጥ ዲዛይን

General Aluminum works
General Gypsum works
Balustrade works
Interior design
Quartz painting





addis getse